# ረ

**ረ** በዚህ መዝገበ ቃላት ፊደል ተራ መሰረት ከ "መ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

**ረሀጥ** ቅ ሙያ የሌላት ሰነፍ፥ ገልቱ(ሴት)።

**ረሃብ** "ራበ" ስር ተመ.

**ረሃብተኛ** ዝ.ከ.

**ረመረመ** ግ በእግር ረገጠ፥ ረጋገጠ፥ ጠቀጠቀ።

**ተረመረመ** ግ በእግር ተረገጠ፥ ተረጋገጠ።

***ረመሰመሰ**

**ርምስም አለ** ግ ተርመሰመሰ።

**ተርመሰመሰ** ግ በብዛት ሆኖ ተንቀሳቀሰ፥ ተላወሰ።

**አርመሰመሰ** ግ 1. በብዛት አንቀሳቀሰ። 2. አተራመሰ።

***ረመደ**

**ርምድ** ስ በሩካቤ ስጋ ምክንያት ወደ ሌላው የሚተላለፍ የቂጥኝ ቁስል በሽታ አይነት።

**[እ]ርምጃ** ስ 1. አካሄድ፥ አረማመድ። 2. በመራመድ ሂደት ላይ ባሉት ሁለት እግሮች መካከል ያለ የቦታ ርዝመት፥ መጠን። 3. እድገት፥ መሻሻል። *ስራው ርምጃ አሳይቷል።* 4. አንድ ግብ ለመድረስ፥ አላማን ለማሟላት የሚደረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ፥ ውሳኔ።*አንድ ርምጃ ካልተወሰደ ነገሩ ፍፃሜ አያገኝም።* 5. ቅጣት። በጥፋተኞቹ ላይ ርምጃ ተወስዷል።

**ራመድ አለ** ግ ሄድ አለ፥ ተራመደ።

**ራመድ ራመድ አለ** ግ እየፈጠነ ሄደ፥ ተራመደ።

**ተራመደ** ግ 1. ሄደ፥ ገሰገሰ። 2. አልፎ፥ ዘልሎ፥ ተሻግሮ ሄደ። 3. እድገት ወይም መሻሻል አሳየ።

**ተራማጅ** ቅ 1. ሂያጅ፥ ፈጣን፥ ገስጋሽ። 2. የህብረተሰብን እድገት ወደፊት ለማራመድ የሚረዳ (አስተሳሰብ፥ አዋጅ፥ አመለካከት፥...)። ስ 3. በአንድ የታሪክ ወቅት የህብረተሰብን እድገት ወደፊት ለማራመድ የሚጥር፥ የሚታገል ሰው።

**መራመጃ** "መረማመጃ"ን ተመ.

**ተረማመደ** ግ 1. ተላለፈ፥ ተሸጋገረ። 2. ረግጦ አለፈ፥ ተሻግሮ ሄደ። 3. አደገ፥ ወደፊት ሄደ (በማእረግ፥ በትምህርት)።

**መረማመጃ(መራመጃ)** ስ መተላለፊያ፥ መሸጋገሪያ፥ መወጣጫ።

*መረማመጃ የለም መፈናፈኛ የለም፥ ጠባብ ነው።*

**አራመደ** ግ 1. አስኬደ። *እግሩ ላላራምድ አለው/መንገዱ ድንጋያማ በመሆኑ እንደልብ አያራምድም።* 2. አካሄደ፥ አስፋፋ፥ አቀነቀነ (ርእዮተ አለም)። *አገሪቱ የሶሻሊስትን ርእዮተ አለም ታራምዳለች።*

**አራምዶ አየ** አሻግሮ አየ፥ ተመለከተ።

**አራማጅ** ቅ አቀንቃኝ። *የሶሻሊዝም ፍልስፍና አራማጅ።*

**አረማመደ** ግ 1. አሸጋገረ፥ አስተላለፈ። 2. አራቀ፥ አሸሸ።*ሌባው ከብቶቹን አረማመዳቸው።*

**አረማመድ** ስ የእግር አጣጣል፥ አካሄድ።

**ረመዳን** ስ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች፥ ፀሃይ ወጥታ እስከምትጠልቅ የሚፆሙበት በእስልምና የቀን አቆጣጠር ዘጠነኛው ወር።

**ረመጠ** ግ ረመጥ ውስጥ ከተተ፥ ጨመረ።

**ረመጥ** ስ የደቀቀ ፍም፤ ፍምነት ያለው አመድ።

**ረሞጫ** ስ ከፀሃይ ግለት የተነሳ እንደረመጥ የሚፋጅ አሸዋ፥ አካባቢ።

**ርሚጦ (ርሚጦሽ)** ስ ሊጡን በቅጠል ሸፍነው ረመጥ ውስጥ በማስገባት የሚያበስሉት ሙልሙል ዳቦ (ብዙውን ጊዜ ለውሻ የሚዘጋጅ)።

**[እ]ርምጥምጥ ([እ] ርሙጥሙጥ)** ቅ ልኩስኩስ፥ ፅዳት የለሽ።

**ተርመጠመጠ (ተርሞጠሞጠ)** ግ በቆሻሻ፥ በማይረባ ቦታ ተልኮሰኮሰ።

**አሪማጥ** ቅ 1. አመዳም፥ ጥላሸታም፥ ፅዳት የሌለው። 2. ጥቁርቁር ያለ፥ ጠቋራ።

**አርመጠመጠ (አርሞጠሞጠ)** ግ አልኮሰኮሰ፥ አጎደፈ፥ በቆሻሻ ነገር በከለ፥ለዋወሰ።

**ረሰረሰ** ግ ረጠበ፥ ራሰ፤ ወረዛ፥ ረዘረዘ።

**አረሰረሰ** ግ አራሰ፥ አረጠበ፥ አወረዛ።

**ረሰሰ** ግ በእርሳስ ምልክት አደረገ።

**[እ]ርሳስ** ስ 1. ክብደትና ለስላሳነት ያለው፥ በቀላሉ የሚቀልጥ የማእድን አይነት። 2. የጥይት አረር። 3. ለመፃፊያ፥ ለመሳያ የሚያገለግል ከእርሳስ ማእድን የሚሰራ የፅህፈት መሳሪያ። (ስእሉን ፅህፈት መሳሪያ ስር ተመ.)

**ረሳ** ግ 1. ዘነጋ፥ ሳተ፥ ማስታወስ አቃተው። 2.በመዘንጋት፥ ባለማስታወስ አንድን ነገር ሳይሰራ፥ ሳያከናውን፥... ቀረ። 3. ተወ፥ ከሃሳብ አወጣ፥ ትኩረት ሳይሰጥ ቀረ። *ምጡን እርሽው ልጁን አንሽው /ሃብት ሲያገኝ የቀድሞ ጓደኞቹን ረሳ።*

**አትርሳ** አንድ ሰው ብድሬን እመልሳለሁ

ለማለትና ቂም መያዙን ለማሳወቅ የሚጠቀምበት አነጋገር:: *መፅሃፋን ላውሰኝ ብልህ ከለከልከኝ ላይደል? ላትርሳ!*

**እርስት አደረገ** ግ 1. ዘነጋ:: 2. ባለማስታወስ፥ በመዘንጋት ሳይሰራ፥ ሳያከናውን ቀረ::

**ተረሳ** ግ 1. ሳይታወስ ቀረ፥ ተዘነጋ፥ ከአእምሮ ጠፋ:: 2. ባለመታወሱ፥ በመዘንጋቱ ተተወ ወይም ቀረ:: *ቦርሳዬ እቢሮ ተረሳ::*

**ተረሳሳ** ግ እየተተወ፥ እየቀረ፥ እየተዘነጋ ሄደ::

**አረሳሳ** ግ 1. አዘናጋ:: 2. ሃዘንን፥ ንዴትን አስተወ፤ አፅናና::

**ማረሳሻ** ስ ማባበያ፥ ማፅናኛ፥ማስረሻ፤ እንዲረሳ ማድረጊያ::

**ረሸነ** ግ ሰውን በፍርድም ይሁን ያለፍርድ በጥይት ደብድቦ ገደለ::

**ተረሸነ** ግ በጥይት ተደብድቦ ሞተ::

**ረሸ** ስ ለአደን የሚያገለግልና ጥይቱ ብዙ ፍንጣሪ ያለው ጠበንጃ::

**ረቀረቀ**[1] ግ 1. መላልሶ መታ፥ ደበደበ:: 2.ረዘም ላለ ጊዜ ጣለ፥ ዘነበ:: *ዝናቡ ሲረቀርቀው አደረ::*

**ረቀረቀ**[2] ግ ሻጠ፥ ሰካ፥ ሰነቀረ፥ ወጋ::

***ረቀረቀ**

**ተስረቀረቀ** ግ 1. ተንሰቀሰቀ አለቀሰ:: 2. ስሜት በሚነካ መልክ ተንቆረቆረ (የድምፁ፥ የዜማው ቃና)::

**አስረቀረቀ** ግ 1. አንሰቀሰቀ፥ አስለቀሰ:: 2. ስሜትን በሚነካ መልክ (ዜማን) አንቆረቆረ::

**ረቀቀ** ግ 1. አነሰ፥ ጥቃቅን ወይም ደቃቃ ሆነ:: 2. ደቀቀ፥ ላመ፥ ተፈጨ (የመገበሪያ ስንዴ):: 3. ቀጠነ፥ መነመነ:: 4. ለመረዳት፥ ለማወቅ የሚያስቸግር፥ ጥልቅ ወይም ውስብስብ ሆነ:: 5. የመጀመሪያና ያላለቀለት፥ በግርድፍ ያለ (የንግግር፥ የፅሁፍ፥... ረቂቅ) ፅሁፍ ተዘጋጀ::

**በረቀቀ ዘዴ** በብልሃት፥ በማይታወቅ ሁኔታ:: *ሌባው በረቀቀ ዘዴ እቃ ከሳጥን ውስጥ ላውጥቶ ወሰደ::*

**ረቂቅ** ቅ 1. ግዝፈት ወይም ትልቅነት የሌለው፤ መጠኑወይም ውፍረቱ በጣም ትንሽና ደቃቃ የሆነ:: 2.ትልቅነት ስለሌለው ወይም ደቃቃ በመሆኑ አስቸጋሪ የሆነና ከፍተኛ ጥበብ የሚጠይቅ (የጌጣጌጥ፥የእደጥበብ፥...ስራ)::3.በአይን የማይታይ፥ በእጅ የማይዳሰስ::4.ደቃቅ በሆነ (ጉልህ ባልሆነ) በትንንሽ ፊደል የተፃፈ (ፅሁፍ):: 5. ውስብስብና ጥልቅ የሆነ፥በቀላሉ መረዳት የማይቻል (አስተሳሰብ፥ የሳይንስ እወቀት፥ ዘዴ፥...):: ስ 6.የተፈጨ፥ የደቀቀ፥ የላመ የመገበሪያ ስንዴ ዱቄት:: 7. ስለ አንድ ነገር በመጀመሪያ በወረቀት ላይ የሰፈረ ሃሳብ (እንደስፈላጊነቱ ሊታረም የሚችል):: 8. ለውሳኔ፥ ለውይይት የቀረበ ፅሁፍ::

**ረቂቅ አዘጋጀ/ፃፈ** እንደስፈላጊነቱ ሊታረም የሚችልና ለመንደርደሪያ የሚሆን የመጀመሪያ ፅሁፍ ፃፈ፥ አቀረበ::

**ረቂቅ ነፍሳት** ስ በአካል ያሉና ያለ ማጉሊያ መነፅር መታየት የማይችሉ ነፍሳት::

**ረቂቅ አዋጅ** ስ ህግ ሆኖ እንዲወጣ፥ እንዲወሰን፥ እንዲፀድቅ ለፓርላማ፥ ለምክር ቤት፥ ለሸንጎ የቀረበ አዋጅ::

**ርቀት** ስ ጥልቀት፥ ረቂቅነት::

**ተረቀቀ** ግ የመጀመሪያ ደረጃ (ፅሁፍ፥ አዋጅ፥...) በወረቀት ሰፈረ::

**ተራቀቀ** ግ በሳይንስ፥ በፍልስፍና፥... መጠቀ፥ ተፈላሰፈ፥ ተጠበበ፥ ተመራመረ:: *በሳይንስ ተራቀቀ::*

**አረቀቀ** ግ 1. ፈጨ፥ አደቀቀ፥ አላመ:: 2. በትናንሽ የፊደል ቅርፅ ፃፈ:: 3. ቃል አውጣጣ፤ ለመጀመሪያ ወይም ለመንደርደሪያ የሚሆን ሃሳብ በፅሁፍ አዘጋጀ::

**አርቃቂ** ቅ ፍሬ ሃሳቦችን አጠናቅሮ የመጀመሪያ ወይም መነሻ የሚሆን ፅሁፍ የሚያዘጋጅ:: *ሕርቃቂ ኮሚቴ::*

**አራቀቀ** ግ 1. በእውቀት የጠለቀ፥ የረቀቀ እንዲሆን አደረገ:: *የከፍተኛ ት/ቤቶች መብዛት ሃገሪቱን በሳይንስ ጥበብ ሊያራቅቃት ቻለ::* 2. ስራውን፥ ጥበቡን የበለጠ ጥልቅ፥ ውብ፥ ጥርት ያለ እንዲሆን አደረገ:: 3. አመሰጠረ (ቅኔን)::

**ረበረበ** ግ 1. ደረደረ፥ ደራረበ፥ አነባበረ (እንጨትን፥ ብረትን፥...):: 2. ረፈረፈ፥ አነባበረ፥ አንዱን በሌላው ላይ ጣለ:: *ጠላቶቹን በጥይት ረበረባቸው::* 3. አርከፈከፈ፥ ረጨ:: 4. መንገድን (ድንጋይ በማንጠፍ፥...) አስተካከለ::

**መረባረብ** የ"ርብራብ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**ርብራብ** ስ 1. ድልድይን ወይም ንጣፍን ለመስራትና ለመደልደል የሚያገለግል እንጨት፥ ብረት፥ ድንጋይ፥...፤መረባርብ:: 2. እንጨት ወይም ብረት በመደርደር የተሰራ::

**ርብራብ አልጋ** ስ በአግድም የተደረደረ የእንጨት ንጣፍ ወይም ርብራብ ያለው አልጋ::

**ርብርብ** ስ አንድን ነገር ፍፃሜ ላይ ለማድረስ የሚደረግ የጋራ ጥረት፤ የጋራ እርምጃ፥ ትግል::

**ተረበረበ** ግ 1. ተደለደለ፥ ተስተካከለ:: 2. በውሃ ተርከፈከፈ፥ ተረጨ::

**ተረባረበ** ግ 1. ተጋገዘ፥ ተረዳዳ፥ ሃይሉን አስተባበረ:: 2. ተሻማ:: *ልብሱን ለመግዛት ሰው ሁሉ ተረባረበ::*

**አረበረበ** ግ 1. ውሃን ረጩ፥ አርከፈከፈ። 2. ንግግር አበዛ፥ ለፈለፈ። 3. (ዘይ.) ሽርጉድ አበዛ፥ አዘጠዘጠ።

**አረብራቢ** ቅ ለፍላፊ፤ አለሁ አለሁ ባይ።

**ረበሸ** ግ 1. በጠበጠ፥ አወከ፥ አስቸገረ፥ ጠብ አነሳ። 2. ሰላም ነሳ፥ እረፍት ነሳ።

**ረባሽ** ቅ በጥባጭ፥ አዋኪ።

**ረብሻ** ስ ሁከት፥ ጠብ፥ ትርምስ፥ ብጥብጥ፥ ግርግር።

**ረብሸኛ** ቅ 1. በጥባጭ፥ አዋኪ። 2. ተደባዳቢ፥ ጠብ ወዳድ።

**ተረበሸ** ግ 1. ተበጠበጠ፥ ግርግር ተፈጠረ። 2. ተጨነቀ፥ ተጠበበ፥ መንፈሱ ታወከ።

**ተረባበሸ** ግ ተተረማመሰ፥ ምስቅልቅሉ ወጣ።

**ተራበሸ** ግ ተበጣበጠ፥ ተጣላ።

**አራበሸ** ግ አጣላ፥ አጋጨ።

**ረበበ** ግ 1. ሰፈፈ፥ ተንሣፈፈ፥ አንሣፈፈ (በአየር ላይ)። 2. አጠላ፥ ጋረደ፥ ድባብን ዘረጋ። 3. አደረ፥ መላ፥ ሰፈነ። *መንፈስ ቅዱስ ረበበት።*

***ረበተበተ**

**[እ]ርብትብት** ቅ 1. ፈሪ፥ ድንጉጥ። 2. ሽቁጥቁጥ። *እገሌ ለጓደኞቹ እርብትብት ነው።*

**[እ]ርብትብት አለ** ግ ተርበተበተ።

**ተርበተበተ** ግ ፈራ፥ ደነገጠ፥ ተንቀጠቀጠ፥ ራደ።

**አርበተበተ** ግ አንቀጠቀጠ፥ አርበደበደ።

***ረበየ**

**ተረባየ** ግ 1. ተረገጠ፥ ተረመረመ። 2. ተበራየ፥ ተወቃ፥ ተሄደ (የእህል ነዶ)።

**አረባየ** ግ 1.ረገጠ፥ ረመረመ፥ ጠቀጠቀ። 2. አበራየ፥ ወቃ፥ አሄደ።

***ረበደበደ**

**[እ]ርብድብድ** ቅ ፈሪ፥ ድንጉጥ፥ እርብትብት።

**[እ]ርብድብድ አለ** ግ ተርበደበደ።

**ተርበደበደ** ግ ተንቀጠቀጠ፥ ራደ፥ ፈራ፥ ተርበተበተ።

**አርበደበደ** ግ አስፈራ፥ አስጨነቀ፥ አንቀጠቀጠ፥ አርበተበተ።

**ረቡእ (ሮብ)** ስ በማክሰኞና በሃሙስ መካከል ያለው ቀን ስም፤ ከእሁድ ጀምሮ ሲቆጠር የሳምንቱ አራተኛ ቀን።

**ረባ** ግ 1. በመውለድ፥ በመዋለድ በዛ፥ በረከተ ተጨመረ። 2. ጠቀመ፥ ፈየደ። *ላሀያ ሰባ ምን ረባ።* 3. (ሰዋ.) ግሱ ወይም አንድ ግሳዊ ቃል በጊዜ፥ በፆታ፥ በመደብ ተተነተነ፥ ተዘረዘረ።

**አይረባም** ጥራት፥ ጥንካሬ፥ ረዥም አገልግሎት የለውም። *የገዛው ሰላት አይረባም።*

**ረብ** ስ ጥቅም፥ ፋይዳ።

**ርቢ** ስ 1. እርባታ፥ ማራባት፥ ማዋለድ፥ ማብዛት። *ከብት ርቢ።* 2. የቤት እንስሳትን ከሌላ ሰው በውለታ ወስዶ በመቀለብና በማዋለድ የሚገኙትን ውልዶች ከእንስሳቱ ባለቤት ጋር እኩል የመካፈል ልምድና ተግባር።

**[እ]ርባታ** ስ 1. ከብትን የማርባት ስራ። 2. ግስን ወይም አንድን ግሳዊ ቃል በተለያዩ ቅርፆች መተንተን ወይም ማርባት።

**[እ]ርባና ([እ]ርባን)** ስ ረብ፥ ጥቅም፥ ፋይዳ።

**[እ]ርባና ቢስ** ጥቅመቢስ፥ ዋጋ የለሽ፥ የማይረባ።

**ተራባ** ግ 1. እየተዋለደ በዛ፥ ተባዛ። 2. ተስፋፋ፥ ተስራጨ። 3. (ሰዋ.) በእርባታ ዘዴ ከአንድ ስርወ ቃል ላይ እንደስም፥ ቅፅል፥... ያሉ ውልድ ቃላት ተፈጠሩ።

**አረባ** ግ 1. ከብትን፥ ዶሮን፥... እየቀለበ በማኖር፥ በማዳቀል፥ በማዋለድ አባዛ። 2. (ሰዋ.) በእርባታ ዘዴ ተጠቅሞ ከአንድ ስርወ ቃል ላይ እንደስም፥ ቅፅል፥... ያሉ ውልድ ቃላትን ፈጠረ።

**-አርቢ** (ከብትን፥ ዶሮን፥...) እየቀለበ፥ እያዳቀለ፥ እያዋለደ የማስፋፋት፥ የማባዛት ስራ የሚሰራ (ሰው)።

**አራባ** ግ 1. እያዋለደ አበዛ። 2. አስፋፋ፥ አስራጨ፥ አዛመተ። *ወሬውን አራባ።* 3. አባዛ። *ፎቶግራፉን አራባ።*

**ረባሽ** "ረበሸ"ስር ተመ.

**ረባዳ** ቅ ጎድጓዳ፥ ዘባጣ (መሬት)።

***ረብ**

**[እ]ረብ አለ** ግ ወደቀ፥ ዘፍ አለ፥ እንዘጭ አለ።

**ረብ** "ረባ" ስር ተመ.

**ረብሸኛ** "ረበሸ" ስር ተመ.

**ረብሻ** ዝ.ከ.

**ረብጣ** ስ ጥቅል፥ እስር (የገንዘብ፥ የወርቅ)።

**ረታ** ግ 1. አሸነፈ፥ ድል ነሳ (በሙግት፥ በክርክር፥ በጦርነት፥...)። 2. ሰላ፥ ተባ፥ ቀና፥ ስለት አወጣ። 3. ተፍታታ፥ ተቃና ተዘረጋ። 4. አንደበቱ ተፍታቶ በጥሩ ሁኔታ ተናገረ።

**ተረታ** ግ 1. ተሸነፈ፥ ድል ሆነ (በሙግት፥ በክርክር፥...)። 2. ስሜቱ ተሳበ፥ ተመሰጠ ተማረከ። *በፍቅሯ ተረታ።*

**ተረታታ** ግ ተፍታታ፥ ተዘረጋጋ::

**ረከረከ** ግ 1. ዝናብ በጣም ጣለ፥ አጨቀየ:: *ዝናቡ ሲረከርከው አደረ::* 2. በርከርክ የዜማ ስልት አዜመ:: 3. ፅሁፍን አጨማልቆ፥ በጫጭሮ ፃፈ::

**ርክርክ** ስ ከያሬዳዊ የዜማ ስልቶች ወይም ምልክቶች አንዱ::

**ረከሰ** ግ 1. ዋጋው ዝቅ አለ፥ ወረደ:: 2. በመጥፎ ስራ ወይም በሃጢአት ላይ ተገኘ:: 3. ንፁህነቱን፥ ክብሩን አጣ:: 4. ሃይሉ ጠነገፈ፥ ተበላሸ (አስማት፥ መድሃኒት፥...):: 5. ከመብዛቱ ወይም ፈላጊ ከማጣቱ የተነሳ ዋጋ አጣ፥ ወደቀ::

**ረኪስ** ቅ ዋጋው ያልተወደደ፤ ርካሽ::

**ርካሽ** ቅ 1. ዋጋው ቀላል፥ ዝቅተኛ የሆነ:: 2. በአይነቱና በደረጃው ተራ፥ መናኛ፥ዝቅተኛ የሆነ:: 3. ከብቶች ሲበሉ ያዝረከረኩት የድርቆሽ ወይም የገለባ ትርፍራፊ::

**[እ] ርኩስ** ቅ ንፁህ፥ ቅዱስ ያልሆነ፥ ነውረኛ፥ በሃጢአት ያደፈ:: 2. አስፀያፊ፥ እንደነውር የሚታይ፤ ሊቀመስ፥ ሊበላ የማይችል:: 3. ክፉ፥ የተጠላ፥ ቅን የማያስብ::

**[እ] ርኩስ መንፈስ** ስ ሰይጣን፥ አጋንንት::

**አረከሰ** ግ 1. ዋጋን ሰበረ:: 2. መጥፎ ስም ሰጠ፥ አንቋሸሸ:: 3. የመድሃኒትን ሃይል ቀነሰ::4. ሃጢአት አሰራ፤ አጎደፈ፤ በከለ::

**ማርከሻ** ስ መድሃኒት ከተወሰደ በሁላ ሰውነት የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ የመድሃኒቱን ሃይል ለመቀነስ ወይም መርዝነቱን ለማፍረስ የሚወሰድ መድሃኒት::

**አራከሰ** ግ 1. ዋጋ ሰበረ፥ ዋጋ አጣጣ:: 2. አጥላላ፥ አንቋሸሸ::

***ረከበ**[1]

**ሩካቤ [ስጋ]** ስ ፍትወተ ስጋ፥ የወንድና የሴት የግብረስጋ ግንኙነት::

**ተራክቦ** ስ 1. የወንድና የሴት በግብረ ስጋ መገናኘት:: 2. ግንኙነት::

***ረከበ**[2]

**ርክክብ** ስ የመቀበልና የመስጠት ክንውን::

**ተረከበ** ግ ተቀበለ፥ ወሰደ፥ በእጅ አደረገ::

**ተረካቢ** ስ በአስረካቢ እጅ የነበረን እቃ ወይም ስራ የሚቀበል ወገን፥ ተቀባይ ክፍል::

**ተረካከበ** ግ ተረካቢ ከአስረካቢ ተቀበለ፥ ወሰደ (እቃን፥ ስራን፥...)::


**አረካከበ** ግ በተረካቢና በአስረካቢ መካከል የሚካሄደውን የርክክብ ስራ መራ፤ እንደታዛቢ ወይም እንደ ምስክር ሆኖ ተመለከተ::

**አረካካቢ** ስ የርክክብን ስራ ወይም ክንውን የሚቆጣጠር፥ በምስክርነት የሚመለከት ግለሰብ ወይም አካል::

**አስረከበ** ግ በይዞታ የነበረውን እቃ ወይም ንብረት፥... ለተረካቢው ወገን ሰጠ::

**አስረካቢ** ስ በይዞታው ስር የነበረውን እቃ፥ ንብረት፥... ለተረካቢ የሚሰጥ፥ የሚያስተላልፍ ግለሰብ ወይም ድርጅት::

**ረከቦት** ስ ከእንጨት፥ ከብረት፥... የተሰራና ቡና በሚቀዳበት ጊዜ ስኒ የሚደረደርበት እቃ::



ረከቦት

***ረከፈከፈ**

**[እ] ርክፍካፌ** ስ ካፊያ:: *በሃምሌ ወጨፎ በሰኔ ርክፍካፌ::*

**ተርከፈከፈ** ግ 1. ተረጨ:: 2. ተጎዘጎዘ፥ ተረበረበ:: 3• ጥቂት ጥቂት ተዳረሰ፥ ትንሽ ትንሽ ተሰጠ::

**አርከፈከፈ** ግ 1. ረጨ:: 2. አካፋ፥ አንጠባጠበ:: 3. ጥቂት ጥቂት አዳረሰ:: 4. ረበረበ፥ ጎዘጎዘ::

**ረኪስ "ረከሰ"** ስር ተመ.

**ረካ** ግ 1. ጠጥቶ ጠገበ፤ ጥሙን ቆረጠ:: 2. የልቡ ደረሰ፤ የሚፈልገውን በማግኘቱ ተደሰተ::

**[እ]ርካታ** ስ የፈለጉትን በአጥጋቢ ሁኔታ በማግኘት፥ በማድረግ፥... የሚገኝ ደስታ::

**አረካ** ግ 1. አጠገበ:: 2. የልብ አደረሰ፥ አስደሰተ::

**አርኪ** ቅ አጥጋቢ፥ የልብ የሚያደርስ::

***ረኮተ**

**ርኩቻ** ስ የአካል ወይም የአስተሳሰብ ግጭት፥ ፍትጊያ፤ ጥል::

**ተራኮተ** ግ 1. ተጣላ፥ ተማታ፥ ተደባደበ:: 2. ተሻማ፥ ተናነቀ፤ አንድን ነገር ለማግኘት፥ ለመውሰድ ተጋፋ:: 3. ተሟገተ፥ ተከራከረ፥ ተጠቃጠቀ::

**አራኮተ** ግ 1. አጣላ፥ አማታ፥ እርስ በርስ አደባደበ:: 2. አሻማ::

***ረወጠ**

**ተራወጠ** ግ ተሯሯጠ፥ ወዲያ ወዲህ ሄደ፥ ኳተነ::

**አራወጠ** ግ 1. አባረረ፥ አሯሯጠ። 2. አለፋ፥ አዋከበ፥ ወዲያ ወዲህ አጣደፈ።

**ረዘመ** ግ ተመዘዘ፥ አደገ፥ በቁመት ከፍ አለ። 2. በለጠ። 3. በዛ፥ ከሚፈለገው ወይም ከልኩ በላይ ሆነ። 4. ተጓተተ፥ ተንዛዛ።*የስራ አስኪያጁ ንግግር ረዘመ።* 5. ብዙ ቆየ። *እድሜው ረዘመ።*

**ረኸም** "ረጅም"ን ተመ.

**ረጅም(ረኸም)** ቅ 1. ቁመቱ ትልቅ የሆነ፥ ዘለግ ያለ። 2. የተንዛዛ። 3. ብዙ የሚቆይ (የቆየ)። *የእቃው አገልግሎት ረኸም ነው።*

**ለረጅም ጊዜ** ለብዙ ጊዜ።

**በረጅሙ ተጣራ** ጮክ ብሎ፥ ድምፁን ዘለግ አድርጎ ጠራ።

**በረጅም ጊዜ የሚከፈል** ቀስ በቀስ፥ ጊዜ ወስዶ የሚከፈል።

**ከረጅሙ በአጭሩ** አንድን ሃሳብ ከብዙ በጥቂቱ ለማቅረብ ሲፈለግ በማያያዣነት ወይም በመንደርደሪያነት የሚያገለግል ሃረግ። *ከረጅሙ ባጭሩ ሁኔታውን እንደሚከተለው አቀርባለሁ።*

**ረጅሜ** ስ ረዘም ያለው የዶሮ ቅልጥም(ስእሉን የዶሮ ብልት ስር ተመ.)።

**ረጅም ልቦለድ** ስ (ስነ.ፅ.) በርከት ያሉ ገፀባህርያትና ውስብስብ ታሪኮችን በአንድነት አስተሳስሮ ይዞ የሚጓዝና የፈጠራ ስራ የሆነ፥ በስድ ንባብ የተቀነባበረ የስነ ፅሁፍ ዘርፍ።

**ርዝመት** ስ 1. በቁመት ትልቅ መሆን። 2. የቁመት ወይም የርቀት መጠን።

**ርዝመት አለው** በቁመቱ ትልቅ፥ ረጅም ነው።

**ርዝማኔ** ስ የቁመት መጠን።

**ተራዘመ** ግ 1.ለሌላ ጊዜ ተላለፈ (ለምሳሌ ቀጠሮው)። 2. ኮንትራቱ፥ የስራ ውሉ፥... ቀጠለ፥ የጊዜ ወሰኑ ጨመረ። 3. የጊዜ መጠኑ ወይም ቆይታው ጨመረ፥ ከፍ አለ።

**አረዘመ** ግ 1. ከፍ አደረገ (በቁመት)። 2. አጓተተ፥ አንዛዛ (ነገርን)። 3. ብዙ ጊዜ ወይም ዘመን አቆየ። *እድሜውን አረዘመ።*

**አራዘመ** ግ 1. ለሌላ ጊዜ አስተላለፈ። 2. (የውልን፥ የኮንትራትን፥...) የቆይታ ጊዜ ጨመረ። 3. የጊዜ መጠኑን ወይም ቆይታውን ጨመረ፥ ከፍ አደረገ።

**አስረዘመ** ግ 1. (በቁመት) ከፍ አደረገ። 2. አጓተተ፥ አንዛዛ (ነገርን)። 3. አረዘመ (እድሜን)።

**ረዳ** ግ 1. በገንዘብ፥ በቁሳቁስ፥ በስራ፥ በጉልበት፥ በሃሳብ፥... አገዘ። 2. በመድሃኒትነት፥ በመፍትሄ ሰጭነት፥... አገለገለ። *መድሃኒቱ ለራስ ምታት ይረዳል።*

**ርዳ ተራዳ** ተጋገዘ፥ ተደጋገፈ፥ ተባበር።

**ረዳት** ስ 1. አንድን ሰው በተለያዩ መንገዶች የሚያግዝ፥ የሚረዳ ሰው፥ አጋር፥ ደጋፊ። 2. በትላልቅ ወይም በንግድ መኪናዎች ላይ ለመኪናው ውሃ፥ ናፍታ፥ ዘይት የመሙላቱን፥ ሸራ የማልበሱን፥... ስራ የሚሰራ ሰው። ቅ 3. የበላይ ሃላፊውን በስራ የሚያግዝ ወይም የሚረዳ።

**ረድ (ረድእ)** ስ በገዳም ውስጥ አቅመ ደካማ መነኮሳትን የሚያገለግል ሰው።

**ረድኤት (ረዴት)** ስ 1. በረከት። 2. እርዳታ።

**አርድእት** በፊደል ተራው ተመ.

**[እ]ርዳታ** ስ የገንዘብ፥ የቁሳቁስ፥ የጉልበት፥ የሃሳብ፥... እገዛ፥ ድጋፍ።

**የ[እ]ርዳታ ድርጅት** ስ እርዳታን የሚሰጥ ወይም የሚለግስ በጎ አድራጊ ድርጅት።

**ተረዳ** ግ እርዳታ አገኘ፥ ተሰጠው።

**ተረጂ** ስ በሌሎች እርዳታ የሚኖር ሰው። 2. ድጋፍ ወይም እርዳታ ተቀባይ።

**መረዳጃ** ቅ እርዳታን፥ ድጋፍን (ለአባላቱ) የሚሰጥ፥ የሚያስተባብር (ማህበር፥ ተቋም፥...)።

**መረዳጃ ማህበር** ስ እርዳታን፥ ድጋፍን (ለአባላቱ) የሚሰጥ ወይም የሚያስተባብር ማህበር፥ ተቋም።

**ተራዳ** ግ ረዳ፥ አገዘ።

**ተራድኦ** ስ የመረዳዳት ወይም እርዳታ የመስጠት ተግባር።

***ረዳ**

**መርዶ** ስ 1. የዘመዱን፥ የወዳጁን፥... መሞት እንዲሰማና እርሙን እንዲያወጣ ለሟች ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ የሚነገር የሞት ዜና። 2. አሳዛኝና አስደንጋጭ ዜና።

**ተረዳ** ግ 1. ተገነዘበ አወቀ። 2. የቅርብ ዘመዱን ወይም ወዳጁን ሞት ሰማ።

**መረጃ** ስ 1. ስለ አንድ ነገር የሚሰጥ ማብራሪያ ወይም መግለጫ። 2. የትምህርት፥ የስራ፥ የተሳትፎ፥... ማስረጃ ወይም የምስክር ወረቀት። 3. አንድ ነገር መሆን አለመሆኑን ወይም መደረግ አለመደረጉን የሚጠቁም፥ የሚያሳይ የፅሁፍ ወይም የቃል ማስረጃ። 4 የመንግስት የስለላ ድርጅት።

**አረዳ** ግ መርዶ ነገረ።

**አስረዳ** ግ ገለፀ፥ አብራራ፥ አወቀ፥ አስገነዘበ።

**ማስረጃ** ስ 1. ምስክር። 2. የአንድ ነገር ማረጋገጫ ሰነድ ወይም የምስክር ወረቀት።

**አስረጅ** ስ 1. በአንድ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ የሚሰጥ ሰው። 2. እንደምሳሌነት፥ እንደ ምስክርነት፥ እንደማብራሪያ የሚያገለግል ወይም

የሚቀርብ ነገር::

**ረዳት** " **ረዳ**" ስር ተመ.

**ረድ** ዝ.ከ.

**ረድኤት** ዝ.ከ.

**ረድፍ** ስ ሰዎች ወይም ሌሎች ነገሮች የተደረደሩበት፥ የተሰለፉበት መስመር::

**ረጅሜ** "**ረዘመ**" ስር ተመ.

**ረጅም** ዝ.ከ.

**ረገመ** ግ "እንዲህ ይድረስብህ"፥ "እንዲህ ያድርግህ"፥ "እንዲህ ሁን" እያለ አወገዘ፤ በሌላው ላይ አንዳች መጥፎ ወይም ክፉ ነገር እንዲደርስ ተመኘ።

**መርገም** ስ የወር አበባ (ብዙውን ጊዜ የመፅሃፍ ቅዱስ አጠቃቀም)::

**[እ]ርጉም** ቅ ከይሲ፥ ያልተባረከ፤ ክፉ::

**[እ]ርግማን** ስ በሌላው ላይ ክፉ ነገር እንዲደርስ ተብሎ የተነገረ መጥፎ ምኞት፥ ውግዘት::

**የተረገመ** ቅ መጥፎ፥ ክፉ (ሰው)::

**ተራገመ** ግ ረገመ::

***ረገረገ**

**ረግረግ** ስ ውስጡ ውሃ ያለበትና ሲረግጡት ስምጥ ስምጥ የሚል መሬት::

**የረግረግ ወፍ** ስ ሙሉ ለሙሉ ጥቁር ሆና ግንባሯ ነጭ የሆነ፥ በረግረግ ቦታዎች የምትኖር፥ ሴት ዶሮ የምትመስልና የምታክል ወፍ(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)::

**ተረገረገ** ግ ነጠር ነጠር እያለ የኩራት አካሄድ ሄደ::

**ተረገረገብኝ** ተገቢ ካልሆነ ንግግር ጋር የትእቢት፥ የንቀትና የቁጣ አካላዊ እንቅስቃሴ አሳየኝ፤ ተንቀነቀብኝ::

**አረገረገ** ግ ወደላይና ወደታች ተንቀሳቀሰ፤ ተወዛወዘ (ምቾት ለመስጠት ወይም ጥብቀት በማጣት ወይም በመበላሸት፥ ለምሳሌ የሽቦ አልጋ፥ የእንጨት ድልድይ፥...)::

**አረግራጊ** ቅ ምቾት ያለው፥ የሚያነጥር (አልጋ፥ መኪና፥...)::

**ረገበ** ግ 1. የተወጠረው፥ የጠበቀው ላላ ወይም ለቀቅ አለ:: *የአልጋው ሽቦ ረገበ*፡ 2. በረደ፥ ቀዘቀዘ (የጦርነት፥ የጠብ፥... ውጥረት)::

***ረገበ**

**[እ]ርግብግቢት** ስ በተለይ በህፃናት አናት ላይ ከፍ ዝቅ እያለ በትርታ አይነት ሲንቀሳቀስ የሚታይ ከግንባር ከፍ ብሎ የሚገኝ የሰውነት ክፍል::

**[እ]ርግብግብ** ቅ ርህሩህ፥ ጭካኔ የሌለው፥ ሽቁጥቁጥ::

**ተራገበ** ግ 1. በማራገቢያ አማካኝነት ነፋስ እንዲያገኘው ተደረገ:: *ካልተራገበ ከሰሉ አይቀጣጠልም*:: 2. (ዘይ.) ተሟሟቀ፥ ተናፈሰ፥ እንዲጋጋል ተደረገ (ጠቡ፥ ወሬው)::

**ተርገበገበ** ግ 1. ተወዛወዘ፥ ተውለበለበ:: 2. በማራገቢያ አማካኝነት ነፋስ እንዲያገኘው ተደረገ:: 3. ተንሰፈሰፈ፥ ራደ፥ ተንቀጠቀጠ:: 4. (ዘይ.) ተጨነቀ፥ ተሽቆጠቆጠ::

**አራገበ** ግ 1.ምልክት ለማሳየት አውለበለበ (ጨርቅን፥ መሃረብን፥...):: 2. በማራገቢያ ነፋስ ሰጠ:: 3. (ዘይ.) አባባሰ፥ አጋጋለ (ነገርን)::

**ማራገቢያ** ስ 1. እሳትን ለማቀጣጠል ወይም እብቅን ከፍሬ በንፋስ ግፊት አማካይነት ለመለየት፥... እንዲረዳ በስሱ የተዘጋጀ ስሌን፥ ቆዳ፤ ማርገብገቢያ:: 2. በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ ጥፋት ሲሰራ የመስመር ዳኛው ምልክት የሚሰጥበት ጨርቅ::

**አራጋቢ** ስ በእግር ኳስ ጨዋታ የዋናው ዳኛ ረዳት፤ የመስመር ዳኛ::

**አርገበገበ** ግ 1. አወዛወዘ፥ አውለበለበ:: 2. አንሰፈሰፈ፥ አንቀጠቀጠ:: 3. (ዘይ.) አሰጨነቀ፥ አሽቆጠቆጠ::

**ማርገብገቢያ** ስ አየር ወደ እሳት አቅጣጫ እንዲንቀሳቀስ የሚገፋና እሳትን ለማቀጣጠል፥ እንዲሁም ሞቃታማ አየርን ወዲያና ወዲህ በፍጥነት በማንቀሳቀስ የሙቀቱን ሃይል ለመቀነስ የሚረዳ ከሰሌን፥ ከሳር፥... የሚሰራ እቃ፤ ማራገቢያ::

**ረገዘ**

**[እ]ርጉዝ** ቅ የፀነሰች፥ ያረገዘች (ሴት)፤ ነፍሰጡር::

**እርግዝና** ስ ፅንስ መያዝ፥ ማርገዝ::

**ተረገዘ** ግ ተፀነሰ፥ በማህፀን ውስጥ ተቋጠረ (ሽሉ)::

**አረገዘ** ግ በውስጡ ያዘ፥ አዘለ:: *ደመናው ዝናብ አረገዘ /ሰውየው በልቡ ነገር አርግዟል*::

**አረገዘች** በማህፀኗ ሽል ቋጠረች፥ ፀነሰች::

**አስረገዘ** ግ እንድትፀንስ፥ እንድታረግዝ አደረገ (በግብረስጋ ግንኙነት)::

**ረገደ** ግ 1. ተንቀጠቀጠ፥ ተንዘፈዘፈ፥ ራደ:: *ከህመሙ የተነሳ ሰውነቱ ረገደ*:: 2. ዘለለ፥ ጨፈረ፤ መሬት እየደቃ አለቀሰ::

**ርግዶ (ረግዶ፥ ረገዳ)** ስ በለቅሶ ጊዜ ከሃዘን የተነሳ የሚደረግ ዝላይ፥ ጭፈራ::

**ተርገደገደ** ግ አቅም ከማጣት የተነሳ ተንገዳገደ::

**አረገደ** ግ 1. አቅም ከማጣት የተነሳ ተንቀጠቀጠ፥ ተብረከረከ:: 2. እየዘለለ፥ ደረት

እየመታ አለቀሰ:: 3. (ዘይ.) ተሽቆጠቆጠ፥ ተለማመጠ፥ ሽርጉድ አለ:: *ባለው ቅንጭብ ያረግዷል::*

**ማርገጃ** ስ ከቤተክርስቲያን ቅፅረ ግቢ ውጪ የሚገኝ የሟች ዘመድና ወዳጅ ደረት እየመቱና እየዘለሉ የሚያለቅሱበት ክልል ወይም ቦታ::

**አርጋጅ** ስ ደረት እየመታና እየዘለለ ለሞተ ዘመድና ወዳጅ የሚያለቅስ ሰው::

**አርገደገደ** ግ አንገዳገደ::

**አስረገደ** ግ አስፈራ፥ አሽቆጠቆጠ፥ አንቀጠቀጠ::

**ረገድ** ስ 1. አኳያ፥ በኩል:: *በትምህርት ረገድ ሃገራችን ከፍተኛ ጥረት ታደርጋለች::* 2. አቅም፥ መጠን:: *በተቻለ ረገድ ልረዳህ እሞክራለሁ::*

**ረገጠ** ግ 1. በእግር ደቀደቀ፥ ጠቀጠቀ፥ ረመረመ:: 2. መታ፥ ደበደበ፥ ቀጠቀጠ:: 3. እግሩን አሳረፈበት፥ በእግሩ ተጫነ፥ በላዩ ላይ ቆመ:: *እግሬን ረገጠኝ*:: 4. በእግር አሸ (ቆዳን፥ ስልቻን፥ ዝተትን፥...):: 5. (ለቤት መምረጊያ የሚሆን ጭቃን ከጭድ ጋር) አቦካ:: 6. ጨፈረ:: 7. ናቀ፥ ደፈረ፥ ጥሶ ሄደ (ስብሰባን፥ ማእድን):: 8. ከለለ (ድንበርን):: 9. ሰረረ፥ መታ (ፈረስ፥ አህያ)::

**ረግጦ ገዛ** በጭቆና አስተዳደረ::

**መርገጥ** ስ ወገልንና ሞፈርን የሚያያይዝ ጠፍር ወይም ገመድ (ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)::

**መርገጫ** ስ 1. በወረቀት ላይ ያረፈ ቀለምን ለማምጠጫ የሚያገለግል የፅህፈት መሳሪያ:: 2. ማህተምን ወይም የጣት አሻራን ለፊርማ ቀለም የሚያስነኩበት የቀለም መደብ::

**ረጋጭ** ስ ሰልፍ የሚማር ምልምል ወታደር::

**[እ]ርጋጭ** ቅ በከብቶች እግር እየተረገጠ የቆሸሸና መጥፎ ጣእም ያለው (ውሃ፥ ሳር፥...)::

**[እርግጫ** ስ 1. ዱካ፥ ኮቴ፥ ፈለግ:: 2. እግርን አንስቶ በመማታት የሚጫወቱት የልጆች ጨዋታ:: 3. ልፊያ:: 4. የወታደር የሰልፍ ትምህርት::

**ተራገጠ** ግ 1. በእርግጫ መታ፥ ተማታ:: 2. ተላፉ፥ ተዛለለ::

**ተራጋጭ** ቅ የመራገጥ አመል ያለበት(ብዙውን ጊዜ ለከብት)::

**ተረጋገጠ** ግ በእግር ተረመረመ::

**መረጋገጫ** ስ 1. መረማመጃ፥ መተላለፊያ መንገድ:: 2. መወጣጫ እርከን፥ ደረጃ::

**አስረገጠ** ግ አሸበሸበ:: *መዘምራኑ ለማስረገጥ ተዘጋጅተዋል::*

**አስረጋጭ** ስ አሸብሻቢ (ደብተራ፥ ካህን)::

***ረገጠ**

**[እ]ርግጥ** ቅ ትክክል፥ የማያጠራጥር፥ ሃቅ ወይም እውነት የሆነ::

**[እ]ርግጠኛ** ቅ 1. ትክክለኛ፥ የማያጠራጥር፥ እውነተኛ:: 2. ጥርጣሬ የሌለው፥ የሚተማመን፥ በትክክል የሚያውቅ:: *እቃው ይሄ ለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ::*

**ተረጋገጠ** ግ 1. ትክክል መሆኑ፥ እውነቱ፥ ወይም ሃቁ ታወቀ:: 2. እውን ሆነ፥ በተግባር ተተረጎመ::

**አረጋገጠ** ግ 1. እውነት መሆኑን አጣራ፥ አወቀ:: 2. እውነት ወይም ትክክል መሆኑን አሳወቀ፥ መሰከረ:: 3. እውን አደረገ፥ በተግባር ላይ አዋለ::

**አስረገጠ** ግ እውነት ወይም ትክክል መሆኑን፥ አጣራ፥ አወቀ:: *አስረግጠህ ተናገር::*

**ረገፈ** ግ 1. ከነበረበት ወደታች ወረደ፥ ወደቀ ፥ ተንጠባጠበ:: 2. ጠፋ፥ ጸነ (የኩፍኝ፥ የፈንጣጣ፥... ቁስል)::3. ወለቀ፥ ተነቀለ (ጥርስ):: 4. (ዘይ.) ሀ.አለቀ፥ ሞተ:: *ብዙ ሰው ረገፈ::* ለ.ጠፋ፥ በነነ:: *ወበቁ ረገፈ::*

**መርገፍ** ስ በድባብ፥ በጃንጥላ፥ በቤተክርስቲያን ጉልላት፥ በመሶበወርቅ ወይም በበቅሎ እቃ ላይ የሚደረግ ዘርፍ፥ አጫዋች ጌጥ::




**ርጋፊ** ቅ 1. የወደቀ፥ የተንጠባጠበ (ፍራፍሬ ወይም ሌላ ነገር):: 2. የመጨረሻ፥ እላቂ፥ ሙጣጭ (እህል፥ ዱቄት፥...):: 3.(ዘይ.) የተጣለ፥ የማይረባ፥ ይህ ነው የማይባል፥ ውዳቂ::

**ርጋፎ** ዝ.ከ.

**[እ]ርግፍ [እ]ርግፍ አለ** ግ 1. ፈሰሰ ፥ ዱብዱብ አለ (ለምሳሌ እንባ):: 2. ረገፈ::

**[እ]ርግፍ አደረገ** ግ 1. ፈፅሞ፥ ጨርሶ ተወ:: 2- ሙጥጥ አድርጎ ጨረሰ::

**ተራገፈ** ግ 1. ተወገደ (ቆሻሻ):: 2. ባዶ ሆነ፥ ተሟጠጠ:: 3. ወረደ (ጭነት ወይም ተሳፋሪ)::

**አራገፈ** ግ 1. አወለቀ፥ ነቀለ (ጥርስን):: 2. አወረደ (ጭነትን፥ ተሳፋሪን):: 3. አስወገደ

(ቆሻሻን)። 4. ጨረሰ፣ አሟጠጠ።

*ረገፈገፈ

**[እ]ርግፍግፍ አለ** ግ ተርገፈገፈ።

**ተርገፈገፈ** ግ ተንቀጠቀጠ፣ ተንዘፈዘፈ።

**አርገፈገፈ** ግ አንቀጠቀጠ፣ አንዘፈዘፈ፣ ነቀነቀ።

**ረጋ**

**ረጋ ሰራሽ** ቅ አዋቂ ወይም ባለሙያ ያልሰራው እቃ።

**ረጋ** ግ 1. ቆመ፣ ፀና። 2. ወፈረ፣ ተጋገረ፣ ለደለደ። 3. ፀጥ አለ፣ በረደ፣ ሰላም ሰፈነ።

**ይርጋ** ስ (ህግ) በፍርድ ቤት የሚነሱ ክርክሮች በህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንደሚገባቸውና ጉዳዮቹ በተቀረጠው የጊዜ ገደብ ካልቀረቡ በጉዳዮቹ ላይ ክስ ማቅረብ አለመቻሉን፣ ክሱም ቀሪ መሆኑን የሚያመለክት ሁኔታ።

**እርጋታ** ስ ዝግታ፣ ቀስታ፣ የሰከነ ሁኔታ።

**እርጎ** ስ የረጋ ወተት።

**ረጋ አለ** 1. አደብ ገዛ፣ መንቀዥቀዥ ተወ፣ ሰከነ፣ ጨመተ። 2. ጋብ፣ ቀዝቀዝ አለ።

**ተረጋጋ** ግ 1. ፀጥ አለ፣ በረደ (ሩብሻ፣ ሁከት)። 2. ተፅናና፣ ተበረታታ፣ የመንፈስ እረፍት አገኘ።

**አረጋ** ግ 1. አቆመ፣ አሳረፈ። 2. አፀና፣ አፀደቀ።

**አረጋጋ** ግ 1. ሁከትን አበረደ፣ ሰላም አሰፈነ። 2- አፅናና፣ አበረታታ፣ የአእምሮ እረፍት ሰጠ።

**ረጋጭ** "ረገጠ" ስር ተመ.

**ረግረግ** "*ረገረገ" ስር ተመ.

**ረግዶ** "ረገደ" ስር "ርግዶ" ን ተመ.

**ረጠበ**[1] ግ ራሰ፣ ረሰረሰ።

**[እ]ርጥብ** ቅ 1. የራሰ፣ የረሰረሰ። 2- ለምለም 3. ያልደረቀ። 4. (ዘይ.) ሞኝ፣ ያልበሰለ (ሰው)።

**[እ]ርጥብ ልጅ** ስ ያልጠና፣ ያልጠነከረ፣ አራስ ልጅ፣ ጨቅላ።

**[እ] ርጥብ ሬሳ** ስ ሞቶ ያልዋለና ያላደረ፣ ትኩስ ሬሳ።

**[እ] ርጥብ ስጋ** ስ ያልተጠበሰ ወይም ያልተቀቀለ፣ ትኩስ ጥሬ ስጋ።

**[እ] ርጥብ አራስ** ስ በቅርብ ቀን የወለደች ሴት።

**[እ] ርጥብ እማኝ** ስ በሸንጎ ላይ የሚነሳ አዲስ ተጨማሪ ምስክር።

**[እ] ርጥበት** ስ በፈሳሽ ነገር የመራስ ሁኔታ፣ በላዩ ወይም በውስጡ ያዘለው ፈሳሽ።

**አረጠበ** ግ 1. ውሃ ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገር አስነካ። 2. አራሰ፣ አረሰረሰ።

**አራጠበ** ግ ልትወልድ የደረሰች ሴት በምጥ ሰአት ላይ የእንሽርት ውሃዋ ፈሰሰ።

**ረጠበ**[2] ግ የተቸገረን ለመርዳት፣ የጠፋን ለመተካት የገንዘብ ወይም የእቃ ስጦታ አደረገ፣ እርዳታ ሰጠ።

**እርጥባን** ስ እርዳታ (የገንዘብ፣ የእቃ)።

**ተረጠበ** ግ እርጥባን ተሰጠው፣ ተቀበለ።

**ተረጣቢ** ቅ ገንዘብ ተረጂ።

**ረጠጠ** ግ አመቀ፣ ተጫነ (የሚሰፈር እህልን)።

**ርጭ** ስ አነባበሮ (ድልህ፣ ስሊጥ፣ ኑግ፣ ተልባ ያለበት)።

**[እ] ርጥጥ** ቅ 1. እምቅ። 2. (ዘይ.) ውዝፍ።

**ተረጠጠ** ግ 1. ታመቀ። 2. (ዘይ.) ስራ ፈትቶ፣ ተወዝፎ ተቀመጠ።

**አርጣጣ** ቅ 1. ሰነፍ፣ ውዝፍ፣ ከተቀመጠበት የማይነሳ (ሰው)። 2. ቁመተ ረዥም፣ በገፀ ስፊ የሆነች (ሴት)።

**ረጨ** ግ 1. ፈነጠቀ፣ አርከፈከፈ። 2. ነዛ፣ በተነ፣ ዘራ። 3. አስራጨ፣ አደረሰ። 4. (ዘይ.) አባከነ (ገንዘብን)።

**ተረጨ** ግ ተፈነጠቀ፣ ተርከፈከፈ (ለምሳሌ ውሃ፣ ጠበል)።

**ተራጨ** ግ ረጨ፣ ፈሳሽን ፈነጠቀ (ሌላ ሰው ላይ ወይም እርስ በራሱ)።

**ረጪት** ስ የቡሆ እቃ እጣቢ፣ ልቅላቂ።

**ረፈረፈ** ግ 1. ጣለ፣ ለሸለሸ፣ አስተኛ፣ አጋደመ። 2. (ዘይ.) በብዛት ገደለ፣ ጨፈጨፈ።

**ረፍረፎ** ስ ሹሩባ ያልተሰራ ወይም ያልተሞሸጠ የሴት ፀጉር፣ ጎፈሬነት ያለው።

**ተረፈረፈ** ግ ወደቀ፣ ተጋደመ፣ ተኛ (በእንቅልፍ፣ በበሽታ፣ በሞት፣...)።

***ረፈቀ**

**ምርፋቅ** ስ 1. በቤተክርስቲያን ጓሮ በቤተልሄም አጠገብ ካህናት ተረፈ መስዋእት ለመመገብ የሚቀመጡበት ስፍራ። 2. በገዳም የሚኖሩ መነኮሳት በህብረት የሚመገቡበት ቤት፣ የምግብ አዳራሽ፣ ቤተምርፋቅም ይባላል።

**አረፈቀ** ግ 1. አቅም አጣ፣ ደከመ፣ ተኛ፣ ወደቀ። 2. እቤት ዋለ፣ ደከመ (ሽማግሌ)።

**ረፈደ** ግ 1. ከንጋ ቆየ፣ ከጧትነት አለፈ፣ ረፋድ ሆነ። 2. ከሚፈለገው ወይም ከተወሰነው ሰአት በላይ አለፈ፣ ዘገየ።

**ረፋድ** ስ ጥዋት ከሰአት እስከ አምስት ሰአት

ድረስ ያለው ጊዜ።

**አረፈደ** ግ ዘገየ፥ ቆየ፥ የተወሰነውን ሰአት አሳለፈ።

**አርፋጃ** ስ ረፋድ።

**አርፋጅ** ቅ የተወሰነውን ሰአት አሳልፎ የሚመጣ፥ የሚዘገይ።


**ረፍረፎ** "ረፈረፈ" ስር ተመ.

**ሩ** የ"ረ" ፊደል ካእብ ዘር።

**ሩሀ** ስ ነፍስ።

**ሩሀሩሀ** "ራራ" ስር "ርሀሩሀ" ን ተመ.

**ሩሎ** ስ ለመንገድ ስራና ለመሬት መደመጫ (ማስተካከያ) የሚያገለግል ከባድ የሆነ ተንከባላይ የብረት አካል ያለው መኪና፣ ዳምጠው።



ሩሎ

**ሩር(እሩር)** ስ 1. ከእንጨት ቁራጭ የሚሰራ ድቡልቡል የገና መጫወቻ ኳስ። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) አጭር (ሰው)።

**ሩቅ** "ራቀ" ስር ተመ.

**ሩቤቶ** ስ የቧንቧ መክፈቻና መዝጊያ።

**ሩብ (እሩብ)** ቅ 1. ከአራት አንድ እጅ፣ አንድ አራተኛ። ስ 2. በቀድሞ ጊዜ የነበረ፥ በጊዜው የብር አንድ አራተኛ ዋጋ የነበረው ገንዘብ።

**ሩካቤ [ስጋ]** "ረከበ"ስር ተመ.

**ሩዝ** ስ በአብዛኛው ሞቃት በሆነው የእስያ አህጉር ውስጥ የሚበቅልና የአለም አንድ ሶስተኛው ህዝብ የሚመገበው የእህል አይነት።

**ሩጋ** ስ የአውሬ መያዣ ወጥመድ።

**ሩጫ** "ሮጠ" ስር ተመ.

**ሪ** የ "ረ" ፊደል ሳልስ ዘር።

**ሪህ** ስ በአካል መጋጠሚያዎች ላይ የሚሰማ የቁርጥማት በሽታ።

**ሪቅ** ስ ከእንጨትና ከጭቃ የሚሰራ፥ ከላይ ደረባ ያለው የእህል መክተቻ፣ ጎተራ።

**ሪኮርድ** ስ 1. ተመዝግቦ የሚገኝ መረጃ። 2. (ስፖ.) ተመዝግቦ የሚገኝ ከፍተኛ የውድድር ውጤት፥ ነጥብ።

**ሪኮርድ ሰበረ** ቀደም ሲል ተገኝቶ የነበረውን ከፍተኛውን የውድድር ውጤት አሻሻለ።

**ሪኮርድ አለበት** ካሁን በፊት የሰራውና ተመዝግቦ የሚገኝ የወንጀል ድርጊት መረጃ አለበት።

**ሪዝ** ስ 1. ጢም። 2.ፀጉሩን ተሸልቶ የማያውቅ የበግ ጠቦት። 3. ለመጀመሪያ ጊዜ የተሸለተና ለበርኖስ የሚሆን ለስላሳ የጠቦት በግ ፀጉር።

**ሪጋ** ስ 1. ተራ፡ ረድፍ። 2. በጨርቅ ወይም በሌላ ነገር ላይ በተደጋጋሚነት የተሰመረ መስመር። 3. የልስን ማስተካከያ ረዥም ባውላ፡ እንጨት።

**ሪፈረንደም** ስ ውሳኔ ህዝብ።

**ሪፐብሊክ** ስ ህዝብ በመረጠው መሪ የሚተዳደር መንግስት፣ ህዝባዊ መንግስት።

**ሪፖርተር** ስ 1. ሪፖርት የሚያዘጋጅና የሚያቀርብ ሰው። 2. ቃል አቀባይ፥ ዘጋቢ።

**ሪፖርት** ስ ስለ አንድ ነገር ወይም ሰው የሚሰጥ የፅሁፍ ማብራሪያ፥ መግለጫ፣ ዘገባ።

**ራ** የ"ረ" ፊደል ራብእ ዘር።

**ራሄሎ** ስ የዛር ስም (በባላገር እንደወረረሽኝ፥ ጉንፋን ያለ በሽታ በገባ ጊዜ፥ ራሄሎ ይዛልን ትሄዳለችና እንሸኛት በሚል እምነት ንፍሮ ቀቅለውና ራቅ ወዳለ ቦታ ወስደው መንገድ ላይ ይበትኑላታል)።

**ራመመ** ግ ፈገፈገ፥ አሸ፥ ዳመጠ፥ አለሰለሰ (ብራናን)።

**ራመድ አለ** "*ረመደ"ስር ተመ.

**ራማ** ስ (መፅ.ቅ.) ሰማይ።

**ራራ** ግ የሃዘኔታ፥ የደግነት፥ የመሳሳት ስሜት አሳየ።

**ራሮት** ስ ሃዘኔታ።

**ርሀሩሀ (ሩሀሩሀ)** ቅ አዛኝ፣ ጨካኝ ያልሆነ።


**ርሀራሄ** ስ ሃዘኔታ፣ ቸርነት፣ ደግነት።

**አራራ** ግ አዛኝ፥ ርሀሩሀ አደረገ፣ አሳዘነ፣ ልብ ነካ።

**ራሰ** ግ ረጠበ፥ ረሰረሰ።

**አራሰ** ግ 1. አረጠበ፥ አረሰረሰ፥ አበሰበሰ። 2. አረካ፥ አስደሰተ። *ላንጀቱን አራሰው።*

**ራስ** ስ 1. የሰውና የእንስሳት ሰውነት የላይኛው ክፍል፡ ጭንቅላት፣ አናት፣ አንጎልን የያዘው ክፍለ አካል። 2. የአንድ ነገር ጫፍ፡ ቁንጮ፥ አናት። 3. ከደጃዝማች በላይ ከንጉስ በታች የሆነ የቀድሞ ጊዜ የማእረግ ስም። 4. የግለሰብ እኔነት ወይም አንድን ሰው በአፅንኦት ለመጥቀስ ሲፈለግ የሚያገለግል ተውላጠ ስም። *ነገሩን እኔ ራሴ አይቸዋለሁ /አንተ ራስህን ጠብቅ/ ራሳችን ባመጣነው ጣጣ ሌላውን ልንወቅስ አይገባም።*




ራስ

**ራሱ ዞረ** 1. ተናደደ፥ ተበሳጨ:: 2. ግራ ገባው፥ ተምታታበት፥ ተደናገረ::

**ራሱ ጠና** በረታ፥ ሰውነቱ ጠነከረ (ህፃን)::

**ራሱን ሳተ** ከድካም፥ ከስካር፥ ከበሽታ፥... የተነሳ ዛለ፥ አቅም አጣ፥ ደከመ፤ ራሱን መቆጣጠር አቃተው::

**ራሱን ተሳመ** እንደዚህ እንደዚህ ያለ ስራ አለብኝና ሰው አስተባብረህ ስራውን እንድትረዳኝ ተብሎ ተጠየቀ፥ ልመና ቀረበለት::

**ራስ ስሞሽ** ስ ሰው አስተባብረህ በተሰወነ ቀን ስራ እንድታግዘኝ የሚል ጥብቅ ልመና፥ ጥያቄ::

**ራሱን ቻለ** ግ 1. ራሱን በራሱ ማስተዳደር ወይም መርዳት ጀመረ፤ ተቋቋመ:: 2. የሌላ እርዳታ ከመሻት ዳነ፤ በረታ፤ ጠነከረ::

**ራሱን ነቀነቀ** ራሱን በማንቀሳቀስ የዛቻ፥ የማስጠንቀቂያ፥ የእሽታ፥ የእምቢታ፥ የትዝብት፥... ምልክት ሰጠ::

**ራሱን አራቀ** ተገለለ፥ ብቻውን ሆነ፥ ራሱን ለየ፥ ሸሸ::

**ራሱን አሸነፈ** የማንንም እርዳታ ሳይሻ ኑሮውን መምራት ቻለ::

**ራሱን አወቀ** 1. በረታ፥ አቅም አገኘ፥ ራሱን መቆጣጠር ቻለ:: 2. ማስተዋል፥ ማመዛዘን ቻለ:: 3. ማንነቱን ተረዳ፤ አወቀ::

**ራሱን አወጣ** 1. ከመጥፎ ነገር ራሱን አዳነ:: 2. ተጣጥሮ በኑሮው ደህና ቦታ ደረሰ::

**ራሱን አዋረደ** 1. በመጥፎ ድርጊት ላይ ተገኘ:: 2. ታዛዥ ሆነ (ከብሩን በፈቃዱ ዝቅ በማድረግ)::

**ራሱን ገታ** አንድን ነገር ከማድረግ ተቆጠበ::

**ራሱን ጠበቀ** ጤንነቱን ተንከባከበ፤ ራሱን ከአደጋ ወይም ከመጥፎ ነገር አገለለ::

**ራሱን ጣለ** በኑሮው፥ በአለባበሱ ግዴለሽ፥ ደንታ ቢስ ሆነ::

**ራስ ላይ ወጣ** 1. አሰከረ፥ ናላ አዞረ፤ አሳመመ (መጠጥ):: 2. ተንጠባረረ፤ ተንቀባረረ፤ ናቀ፥ ተዳፈረ:: 3. በነገር ጠመደ::

**ራስ በራስ** አናት ባናት፥ ላይ በላይ፥ በተከታታይ:: *ራስ በራስ ልጅ ወልዳ ተቸገረች*::

**ራስ በራ** ቅ በእድሜ ወይም በዘር ምክንያት፥ በከፊል በራሱ ላይ ፀጉር የሌለው::

**ራስ ቡሃ** ቅ በራሱ ላይ ነጭ እከክ ወይም ቆረቆር ያለበት (ሰው)::

**ራስ ከፍት** ቅ ብልሀ፥ ነገር ቶሎ የሚገባው::

**ራስ ዘናና** ቅ ራስ ትልቅ፥ ጭንቅላታም::

**ራስ መጠበቂያ** ስ 1. ጠበንጃ፥ ጩቤ፥ ዱላ የመሳሰለውና ራስን ከወንበዴ ወይም ከአደጋ መከላከያ መሳሪያ:: 2. ለክፉ ጊዜ የሚያስቀምጡት ገንዘብ::

**ራስ ማሰሪያ** ስ ሻሽ::

**ራስ ምላስ** ስ የተቀቀለ የበግ ጭንቅላት ከነምላሱ::

**ራስ ምታት** ስ የራስ ህመም በሽታ::

**ራስ ሰሪ** ስ ፀጉር የምትሰራ ሴት፤ ቆናኝ::

**ራስ ቁር** ስ የጥንት ጦረኛ ከራሱ ላይ የሚያደርገው የራስ መከላከያ ቆብ::

**ራስ ክምር** ስ ራሱ ክብና ጠፍጣፋ የሆነ የእፅዋት አይነት፤ የፈረስ ዘንግም ይባላል::

**ራስ ወርቅ** ስ በጥንት ጊዜ የራስነት ማእረግ የተሰጠው ሰው ራሱ ላይ ያደርገው የነበረ ከወርቅ የተሰራ የራስ ቁር አይነት ቆብ፤ አክሊል::

**ራስ ወዳድ** ቅ ለራሱ እንጂ ለሌሎች የማያስብ፤ ይሉኝታ ቢስ::

**ራስጌ** ስ በመኝታ ጊዜ ራስ ወይም ጭንቅላት የሚውልበት ወይም የሚያርፍበት በታ፥ አቅጣጫ፤ ትራስጌም ይባላል::

**የራስ** የግል::

**እየራሱ** እያንዳንዱ::

**[የ]ራስ ቅል** ስ አንጎልን አቅፎና ሸፍኖ የያዘው የራስ አጥንት::

**የራስ ቅማል** ስ በራስ ጠጉር ውስጥ የሚገኝ ወይም የሚፈጠር ጥቁር ቅማል::

**ራሽን** ስ 1. በጦርነት፥ በድርቅ፥... አደጋዎች ጊዜ ለእያንዳንዱ ሰው ለተወሰነ ጊዜ እንዲያገለግል የሚታደል ምግብና መጠን የመሳሰለ የፍጆታ እቃ:: 2. ለወታደሮች፥ ለተማሪዎች፥... ለተወሰነ ጊዜ እንዲያገለግል የሚታደል የምግብ፥ የመጠጥ አቅርቦት፤ ቀለብ::

**ራሽን ካርድ** ስ በራሽን መልክ የሚሰጡ ነገሮች የሚመዘገቡበት ካርድ፤ የመሸመቻ ካርድም ይባላል::

**ራቀ** ግ 1. ቅርብ ሳይሆን ቀረ፥ በቀላሉ የማይደረስበት፥ ሩቅ ሆነ:: 2. ረዘመ፥ የሚዘገይ ሆነ (የጊዜ):: 3. ተለየ:: *ልጁ ከዘመድ ራቀ*:: 4.

ተው፡ ተገለለ:: *ከመጠጥ ራቀ::* 5. በተወሰነ የቦታ ርቀት ወይም ርዝመት ላይ ሆነ፥ ተገኘ:: *ፅህፈት ቤቱ ከዚህ ላምስት መቶ ሜትር ይርቃል::*

**ራቀው** ሸሸው፥ አጣ:: *ገንዘብ ራቀው /ሰላም ራቀው::*

**ሩቅ** ቅ ቅርብ ያልሆነ::

**ሩቅ ምስራቅ** ስ የምእራብ እስያ፡ ቻይና፡ ጃፓንና በአጠገቡ ያሉት ደሴቶች ጭምር አጠቃላይ መጠሪያ::

**ሩቅ ውዱቅ** ቅ ከፈጣሪ የራቀ፡ እንጦርጦስ የወደቀ (ዲያብሎስ)::

**[የ]ሩቅ ዘመድ** ስ ራቅ ያለ የደም ግንኙነት ወይም ዝምድና ያለው ሰው::

**ርቀት** ስ 1. ሩቅነት፥ ቅርብ ያለመሆን:: 2. ከአንድ ቦታ እስከ ሌላው ያለው የርዝመት ወይም የመራራቅ መጠን::

**ርቀት አለው** ቅርብ አይደለም፥ ሩቅ ነው::

**ተራራቀ** ግ 1. ሩቅ ለሩቅ ሆነ፥ ቅርበት አጣ:: 2. ተለያየ፥ ተነጣጠለ:: 3. ከመቀያየም የተነሳ የማይፈላለግ ሆነ::

**አራቀ** ግ 1. ሩቅ አደረገ:: 2. ነጠለ፡ ለየ:: 3. አገለለ::

**አርቆ አሳቢ /ተመልካች** ቅ አስተዋይ፡ ለወደፊቱ ጭምር የሚያስብ::

**አራራቀ** ግ 1. ሩቅ ለሩቅ አደረገ:: 2. አለያየ፥ ነጣጠለ:: 3. አቀያየመ::

**አራርቆ ወለደ** አከታትሎ ሳይሆን እየቆየ፡ ጊዜ እየሰጠ ወለደ:: *አራርቆ መውለድ ለቤተሰብ ምጣኔ ይረዳል::*

***ራቆተ**

**ራቁት** ቅ 1. ልብስ ወይም ሽፋን የሌለው፥ እርቃን:: 2. ባዶ:: *ራቁት እንጀራ::*

**ራቁቱን አስቀረው** ሙልጭ አድርጎ ወሰደበት (ልብሱን፥ ንብረቱን)::

**ተራቆተ** ግ 1. መለመላውን ወይም ራቁቱን ሆነ:: 2. ባዶውን ሆነ:: 3. ታረዘ፡ ልብስ አጣ:: 4. (ዘይ.) አጣ፥ ደሀየ::

**አራቆተ** ግ 1. ልብስን፥ ንብረትን፡... ገፈፈ፥ መለመላ አስቀረ:: 2. ልብስ ነሳ፡ ከለከለ:: 3. ባዶ አስቀረ:: 4. (ዘይ.) አደሀየ::

**ራበ** ግ 1. ምግብ አሰኘ፥ አስፈለገ:: 2. ከመቸገር ወይም ለብዙ ጊዜ ምግብ ከማጣት የተነሳ የሚመጣ ስቃይ ያዘ፥ አጋጠመ::

**ረሃብ (ራብ)** ስ 1. የምግብ ማሰኘት፡ ማስፈለግ:: 2. ችጋር፥ የምግብ መታጣት:: 3. ከምግብ እጦት ወይም ማነስ የተነሳ የሚመጣና ብዙ ሰውን ለሞት የሚዳርግ ስቃይ ወይም ጠኔ::

**ረሃብ ለቀቀበት** በጣም ተራበ::

**ረሃብ ገባ** በድርቅ ወይም በሌላ ምክንያት የሚበላ እህል ታጣ::

**የረሃብ አለንጋ** ጠኔ፥ ሃይለኛ ረሃብ::

**የረሃብ አድማ** ስ ምግብ መብላት በማቆም የሚደረግ፡ የሚቀርብ፥ የሚገለፅ ተቃውሞ (ለሚቀርበው ጥያቄ ተጠያቂው አወንታዊ ምላሽ እንዲሰጥ ለመገፋፋት)::

**ተራበ** ግ የሚበላው አጣ፣ በረሃብ ተጠቃ::

**ራብእ** ስ እንደ "ሃ"፥ "ላ"፥ "ማ"፥... ያሉ በሳልስና በሃምስ መካከል የሚገኙ አራተኛዎቹ የፊደላት ዘሮች መጠሪያ ወይም የድምፅ ምልክት::

**ራት (እራት)** ስ ምሽት(ማታ) ላይ የሚበላ የእለት ምግብ::


**የራት ልብስ** ስ በእራት ግብዣ ላይ ብቻ የሚለበስ የወንድ ወይም የሴት የክት ልብስ::

**የራት ግብዣ** ስ ማታ ላይ የሚደረግ የመብልና የመጠጥ ድግስ::

**ራቻ** ስ መከር ከመድረሱ በፊት ቀደም ብሎ በመድረስ ለችግር የሚውል ሰብል::

**ራእይ** ስ በእንቅልፍ ወይም በተመስጦ ጊዜ የሚታይ ሀሊናዊ ትርኢት፥ ህልም::

**ራኬት** ስ የጠረጴዛ ኳስን፥ የሜዳ ቴኒስ ኳስን፥... መለጊያ ወይም መጫወቻ መሳሪያ::



ራኬት

**ራዎት** ስ ርኮት፥ ኮዳ፥ የውሃ መያዣ::

**ራዛ** ስ አንበጣ በል የሆነ ነጭ አሞራ::

**ራደ** ግ ፈራ፥ ተንቀጠቀጠ፥ ተብረከረከ፥ ተርበደበደ::

**ርደት** ስ መንቀጥቀጥ፥ መፍራት፥ መብረክረክ፡ መርበድበድ::


**አራደ** ግ አስፈራ፥ አንቀጠቀጠ፥ አብረከረከ::

**ራዲያተር** ስ የመኪና ሞተርን ግለት ለማቀዝቀዝ የሚረዳ ውሃ በውስጡ የሚይዝ የውሃ ጋን::

**ራዳር** ስ ተንቀሳቃሽ ነገሮች በተወሰነ የአየር ክልል ውስጥ መኖራቸውን ወይም መግባታቸውን የሚያሳይ መሳሪያ::

**ራድዮን** "ሬዲዮ"ን ተመ.

**ራጂ** ስ ክብ ነገርን፡ ጎማን ከመሃሉ የሚያያይዝ ቀጫጭን ሽቦ::



ራጂ

**ራጅ** በኤሌክትሪክ ሃይል በሚመነጭና ለአይን በማይታይ ሃይለኛ ጨረር አማካይነት የሚቀረፅ ውስጣዊ የሰውነት ክፍል ምስል፡ ኤክስሬይም ይባላል::

**ራጨት** "**ረጨ**"ስር ተመ.

**ራፖር** ስ ማመልከቻ::

**ሬ** የ"**ረ**" ፊደል ሃምስ ዘር::

**ሬሳ** ስ 1. ነፍስ የተለየው፡ የሞተ፡ በድን የሆነ አካል:: 2. (ዘይ.፡ስድብ) ሙትቻ፡ አቅመቢስ::

**[የ] ሬሳ ሳጥን** ስ የሞተ ሰው አስከሬን እንዲቀበርበት የተዘጋጀ ሳጥን::

**ሬስቶራንት** ስ እየተከፈለ የሚበላበት ምግብ ቤት::

**ሬብ** ስ የአይነ ምድር መውጫ::

**ሬባም** ቅ (ስድብ) ቁሻሻ፡ ዝርክርክ፡ ፈሪ::

**ሬት(እሬት)** ስ ጠፍጠፍ፡ ረዘምና ሾጠጥ ያለ ቅርፅ ያለውና ወፍራም ቅጠሉን ሲፈነክቱት ዘለግላጋ የሆነ መራራ ፈሳሽ የሚወጣው የእፅዋት አይነት::

**ሬት ሬት አለ** 1. መረረ:: 2. (ዘይ.) አስጠላ፡ በጣም ሰለቸ:: *ንግግሩ ሬት ሬት ሳለኝ::*

**ሬንሳ (እሬንሳ)** ስ በገጠር አካባቢ ለሃገረሰብ መድሃኒት የሚከፈል ገንዘብ::

**ሬንጅ** ስ ከነዳጅ ዘይት ድፍድፍ የሚገኝና ለአስፋልት ስራ የሚያገለግል ጥቁር መጣብቅ፡ ካትራሜ::

**ሬኮማንዴ** ስ 1. የአደራ ደብዳቤ:: 2. ህጋዊ ደብዳቤ የደረሰው ሰው ለመቀበሉ ማረጋገጫ የሚፈርምበት መዝገብ::

**ሬዲዮ(ራድዮ)** ስ ከአንድ የተወሰነ አካባቢ የሚተላለፈውን የድምፅ መልእክት እየጠለፈ በሚፈለገው ሁኔታ አጉልቶ የሚያሰማና በባትሪ ወይም በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰራ መሳሪያ::

**ሬድዮ አስተላለፈ** በሬዲዮ አማካኝነት መልእክትን ነገረ፡ ለሌላ እንዲደርስ አደረገ::

**ሬድዮ ከፈተ** በሬድዮ የሚተላለፈውን ፕሮግራም ለማዳመጥ እንዲቻል ተዘግቶ የነበረውን ሬድዮ፡ መክፈቻውን በመጠቀም እንዲሰራና ፕሮግራም እንዲያስተላልፍ አደረገ፡ አስጀመረ::

**ሬድዮ ዘጋ** ሬድዮኑን ዝም እንዲል፡ እንዲያቆም አደረገ::

**ሬድዮ ጣቢያ** ስ በሬድዮ አማካኝነት የሚተላለፉ መልእክቶች የሚሰራጩበት ስፍራ ወይም መስሪያ ቤት::

**ሬጅስትራር** ስ ፩ በአብዛኛው በዩኒቨርሲቲ፡ በፍርድ ቤት፡ በፖስፒታል፡... ህጋዊ መረጃዎች ወይም ሰነዶች የሚቀመጡበትና ምዝገባ ባለ ጊዜ ምዝገባ የሚደረግበት ቦታ:: 2• ከላይ በተጠቀሱት ቦታዎችና የስራ አይነቶች በሃላፊነት የሚሰራ ሹም::

**ር** የ"**ረ**" ፊደል ሳድስ ዘር::

**ርህሩህ** "**ራራ**" ስር ተመ.

**ርህራሄ** ዝ.ከ.

**ርሚጦ[ሽ]** "**ረመጠ**" ስር ተመ.

**ርምስምስ አለ** "***ረመሰመሰ**" ስር ተመ.

**ርምድ** "***ረመደ**" ስር ተመ.

**ርምጃ** ዝ.ከ.

**ርምጥምጥ** "**ረመጠ**" ስር ተመ.

**ርስት** ስ 1. ቤተዘመድ የሆነ እያረሰ የሚጠቀምበትና ለተወላጅ በውርስ የሚተላለፍ መሬት፡ አፅመ ርስትም ይባላል:: 2. የግል ወይም የራስ ይዞታ የሆነ ቦታ፡ መሬት::

**ርስተኛ** ስ በተወላጅነት ርስት አግኝቶ በመጠቀም ላይ ያለ ሰው፡ የርስት ባለቤት::

**ርስተ ጉልት** ስ በርስትነት ከንጉስ ይሰጥ የነበረ መሬት፡ ጉልት::

**ርቀት**[1] "**ራቀ**" ስር ተመ.

**ርቀት**[2] "**ረቀቀ**" ስር ተመ.

**ርቢ** "**ረባ**" ስር ተመ.

**ርባታ** ዝ.ከ.

**ርባና** ዝ.ከ.

**ርባን** ዝ.ከ.

**ርትእ** ስ ትክክለኝነት፡ ቀጥተኝነት:: *ፍትህና ርትእ::*

**ርቱእ** ቅ 1. ቀጥተኛ:: 2. ግልፅ የሆነ፡ የተብራራ::*ሳንደበቱ ርቱእ ነው::*

**ርቱእ ተሳቢ** ስ (ሰዋ.) በአረፍተ ነገር ውስጥ የተሻጋሪ ግሱ ድርጊት ተቀባይ የሆነው ቃል መጠሪያ (ለምሳሌ "ካሳ ብርቱካን በላ" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ " ብርቱካን" ርቱእ ተሳቢ ነው፡ ቀጥተኛ ተሳቢም ይባላል)::

**ኢርቱእ ተሳቢ** ስ (ሰዋ.) ቀጥተኛ ያልሆነ

ተሳቢ (ለምሳሌ "አባቴ ገንዘብ ላከልኝ" በሚለው ውስጥ "ለእኔ" የሚለውን የሚያመለክተው "-ልኝ " ኢርቱእ ተሳቢ ነው)::

**ርብራብ** "ረበረበ" ስር ተመ.

**ርብርብ** ዝ.ከ.

**ርብትብት** "*ረበተበተ" ስር ተመ.

**ርብትብት አለ** ዝ.ከ.

**ርብድብድ** "*ረበደበደ" ስር ተመ.

**ርእስ (አርእስት)** ስ 1. የአንድን ፅሁፍ ወይም መፅሃፍ ፍሬ ጉዳይ የሚያመለክት የፅሁፉ ወይም የመፅሃፉ መጠሪያ:: 2. አንድ ፅሁፍ፥ ውይይት፥...የሚያተኩርበት ጉዳይ ("አርእስት" የብዙ ቁጥር ቅርፅ ቢሆንም እንደነጠላ ቅርፅ ሆኖም ያገለግላል)::

**አርእስት** 1. ከመፅሃፍ ገፅ ላይ ከወደአናት በኩል የሚገኝ፥ ፅሁፍ ያልሰፈረበት ክፍት ቦታ፤ የህዳግ ተቃራኒ:: 2. የ"ርእስ"ን ፍቺ ተመ.

**ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት** ስ (ቤ.ክህ.)ከሊቃነ ጳጳሳት ከፍ ያለ ማእረግ ያለው ጳጳስ::

**ርእሰ መምህር** ስ የትምህርት ቤት ስራ መሪ፥ ሃላፊ፤ ዳይሬክተርም ይባላል::

**ርእሰ ብሄር** ስ የአንድ ሃገር ወይም መንግስት መሪ::

**ርእሰ አንቀፅ** ስ በአንድ ጋዜጣ ወይም መፅሄት ላይ በዝግጅት ክፍሉ ወይም በዋና አዘጋጁ የሚቀርብ በአብዛኛው የወቅቱን አቢይ ጉዳይ ወይም የመፅሄቱን ልዩ ትኩረት የሚመለከት ፅሁፍ::

**ርእሰ አውዳመት** ስ የዘመን መለወጫ በአል፤ እንቁጣጣሽ፤ መስከረም አንድ ቀን፥ የአዲስ አመት መጀመሪያ::

**ርእሰ ደብር** ስ (ቤ.ክህ.) ማእረጉ ከሊቀ ጠበብት በታች፥ ከቀኝ ጌታና ከግራ ጌታ በላይ የሆነ የመዘምራን አለቃ::

**ርኩስ** "ረከሰ" ስር ተመ.

**ርኩቻ** "*ረኮተ" ስር ተመ.

**ርካሽ** "ረከሰ" ስር ተመ.

**ርካብ (እርካብ)** ስ በፈረስና በበቅሎ ኮርቻ ግራና ቀኝ የሚንጠለጠል፥ ለመወጣጫ፥ እግር ለማሳረፊያ፥ ሚዛን ለመጠበቂያ የሚያገለግል የኮርቻ እቃ (ስእሉን ኮርቻ ስር ተመ.)::

**ርካታ** "ረካ" ስር ተመ.

**ርክርክ** "ረከረከ" ስር ተመ.

**ርክበ ካህናት** ስ ከትንሳኤ በሂላ በሃያ አምስተኛው ቀን፥ ሃዋርያት ኢየሱስን ያገኙበት እለት ነው ተብሎ የሚታወስ በአል::

**ርክክብ** "*ረከበ²" ስር ተመ.

**ርክፍክፍ** "*ረከፈከፈ" ስር ተመ.

**ርዝመት** "ረዘመ" ስር ተመ.

**ርዝማኔ** ዝ.ከ.

**ርዝራዥ** ስ ተርፎ የቀረ ነገር፤ ትራፊ፥ ቅሪት::

**ርደት** "ራደ" ስር ተመ.

**ርዳታ** "ረዳ" ስር ተመ.

**ርጉም** "ረገመ" ስር ተመ.

**ርጋታ** "ረጋ" ስር ተመ.

**ርጋጭ** "ረገጠ" ስር ተመ.

**ርጋፊ** "ረገፈ" ስር ተመ.

**ርጋፎ** ዝ.ከ.

**ርግማን** "ረገመ" ስር ተመ.

**ርግብ (እርግብ)** ስ 1. ብዙውን ጊዜ የሰላም ምልክት ተደርጋ የምትወሰድ ከአሞራ የምታንስ ከወፍ ከፍ የምትል የአእዋፍ አይነት::(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.) 2. (ዘይ.) የዋህ፤ ገር፤ ደግ፤ ተንኮል የሌለው::

**ርግብግቢት** "*ረገበ" ስር ተመ.

**ርግብግብ** ዝ.ከ.

**ርግዶ** "ረገደ" ስር ተመ.

**ርግጠኛ** "*ረገጠ" ስር ተመ.

**ርግጥ** ዝ.ከ.

**ርግጫ** "ረገጠ" ስር ተመ.

**ርግፍ ርግፍ አለ** "ረገፈ" ስር ተመ.

**ርግፍ አደረገ** ዝ.ከ.

**ርግፍግፍ አለ** ዝ.ከ.

**ርጥ** "ረጠጠ" ስር ተመ.

**ርጥበት** "ረጠበ" ስር ተመ.

**ርጥብ** ዝ.ከ.

**ርጥጥ** "ረጠጠ" ስር ተመ.

**ርጭ አለ** "እርጭ አለ" ን ተመ.

**ሮ** የ"ረ" ፊደል ሳብእ ዘር::

**ሮማን** ስ መጠኑ ብርቱካን የሚያክል፥ ውስጡ ቀያይና ትንንሽ የሆኑ ጠንካራ የዘር ፍሬዎች በብዛት ያሉትና ጣፋጭ የሆነ ፍሬ፤ ተክሉም ሮማን ይባላል።

**ሮሮ (እሮሮ)** ስ 1. ሃዘን፤ ዋይታ:: 2. ስሞታ፤ ብሶት::

**ሮስተር** ስ የተማሪዎች የትምህርት ውጤት የሚሰፍርበት መዝገብ::

**ሮቃ** ስ ፍሬውን ሲበሉት የሚኮመጥጥ የብርብራ አይነት ዛፍ፤ ሆመርም ይባላል፤ ፍሬውም ሮቃ (ሆመር) ይባላል::

**ሮቄ** ስ ማጥ፥ ረግረግ፥ አረንቋ።

**ሮብ** "ረቡእ"ን ተመ.

**ሮንዴላ** ስ የታሰረ ብሎን በንቅናቄ እንዳይፈታ አፍኖ የሚይዝ፥ መሃሉ ክፍት የሆነ ክብና ጠፍጣፋ ብረት ወይም ጎማ።

**ሮጠ** ግ 1. ቶሎ ቶሎ ተራመደ፥ በፍጥነት ሄደ፥ ሸመጠጠ። 2. ቸኮለ፥ ተጣደፈ። *ለጠብ ለምን ትሮጣለህ።*

**ሩጫ** ስ 1. የጥድፊያ፥ የችኮላ፥ የፍጥነት እርምጃ። 2. ችኮላ፥ ጥድፊያ። 3. በበለጠ ፍጥነት በመሮጥ ሌላውን ለመቅደም የሚደረግ ስፖርታዊ ውድድር፥ እሽቅድድም።

**ሯጭ** ቅ 1. ፈጣን። ስ 2. በሩጫ ውድድር የሚካፈል፥ የሚወዳደር ስፖርተኛ።

**ተሯሯጠ** ግ 1. ሌላውን ለመቅደም፥ ለመከተል፥ ለማሳደድ ወይም ተከታትሎ ለመድረስ ሮጠ። 2. ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተዋከበ (ጉዳይ ለመፈፀም፥ አንድ ነገር ለማግኘት፥...)።

**አሯሯጠ** ግ 1. አሳደደ፥ አባረረ፤ ለመያዝ፥ ለመምታት፥... ሲል ተከትሎ ሮጠ። 2. አጣደፈ። 3. አዳከመ፥ አለፋ።

**አሮጠ** ግ 1. እንዲሮጥ አደረገ፥ አጣደፈ። 2. አለፋ፥ አደከመ፥ ወዲያ ወዲህ አሰኘ።

**ሯ** የ "ረ" ፈደል ፍንፅቅ ዘር።

**ሯጭ** "ሮጠ" ስር ተመ.

# ሰ

**ሰ** ከ "ረ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

**ሰሃ (ስሃ)** ስ እንከን÷ ሳካ÷ ሳንካ::

**ሰሃን** "ሳህን" ን ተመ.

**ሰለለ**[1] ግ 1. ቀጠነ÷ መነመነ:: 2.ቀጠነ(ለድምፅ)::

**ስሉል** ቅ 1. ቀጭን÷ የመነመነ:: 2. ቀጭን(ለድምፅ):: *ድምፀ ስሉል::*

**ስሉል መሉል** ቅ ትክክል ያልሆነ÷ ቀጭንና ወፍራም ሆኖ የተፈተለ(ፈትል)::

**አሰለለ** ግ አቀጠነ÷ አመነመነ::

**ሰለለ**[2] ግ 1. በማየት÷ በመስማት ወይም በሌላ ዘዴ የሌላውን ወገን ምንነት÷ ሁኔታ÷... በሚመለከት ምስጢራዊ መረጃ አጠናቀረ÷ ሰበሰበ:: 2. አየ÷ ተመለከተ÷ ቃኘ::

**ሰለል ብሎ ገባ** ሰተት ብሎ ሳይታወቅ÷ ሳይሰማ ገባ::

**ሰላይ** ስ ምስጢራዊ መረጃ የሚያጠናቅርና የሚሰበስብ ሰው::

**ስለላ** ስ የመሰለል ተግባር::

**[የ]ስለላ ድርጅት** ስ የስለላ ስራን የሚያካሂድ ድርጅት::

**ተሰለለ** ግ አንድን ሰው÷ ሃገር÷... በተመለከተ ምስጢራዊ መረጃ ተሰበሰበ፥ የስለላ ተግባር ተካሄደበት::

**ተሳለለ** ግ የማጠያየቅ÷ የማፈላለግ ስራ ሰራ÷ አየ÷ ቃኘ:: *ልጅ ጠፍቶብኛልና እስኪ በአካባቢህ ተሳለልልኝ::*

**አሰለለ** ግ 1. ሰላይ ምስጢራዊ መረጃ እንዲያገኝ አደረገ÷ ሁኔታን አመቻቸ:: 2. በሌላው ላይ ስለላ እንዲካሄድ አደረገ::

**አሳለለ** ግ አጠያየቀ÷ አፈላለገ÷ አየ÷ ቃኘ::

**ሰለመ**[1] ግ የእስልምና ሃይማኖትን ተቀበለ÷ እስላም ሆነ::

**ሙስሊም** ስ እስላም::

**እስላም** ስ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ፤ሙስሊም::

**እስልምና** ስ በነቢዩ መሃመድ የተመሰረተና አላህን ብቸኛ አምላክ÷ ነቢዩ መሃመድን የአላህ መልእክተኛ ወይም ነቢይ አድርጎ የሚቀበል ሃይማኖት::

**ሰለመ**[2] ግ 1. ጨለመ:: 2. ደከመ÷ ዛለ (አይን÷ ሰውነት÷...)::

**ስልም አለ** ግ 1. ጭልም አለ:: 2. ዛል÷ ድክም አለ::

**ስልምልም** ቅ ዝልፍልፍ ወይም ድክም ያለ::

**ስልምልም አለ** ግ 1.ዝልፍልፍ ወይም ድክም አለ:: 2. አይኑ በድካም መልክ ክፍት ክድን አለ::

**ስልምልም አደረገ** ግ አዝለፈለፈ÷ አደካከመ፤ አይኑን ክፍት ክድን አደረገ::

**ተስለመለመ** ግ 1. ተዝለፈለፈ÷ ድክምክም አለ:: 2. በድካም መልክ ክፍት ክድን አለ(አይኑ)::

**አስለመለመ** ግ 1. አዝለፈለፈ÷ አደከመ:: 2. በድካም መልክ ክፍት ክድን አደረገ(አይኑን)::

***ሰለመ**

**ሰላም** ስ 1. ረብሻ÷ ሁከት÷ ጦርነት የሌለበት÷ የተረጋጋ ሁኔታ:: 2. ደህንነት÷ ጤንነት÷ የአእምሮ እረፍት:: 3. በቁም ዜማና በማህሌት መጨረሻ ላይ የሚባል ዜማ::

**ሰላም አለ** ሰላምታ ሰጠ::

**ሰላም ወዳድ** ሰላምን የሚፈልግ÷ ለሰላም የቆመ::

**በሰላም** ተው.ግ. 1. በደህና÷ አደጋ በሌለበት ሁኔታ:: *በሰላም ይመልስህ*፡ 2. ጠብ÷ ረብሻ÷ ግጭት በሌለበት ሁኔታ:: *በሰላም አብረን እንኖራለን::* 3. በተረጋጋ መንፈስ:: *ስራዬን በሰላም መስራት እፈልጋለሁ::*

**በሰላም(በሰላማዊ) መንገድ** በመግባባት መልክ÷ ቅራኔን በውይይት በመፍታት÷ ያለ መሳሪያ ትግል::

**የሰላም ልኡካን** ስ ሰላምን ለማስፈን÷ እርቅን ለማውረድ÷... የተላኩ መልእክተኞች::

**የሰላም ውል** ስ በጠብ ወይም በጦርነት ያለ መፈላለግ ውል::

**የሰላም ጉባኤ** ስ በሃገሮችና በህዝቦች መካከል ሰላም እንዲሰፍን÷ ወንድማማችነትና የጋራ ትብብር እንዲዳብር ለማድረግ የሚደረግ ስብሰባ::

**ሰላማዊ** ቅ 1. በወታደራዊ እንቅስቃሴ ወይም በጦርነት ላይ ተሳትፎ የሌለው:: 2. በወንጀል ወይም በሽብር ፈጠራ ተሳትፎ የሌለው፡

**ሰላማዊ ሰልፍ** ስ ፖለቲካን ኢኮኖሚንና ማህበራዊ ጉዳይን አስመልክቶ ደስታን ቅሬታን ለመግለፅ÷ ጥያቄን ለማቅረብ÷መፈክሮችን በመያዝና በአንደበትም በማሰማት በርካታ ሰው በሚገኝበት አካባቢና በአደባባይ በይፋ የሚደረግ ሰልፍ ወይም ስብሰባ፤ ትእይንተ ህዝብ::

**ሰላምታ** ስ ሰዎች ሲገናኙ እጅ በመጨባበጥ፥ ከአንገት ጎንበስ በማለትና እንደምነህ፥ እንደምነሽ በመባባል ወዘተ. ወይም በመልእክተኛ፥ በደብዳቤ የሚለዋወጡት የመልካም ምኞት መግለጫና የጤንነት ጥያቄ።

**ሰላምታ ሰጠ** ለሰላምታ እጁን ዘረጋ፥ አጎነበሰ ፥ እጅ ነሳ።

**ሰላምታ ነፈገ** ሰላምታ መስጠት ተወ ወይም ከለከለ።

**ሰላምተኛ** ቅ ትሁት፥ ትህትና ያለው፥ ሰላምታ ሳይሰጥ የማያልፍ።

**ተሳለመ** ግ ቤተክርስቲያንን፥ መስቀልን፥ ቅዱሳት መፃህፍትን፥ የቄስ እጅን፥ ...በመሳምና እጅ በመንሳት ለእግዚአብሄር ያለውን አምልኮት ወይም ክብርና ምስጋና ገለፀ።

**መሳለሚያ** ስ በቤተክርስቲያን አንፃር ወይም ትይዩ ባለ መንገድ ላይ መንገደኛ የሚሳለምበት የእጅ መንሻ ወይም የመሳለሚያ ምልክት (ለምሳሌ የተከመረ ድንጋይ) ያለበት ቦታ።

**ተሳላሚ** ስ ቤተክርስቲያንን ለመሳለም ወይም ለማስቀደስ የሚሄድ ሰው።

**አሳለመ** ግ 1.ቄሱ እጁን ወይም መስቀልን፥ ዲያቆኑ ቅዱሳት መፃህፍትን በማቅረብ ምእመናን እንዲሳለሙ አደረገ። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) አስከሬን ወደ መቃብር ከመውረዱ በፊት የቤተክርስቲያንን ደጃፍ ሶስት ጊዜ እጅ እንዲነሳ አደረገ፣ አሰገደ(አስከሬኑን ለ3 ጊዜ ዝቅ ከፍ እያደረጉ በማሰገድ)።

**ሰለሰ** ግ 1. ለሶስተኛ ጊዜ አደረገ ወይም ደገመ። 2. ውሃ ጨመረ (በወጥ፥ በጠላ፥... ውስጥ)።

**ሰልስት(ሳልስት)** ስ 1. አንድ ቀን አልፎ ያለው ሶስተኛው ቀን። 2. ሙት የተቀበረበት ወይም አፈር የቀመሰበት ሶስተኛ ቀን።

**ሰልስትና(ሳልስትና)** ከትናንት ወዲያ።

**ሳልሳይ(ሳልሳዊ)** ቅ ሶስተኛ። *ሳልሳይ ዮሃንስ።*

**ሳልስ** ስ እንደ "ሂ" ፥ "ሊ"፥ "ሚ"፥... ያሉ በካእብና በራብእ መካከል የሚገኙ ሶስተኛዎቹ የፊደላት ዘሮች መጠሪያ ወይም የድምፅ ምልክት።

**ስሉስ** ስ 1. በገበጣ ጨዋታ፥ ውግ ሊወጋበት የሚችል ሶስት ጠጠር ያለበት ቤት። 2. የሶስት ቡድን፥ ሶስት በአንድነት። *በስሉስ ዳኛ በሺ ሰርገኛ ልማ በስሉስ ጥፋ በስሉስ።*

**ስሉሴ** ስ በብር ወይም በወርቅ ወይም በነሃስ መደብ ላይ በ3 በ3 ረድፍ ተንጠልጣይ (ፗፗቴ) ሆኖ የሚሰራና በበቅሉ አንገት ላይ የሚደረግ ጌጥ።

**ስላሴ** ስ 1. (ክር.) የእግዚአብሄር በአካል፥ በስም፥ በግብር የሶስትነቱ መግለጫ ስም። 2.የታቦት ስም። 3. ስድስት ቤት ያለው የቅኔ አይነት።

**ተሰለሰ** ግ ሶስት ጊዜ ተደረገ፥...።

**አሰለሰ** ግ 1. ሶስት ጊዜ አደረገ ወይም ሰራ። 2.በየሶስተኛው ቀን መጣ ወይም ሄደ።

**አያሰልስም** አያቋርጥም፤ ሁልጊዜ ይመጣል ወይም ይሄዳል፥ ወይም አንድን ነገር ሁልቀን ያደርጋል።

**ሰለሰለ** ግ 1. ቀጠነ፥ መነመነ፥ ሰለለ። 2. ሰነጠቀ፥ ሸነሸነ (ሰሌንን፥ ግራምጣን፥...)።

**ስልሳላ** ቅ ቀጭን፥ መንማና፥ ሰላላ።

**አሰለሰለ** ግ አቀጠነ፥ አመነመነ፥ አሰለለ።

**ሰለቀ** ግ 1. ፈጨ፥ ደቆሰ፥ አለዘበ፥ አላመ፥ አደቀቀ። 2. አመመ፥ አደከመ። *በሽታው ሰለቀው።* 3. አዘረጠ፥ መታ (በዱላ፥ በክርን)።

**መሰለቂያ(መሰለቂት)** ስ ማላሚያ ወፍጮ (የመገርደፊያ ተቃራኒ)።

**ስልቅ** ቅ የተፈጨ፥ የላመ፥ የደቀቀ (እህል)።

**ተሰለቀ** ግ በጣም ደቆ ተፈጨ፥ ላመ።

***ሰለቀ**

**ስላቅ** ስ ፌዝ፥ ለግጥ፥ ቀልድ።

**ተሳለቀ** ግ አፌዘ፥ አላገጠ፥ ቀለደ፥ አሾፈ።

**ተሳልቆ** ስ ስላቅ።

**ሰለቀጠ** ግ ሳያኝክ ወይም ሳያላምጥ ዋጠ።

**ሰለበ** ግ 1. የወንድን አባለዘር ቆረጠ። 2. በምትሃት፥ በዘዴ፥ በአስማት፥ የሰውን ገንዘብ ወሰደ። 3. አደከመ፥ አዛለ። *በሽታው ልቡን ሰለበው።* 4. ዘጋ (ድምፅን)።

**ሰለባ** ስ 1. የግዳይ፥ የድል ምልክት፥ ምርኮ። 2. በዝርፊያ ወይም በቅሚያ የተሰበሰበ እቃ ወይም ንብረት። 3. በሌላ ሰው ድርጊት ወይም በተለያዩ አደጋዎች ምክንያት መከራ፥ ችግር፥ ጉዳት የደረሰበት ሰው፥አገር፥...። *የጦርነቱ ሰለባዎች ብዙ ናቸው።*

**ሰላቢ** ስ 1. በምትሃት፥ ባስማት ወይም ሳይታወቅበት የሰውን ገንዘብ የሚወስድ። 2.(ስድብ) ሾካካ፥ ቀትረ ቀላል።

**ስልብ** ቅ አባለዘሩ የተቆረጠ (ሰው)።

**ተሰለበ** ግ 1. አባለዘሩ ተቆረጠ። 2. ተፋጠነ፥ ተቀላጠፈ፥ በፍጥነት ተከናወነ፥ ተካሄደ። *እገሌ መንገድ፥ ስራ፥...ይሰለብለታል።* 3. ጠፋ፥ ተሰወረ።

**ሰለተ[1]** ግ የሳር ቤትን ሲሰራ ሰንበሌጡን ወይም

ሳሩን፥...እናቱን ወደታች ስሩን ወደላይ አድርጎ ከደነ።

**ስለታ** ስ የሰንበሌጡ ወይም የሳሩ እናት ወደታች ተዘቅዝቆ፥ ቂጡ ወደላይ ተደርጎ የሚሰራ የሳር ቤት አከዳደን አይነት፤ የከፍከፍ የቤት አከዳደን ተቃራኒ።

**ስለተ**[2] ግ 1. ከሳ፥ ቀጠነ፥ መነመነ። 2. ፍሬ አልባ ሆነ፥ ከሰመ፥ ጠወለገ፥ ደረቀ።

**ስለታ "ስለተ**[1]**"** ስር ተመ.

**ሰለቸ** ግ 1. ታከተ፥ ደከመ። 2. ተመረረ፥ ተንገፈገፈ፥ ጠላ (አንድን ነገር ደጋግሞ በመስራት፥ በማየት፥ በመስማት፥...)። 3. አስጠላ፥ አስቀየመ (ተደጋግሞ በመሰራቱ፥ በመታየቱ፥ በመሰማቱ)።

**ስልቹ** ቅ ቶሎ የሚጠላ፥ የሚሰለች፥ የሚታክት።

**ተሰለቸ** ግ በመደጋገሙ ተጠላ።

**ተሰላቸ** ግ ሰለቸ፥ ጠላ፥ ታከተ።

**አሰለቸ** ግ 1. አደከመ፥ አታከተ፤ አንገፈገፈ፥ አስጠላ (በመብዛት፥ በመደጋገም)። 2. ደጋግሞ ጠየቀ ወይም ለመነ፥ ጨቀጨቀ።

**አሰልቺ** ቅ 1. በጣም አድካሚ የሆነ፥ የሚያሰለች። 2. ጨቅጫቃ፤ በልመና፥ በጥያቄ የሚያሰለች።

***ሰለከለከ**

**ሰለክላካ (ስልክልክ)** ቅ እንደ እባብ ሹልክልክ እያለ የሚሄድ።

**ተስለከለከ** ግ ተሽሎከሎከ።

***ሰለከከ**

**ስልካካ** ቅ አፍንጫው ቀጠንና ረዘም ብሎ የወረደ፤ መልከ ቀና፥ ቆንጆ (ሰው)።

**ስልክክ ያለ** ቀጥ ብሎ የወጣና የሚያምር (አፍንጫ፥ መልክ)።

**ሰለክላካ "*ሰለከለከ"** ስር ተመ.

**ሰለጀጀ** ግ ደከመ፥ ፈዘዘ፥ ነሆለለ።

**ስልጃጃ** ቅ ፈዛዛ፥ ነሁላላ።

**ተንሰለጀጀ** ግ ደከመ፥ ፈዘዘ።

**አንሰለጀጀ** ግ አደከመ፥ አፈዘዘ።

**ሰለጠ** ግ ቀና ሆነ፥ ተከወነ፥ ቀለጠፈ።

**አሰለጠ** ግ ቶሎ ቶሎ አከናወነ፥ አፍጥኖ ጨረሰ።

**ሰለጠነ** ግ 1. አደገ፥ ተሻሻለ፥ ዘመናዊ ሆነ፥ ከፍ ወደአለ የእውቀት ደረጃ ደረሰ፥ ከሂላ ቀርነት ራቀ (ሃገር፥ ህዝብ)። 2. አንድን ነገር ማድረግ ወይም መስራት አወቀ፥ ለመደ። 3. ተሻሻለ፥ ንቁ ሆነ፥ ቀለጠፈ። 4. አንድን ሙያ ተማረ፥ ተካነ፥ ትምህርት አገኘ። *በሀክምና ትምህርት ሰለጠነ።* 5. ምቹ ሁኔታ አገኘ፤ አየለ። *ገደል ባለበት ሃገር ዝንጀሮ ይሰለጥናል።*

**ስልጠና** ስ አንድን ተግባር ወይም ድርጊት በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል እውቀት፥ ተግባራዊ ትምህርት፥ ልምምድ።

**ስልጡን** ቅ 1. ንቁ፥ ቀልጣፋ፤ ጨዋ፤ ትሁት፤ ስርአት ያለው። 2. ስልጠና ያገኘ፥ የሰለጠነ።

**ስልጣኔ** ስ እድገት፥ ዘመናዊነት፥ ከፍተኛ የእውቀት ወይም የመሻሻል ደረጃ።

**ስልጣን** ስ 1. አንድን ነገር ለማድረግ፥ ለመስራት ወይም ለማሰራት የሚያስችል መብት። 2.የመንግስት አስተዳደርን ወይም አመራርን በበላይነት ለማካሄድ የሚያስችል ሃይል። 3. ሹመት፥ ሃላፊነት፤ 4 (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የድቁና ወይም የቅስና፥... ማእረግ፤ ክህነት።

**ስልጣኑን አሳየ** የተሰጠውን ሃላፊነት ተጠቅሞ እርምጃ ወሰደ።

**ስልጣን ያዘ** ስልጣን ጨበጠ፥ ሹመት አገኘ (አብዛኛውን ጊዜ የመንግሥትን)።

**ባለስልጣን** ስ አንድን ነገር ለማድረግ፥ ለመስራት ወይም ለማሰራት አመራርን ለመስጠት ፥ለመወሰን የሚያስችል መብት ያለው ግለሰብ ወይም ድርጅት።

**ከስልጣን በላይ** ስልጣኑ ከሚፈቅድለት፥ ወይም ከችሎታው ክልል ውጭ።

**የስልጣን ሽሚያ** ስ ስልጣንን ለመያዝ ወይም ለመጨበጥ የሚደረግ ውድድር፥ ሽኩቻ።

**የስልጣን ጥመኛ** ቅ ከፍተኛ የሆነ የስልጣን ጉጉት ያለው።

**አሰለጠነ** ግ 1. አሳደገ፥ አሻሻለ፥ ዘመናዊ አደረገ፥ ከፍ ወደአለ የእውቀት ደረጃ አደረሰ። 2.አንድን ነገር ማድረግ ወይም መስራት አስለመደ፥ ሙያን አስተማረ፥ አሳወቀ። 3 ንቁ፥ ቀልጣፋ አደረገ።

**ማሰልጠኛ** ስ አንድ አይነት የሙያ ትምህርት የሚሰጥበት ተቋም።

**አሰልጣኝ** ቅ አንድን ሙያ የሚያስተምር።

**ሰለፈ** ግ 1. ሰደረ፥ ደረደረ። 2. አንድ ነገር ለማድረግ ተዘጋጀ፥ ቸኮለ፥ አቆበቆበ፥ በጣም ጓጓ። 3. ለጦርነት፥ ለውጊያ ተዘጋጀ።

**ሰልፍ** ስ 1. ረድፍን፥ መስመርን፥ ተርታን የያዘና ስነ ስርአትን የተከተለ የእግር ጉዞ። 2 . ረድፍን፥ መስመርን፥ ተርታን ይዞ ስነ ስርአት ባለው ሁኔታ የቆመ የሰዎች ስብስብ። 3. ተራ ወይም ቅደም ተከተል ያለው ወይም ረድፍ የያዘ አቋቋም፥ አቀማመጥ።

**ሰልፈኛ** ስ ረድፍን፥ መስመርን፥ ተርታን ይዞና ስነስርአትን ተከትሎ በመጓዝ ወይም በመቆም ሰልፍ ውስጥ የሚሳተፍ ሰው፤ ወይም የሚሳተፉ ሰዎች በጠቅላላ።

**ተሰለፈ** ግ 1. በተርታ፥ በረድፍ፥ በመስመር ገባ፥ ተደረደረ፥ ተሰደረ፥ ተራ ያዘ። 2. በሰላማዊ ሰልፍ ወይም በሌላ ሰልፍ ተሳተፈ።

**ተሰላፊ** ስ ሰልፈኛ።

**አሰለፈ** ግ በሰልፍ፥ በረድፍ፥ በመስመር እንዲሆን አደረገ።

**አሰላፊ** ስ የሰልፍ አስተባባሪ።

**አሰላለፍ** ስ በስፖርት ግጥሚያዎች የተጨዋቾች የቦታ አያያዝ፥ምደባ።

**ሰሊጥ** ስ የመብል ዘይት የሚወጣውን ፍሬ የሚያፈራ ሰብል፤ ፍሬውም ሰሊጥ ይባላል።

**ሰላ**[1] ግ 1. ስለታም ሆነ፥ ተባ፥ ሾለ። 2.(ዘይ.) ጎበዝ ሆነ፥ ቀለጠፈ። 3. ሾለከ። *ውሃ በቀዳዳ ሰልቶ ይወርዳል።* 4. (አባያ የነበረው በሬ) ተስተካከለ፤ ተገራ።

**ስል** ቅ 1. ስለት ያለው፥ በቀላሉ መቁረጥ የሚችል። 2. (ዘይ.) ብልህ፥ ቀልጣፋ፥ ጎበዝ የሆነ።

**ሰላ**[2] ግ በጀ፥ አማረ፥ ቀና፥ ሰመረ፥ ተሳካ።

**ሰላ በልልኝ** ገር፥ ቀና ሁንልኝ።

**አይሰላለትም** አይሳካለትም።

**ተሳላ** ግ 1. ተቀናበረ፥ ተሳካ፥ ተከናወነ። 2. ተስማማ፥ ገጠመ። *ምፈርና እርፉ ተሳላለት።*

**አሳላ** ግ አስማማ። *ምፈርና እርፍ አሳልቶ ማረስ ይችላል።*

**ሰላ**[3] ግ ማረሻ ቀና ብሎ ወደ ሞፈሩ በመጠጋቱ ወይም ዶማ ጋደም ብሎ ወደ እጀታው በመጠጋቱ ጠለቅ አድርጎ የማያርስ ወይም የማይቆፍር ሆነ።

**ስል** ቅ የሰላ (ማረሻ፥ ዶማ)።

**አሰላ** ግ በጣም ጋደም እንዲል፥ ወደ እጀታው ወይም ወደ ሞፈሩ እንዲጠጋ አድርጎ አበጀ (ዶማን ወይም ማረሻን)።

***ሰላ**

**ስሌት** ስ የመደመር፥ የመቀነስ፥ የማብዛትና የማካፈል ስራ።

**ተሳላ** ግ ተሳሰበ፥ ተቆጣጠረ።

**አሰላ** ግ ሂሳቡን አሰበ (ደመረ፥ ቀነሰ፥ አበዛ፥ አካፈለ)።

**ሰላላ** "ሰለለ[1]" ስር ተመ.

**ሰላማዊ** "*ሰለመ" ስር ተመ.

**ሰላም** ዝ.ከ.

**ሰላምተኛ** ዝ.ከ.

**ሰላምታ** ዝ.ከ.

**ሰላሴት** ስ ክክ።

**ሰላሳ** ስ 1. በሃያ ዘጠኝና በሰላሳ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ። በአሃዝ ሲፃፍ ፴፥30 ነው። ቅ 2. ብዛቱ ሶስት አስሮችን የሚያክል የቁጥር መጠን። *ሰላሳ መፃህፍት።*

**ሰላቢ** "ሰለበ" ስር ተመ.

**ሰላት(ሶላት)** ስ የእስልምና ሃይማኖት ፀሎትና ስግደት።

**ሰላቶ** "ሶላቶ" ን ተመ.

**ሰላይ** "ሰለለ[2]" ስር ተመ.

**ሰላጣ** ስ ቅጠሉ ሳይቀቀል ለምግብነት የሚያገለግል የተክል አይነት።(ስእሉን ቅጠላቅጠል ስር ተመ.)

**ሰላጤ** ስ 1. ሹል ወይም ሾጣጣ የሆነ ነገር። 2. በሱሪ ወይም በሌላ ልብስ ላይ ሾጠጥ ብሎ የተሰፋ ወሽመጥ።

**ሰሌን** ስ 1. የዘምባባ ቅጠል። 2. ከዘምባባ ቅጠል የሚሰራ ምንጣፍ።

**ሰሌን ባርኔጣ** ስ ከዘምባባ ቅጠል የሚሰራ ባርኔጣ።

**ሰሌዳ** ስ በላዩ ለመፃፍ፥ ማስታወቂያ ለመለጠፍ ወዘተ. የሚያገለግል ዝርግና ጠፍጣፋ የሆነ እንጨት፥ ክርታስ የመሳሰለ ቁም / ልጥፍ ነገር።

**ሰልሳላ** "ሰለሰለ" ስር ተመ.

**ሰልስት** "ሰለሰ" ስር ተመ.

**ሰልስትና** ዝ.ከ.

**ሰልካካ** "*ሰለከከ" ስር ተመ.

**ሰልጃጃ** "ሰለጀጀ" ስር ተመ.

**ሰልፈኛ** "ሰለፈ" ስር ተመ.

**ሰልፍ** ዝ.ከ.

**ሰመለለ** ግ ኸው አድርጎ ጠጣ፥ ሸመጠጠ።

**ሰመመ** ግ አሸለበ፥ አንቀላፋ፥ አንጎላጀ፥ ፈዘዘ።

**ሰመመን** ስ ሽልብታ፥ እንቅልፍ፥ የመፍዘዝ ሁኔታ።

**ሰመመናም** ቅ የሚደብት፥ የሚጫጫን፥ የሚያፈዝ(ሁኔታ፥ አድራጎት፥...)።

**ሰመረ** ግ አማረ፥ ጥሩ ሆነ፥ ተሳካ።

**ስምረት** ስ የማማር፥ የመሳካት ሁኔታ።

**አሰመረ** ግ አሳካ፥ ጥሩ አደረገ።

***ሰመረ**

**መስመር** ስ 1. ቀጥተኛነት ያለውና ረዘም ያለ የቀለም፥ የእርሳስ ወይም የሌላ ነገር ጭረት። 2. አቅጣጫ። *የጉዟችን መስመር በሰሜን በኩል ነው።* 3. አርእስት። *ውይይታችን መስመሩን ሲቷል።* 4. ተርታ፥ መደዳ፥ ሰልፍ። 5. ፅሁፍን በቀጥታ፥ በተርታና ወጣ ገባ ሳይል ለመፃፍ እንዲያስችል በሚፃፍበት ነገር ላይ የተደረገ ምልክት። 6. ፈር፥ ስርአት። *ስራው መስመር ይዟል።* 7. መመላለሻ፥ መጓጓዣ፥ መገናኛ መንገድ። 8. ጣቢያ (የሬዲዮ)። 9. መመሪያ። *ትክክለኛ የሆነ የፖለቲካ መስመር ይከተላል።*

**መስመር ለቀቀ** ተሳሳተ፥ ትክክል ባልሆነ መንገድ ሄደ።

**መስመር ዘረጋ** እንደ የኤሌትሪክ፥ የቴሌፎን፥ የውሃ፥ የፍሳሽና የትራንስፖርት ያለ የአገልግሎት አውታር ዘረጋ፥ አበጀ፥ አዘጋጀ፥ አቋቋመ።

**ከመስመር ወጣ** ከደንብ፥ ከስነ ስረአት ውጭ ሆነ።

**ከመስመር ውጪ** የእግር፥ የመረብ፥ የቅርጫት ኳስ በመሳሰሉት ጨዋታዎች ከተዘጋጀውና በምልክት ከተከለለው ወይም ከተፈቀደው የሜዳ ክልል ውስጥ የኳስ መውጣት።

**የመስመር ዳኛ** ስ በኳስ ጨዋታ ጊዜ የመሃል ዳኛውን ለመርዳት በኳሱ ሜዳ በስተግራ ወይም በስተቀኝ ሆኖ የሚያገለግል ረዳት ዳኛ።

**ተሰመረ** ግ ቀጥ ያለ መስመር ተደረገ።

**አሰመረ** ግ ቀጥተኛ መስመር ነደፈ።

**አሰመረበት** አፅንኦት ሰጠው።

**ማስመሪያ** ስ ከእንጨት ወይም ከብረት ወይም ከፕላስቲክ ወዘተ. የሚሰራ፥ ቀጥተኛ ጎን ያለውና ቀጥ ያለ መስመር ለመስራት የሚያገለግል፥ ቀጭን፥ ረዥም የሆነና በተወሰነ የርዝመት መለኪያ (በሳንቲ ሜትር፥ በኢንች፥...) መጠን የተከፋፈለ የፅህፈት መሳሪያ(ስእሉን የፅህፈት መሳሪያ ስር ተመ.)።

**ሰሞሬታ** ስ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚደርስ የገብስ አይነት።

***ሰመር**

**ሰመር ገባ** (በትግል ውድድር ላይ) ተያዘ፥ ተሸነፈ፥ በቁጥጥር ስር ሆነ።

**ሰመር ገጠመ** በትግል ወይም በትንቅንቅ ጊዜ ወገብ ለወገብ አጥብቆ ተያያዘ።

**ሰመሰመ** ግ ቶሎ ቶሎ ጎረሰ፥ በላ።

***ሰመነመነ**

**ተስመነመነ** ግ ደከመ፥ ደቀቀ፥ ተስለመለመ(በእንቅልፍ፥ በበሽታ፥ በድካም)።

**አስመነመነ** ግ አደቀቀ፥ አደከመ።

**ሰመግ** ስፍሬው ጥቁረትና ንጣት የተደባለቀበትና በቆላ አካባቢ የሚገኝ እንደ ሃረግ ያለ የእፅዋት አይነት።

**ሰመግግ** ቅ እንደ ሰመግ ፍሬ ዥንጉርጉር፥ ወይም ጠቃጠቆ መልክ ያለው (ለከብት)።

**ሰመጠ(ሰጠመ)** ግ ጠለቀ፥ ገባ፥ ሰረገ፥ ዘቀጠ።

**ስምጥ** ቅ ጥልቅ።

**ስምጥ ሸለቆ** ስ በመሬት መሰንጠቅና በመስረግ ምክንያት የተፈጠረ በሰሜን ምስራቅ አፍሪቃ የሚገኝ ጥልቅና ረባዳ ሸለቆ።

**ስምጥ ስምጥ አለ** ግ ትምቡክ ትምቡክ አለ።

**አሰመጠ (አሰጠመ)** ግ 1. ወደ ውስጥ አጠለቀ፥ አገባ፥ አሰረገ (ውሃ ፥ ረግረግ፥...)። 2. አጠለቀ፥ ዘፈቀ፥ በብዛት ወጣ (ላብ)።

**ሰመጠጠ**[1] ግ ሸመጠጠ፥ ጨለጠ፥ ጠጣ።

**ሰመጠጠ**[2] ግ ከተተ፥ እስከ መጨረሻው አስገባ (ሰንጢ፥ ጩቤ፥...)።

**ሰሙነ ህማማት** "ሰሞን" ስር ተመ.

**ሰማ**[1] ግ 1. አደመጠ። 2. ተቀበለ፥ የተነገረውን ያዘ፥ ተረዳ። *ምክር ይሰማል።*

**ይሰማል** በመጠኑ፥ያውቃል። *ላማርኛ ይሰማል።*

**ስማልኝ** አስተውል፥ ታዘብ፥ ልብ አድርግ።

**ስማ በለው** ስ የቃል ትርጁማን፥ አስተርጓሚ።

**በስማበለው** በአስተርጓሚ። *ከፈረንጁ ጋር በስማ በለው ተነጋገርኩ።*

**ስማ ተሰማማ** በቀድሞ ጊዜ አዋጅ ለመንገር ሲፈለግ ይህን አዋጅ አድምጥ፥ ሳልሰማም ንገር ለማለት አዋጁ በሚነገርበት ቦታ ላይ በመጀመሪያ የሚባል የተሰብሰቡና የአዋጅ ስሙ ጥሪ ማስሚያ ቃል።

**ለይስሙላ** ለወሬ፥ ለስም ያህል፥ በትንሹ።

**ሰሚ** ቅ 1. አድማጭ ወይም አዳማጭ። 2. እሺባይ፥ ተቀባይ።

**አልሰሜ** ቅ ያልሰማ፥ ያልተረዳ፥ ለነገሩ እንግዳ የሆነ (ሰው)።

**ስሚ** ስ ጭምጭምታ፥ ወሬ።

**የስሚ ስሚ** ስ ጭምጭምታ፥ የወሬ ወሬ።

**ስሜት** ስ 1. በአእምሮ ወይም በአካል ላይ የሚንፀባረቅ የአንድ ነገር ተፅእኖ ውጤት። 2. ፍላጎት፥ ዝንባሌ (ለመስራት፥ ለማወቅ፥...)።

**ስሜቱ ተቀሰቀሰ /ተነሳሳ** አንድን ነገር ለመስራት፥ ለማግኘት፥ ለማወቅ ያለው ጉጉት ከፍ አለ።

**ስሜት አይሰጠውም** ደንታ የለውም፥ ግድ የለውም።

**የስሜት ህዋሳት** ስ ለመስማት፥ ለመቅመስ፥ ለማየት፥ ለመዳሰስና ለማሽተት የሚያገለግሉ እንደ ጆሮ፥ ምላስ፥ አይን፥ አፍንጫ የመሳሰሉ የሰውነት ክፍሎች።

**ስሜታዊ** ቅ በግል ፍላጎት የተመረኮዘ፥ ተጨባጭ መለኪያ የሌለው።2.ነገሮችን ሳያገናዝብ በስሜቱ ብቻ የሚመራ(ሰው)።

**ስምም** ቅ 1. ጥል፥ ቅዋሜ፥ ግጭት የሌለው። ስ 2. ፍቅር፥ ወዳጅ፥ ሰላም።

**ስምሙ** ቅ ስምም።

**ስምምነት** ስ 1. ፍቅር፥ ወዳጅነት፥ መግባባት። 2. ውል። 3. በመወያየት ወይም በመነጋገር የሚደረስበት ይሁንታ።

**ስሞታ** ስ እገሌ እንዲህ ሰራኝ፥ አደረገኝ ብሎ ለሶስተኛ ሰው የሚነገር ወቀሳ፥ ቅሬታ።

**ስሞተኛ** ቅ ስሞታ መናገር የሚወድ።

**ተሰማ** ግ 1. ተደመጠ፥ ጆሮ ገባ። 2. በሌሎች ታወቀ። 3. ተቀባይነት፥ ተጻማጭነት አገኘ።

**ተሰማው** 1. የሃዘን፥ የቅሬታ ስሜት ገባው። 2. የኩራት፥ የንዴት፥ የበሽታ...፥ ስሜት ፈጠረበት።

**ተሰሚ** ቅ ተቀባይነት ወይም ተደማጭነት ያለው።

**ተሳማ** ግ ተዳረሰ፥ ተስፋፋ (ወሬው)።

**ተስማማ** ግ 1. ተዋዋለ፥ ውሉታ ገባ። 2. ታረቀ፥ ቅራኔውን አስወገደ። 3. ጥሩ ሆነ፥ ተመቸ(አየሩ፥ ሃገሩ፥ ልብሱ፥...)። 4. አንድ ነገር ለመስራት አበረ፥ አንድ ሆነ። 5. ተቀበለ፥ እሺ አለ።

**ተስማሚ** ቅ ጥሩ፥ ምቹ (አየር፥ ሃገር፥ ልብስ፥...)።

**አሰማ** ግ 1. ነገረ፥ አሳወቀ። *ሓቤቱታውን ሓሰማ*። 2. እንዲደመጥ፥ ከጆሮ እንዲገባ አደረገ።

**አሳማ** ግ አዳረሰ፥ አስፋፋ (ወሬውን)።

**አስማማ** ግ 1. አስታረቀ፥ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ባሉ ሰዎች መካከል የነበረውን ቅራኔ፥ ጥል፥ ግጭት አስወገደ። 2. ለመሸጥ እንደሚፈልግ አሳወቀ ወይም ለገዥ፥ ለደላላ ነገረ። 3. ገዥና ሻጭን አንተ በዚህ ግዛ አንተ በዚህ ሸጥ አለ፥ አግባባ፤ ደለለ።

**አስማሚ** ስ አስታራቂ፥ ገላጋይ፥ ሽማግሌ።

**ሰማ²** ግ ሞቀ፥ ጋለ፥ ጋመ (ለምጣድ)።

**አሰማ** ግ አሞቀ፥ አጋለ፥ አጋመ።

***ሰማራ**

**ስምሪት** ስ 1.ለአንድ አይነት ስራ መሄድ ወይም መውጣት። 2.ግጦሽ መውጣት (የከብት)። 3.(ትራንስፖርት) የጉዞ መስመር ምደባ።

**ተሰማራ** ግ 1. ለአንድ አይነት ስራ ሄደ ወይም ወጣ። 2. ለግጦሽ ተነዳ፥ ተወሰደ (ከብት)።

**አሰማራ** ግ 1. ለአንድ አይነት ስራ ላከ፥ ሰደደ፥ መደበ። 2. ለግጦሽ አወጣ (ከብትን)።

**ሰማንያ** ስ 1. በሰባ ዘጠኝና በሰማንያ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ በአሃዝ ሲፃፍ "፹" "80" ነው። 2. የጋብቻ ውል። 3. የሙት ሰማንያኛ ቀን፤ ተዝካር። ቅ 4. ብዛቱ ስምንት አስሮችን የሆነ።

**ሰማንያ አወረደ** የጋብቻ ውል አፈረሰ፥ ሚስቱን ፈታ።

**የሰማንያ ሚስት** ስ በጋብቻ ውል የተገባች ህጋዊ ሚስት።

**የሰማንያ ባል** ስ ህጋዊ ባል።

**ሰማእት** (ብ.ቁ. **ሰማእታት**) ስ ለሃገሩ፥ ለእምነቱ፥ ለሃይማኖቱ፥...መስዋእት የሆነ ሰው።

**ሰማይ** ስ ምድርን የከደናት የሚመስል ህዋ፥ ጠፈር፥ ከመሬት በላይ ከአድማስ እስከ አድማስ ያለው ቦታ።

**ሰማይ አረገዘ** ሊዘንብ የተቃረበ መሰለ።

**ሰማይ ከበደ** ሰማይ ጠቆረ፥ ደመና ሆነ፥ ጨፈገገ።

**ሰማይ ሆኗል/ነክቷል** በጣም ውድ ሆኗል (ዋጋው)።

**ሰማይ ተደፋበት** ተቸገረ፥ የሚያደርገውን አጣ።

**ሰማይ ይነካል** በጣም ረዥም ነው (ቁመቱ)።

**ሰማይ ቤት** ስ ከሞት በሃላ ነፍስ ትሄድበታለች ተብሎ የሚታመንበት ቦታ።

**ሰማይ ጠቀስ** ቅ ቁመቱ በጣም ረዥም የሆነ። *ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ሓለው።*

**ሰማይና ምድር** ቅ የተራራቀ፥ የተለያየ፥ የማይመጣጠን።

**የሰማይና የምድሩን ያህል** በሰፊው፥ እጅጉን (ለሰላምታ)።

**የሰማይ ስባሪ** ግዙፍ፥ ትልቅ።

**የሰማይ ቁጣ** ስ የእግዚአብሄር ቁጣ።

**ሰማያዊ** ቅ 1. ሰማይ የሚመስል መልክ

*ወይም ቀለም ያለው*:: 2. *መለኮታዊ፣ ምድራዊ ወይም ኣለማዊ ያልሆነ*:: 3. በሰማይ የሚኖር::

**ሰሜን** ስ ፊቱን ወደ ፀሃይ መውጫ ላዞረ በስተግራ በኩል ያለ አቅጣጫ፤ የደቡብ ትይዩ::

**ሰሜን ምስራቅ** ስ በሰሜንና በምስራቅ መካከል ያለ ቦታ፤ አቅጣጫ፤ መስእ::

**ሰሜን ምእራብ** ስ በሰሜንና በምእራብ መካከል ያለ ቦታ፥ አቅጣጫ፤ ባህር::

**የሰሜን ዋልታ** ስ የምድር ሰሜናዊ ጫፍ::

**ሰሜናዊ** ቅ 1. በስተሰሜን አቅጣጫ ያለ ወይም የሚገኝ:: 2. የሰሜን::

**ሰም** ስ 1. በቀላሉ የመቅለጥ ባህርይ ያለው የተለጠለጠ ወይም የተጋገረ የማር ሰፈፍ:: 2. የጣውላ ወለልን ለመወልወል የሚያገለግል ቅባት:: 3. (ቅኔ) ላይ ላዩን የሚታይ ወይም ግልፅ ሆኖ ፊት ለፊት የሚተላለፍ ሃሳብ::

**ሰምና ፈትል ሆኑ** ተስማሙ፥ ተፋቀሩ፥ ኣንድ ሆኑ::

**ሰም ለበስ** ስ ግሱ እንደሰም ሆኖ የገባበት የቅኔ መንገድ::

**ሰም ረገፍ** ስ ከሰሙ ተለይቶ በወርቅ ብቻ የሚነገር ቅኔ::

**ሰምና ወርቅ** ስ ባለቤቱ ሁለት ሆኖ ባንድ አንቀፅ የሚነገር የቅኔ አይነት::

**ሰምበሌጥ** “**ሰንበሌጥ**” ን ተመ.

**ሰምበር** “**ሰንበር**”ን ተመ.

**ሰምበቴ** “**ሰነበተ**” ስር “**ሰንበቴ**” ን ተመ.

**ሰምና ወርቅ** “**ሰም**” ስር ተመ.

**ሰሞን** ስ 1. ስምንት ቀን:: 2. ጥቂት ቀናት:: *ለኣንድ ሰሞን ወደ ውጪ ሄጄ ነበር*:: 3. ቅርብ ቀን:: *ሰሞኑን እመጣለሁ*::

**ሰሙነ ህማማት** ስ ከሆሳእና እሁድ ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ስኡር ድረስ ያሉት ቀናት::

**የሰሞን መሬት** ስ ለቤተክርስቲያን ኣገልጋዮች (ለቀዳሾች) ይሰጥ የነበረ መሬት::

**ሰሞነኛ** ስ ከእሁድ እስከ እሁድ ቤተክርስቲያንን የሚያገለግል ተረኛ ቄስ ወይም ዲያቆን::

**ሰረረ** ግ ጠቃ፥ መታ፥ በፍትወተ ስጋ ተገናኘ (ለእንስሳ)::

**ስሪያ** ስ የእንስሳት ሩካቤ ስጋ::

**ስር** ቅ የተጠቃች፥ የተሰረረች (ለእንስት እንስሳ)::

**ተሰረረች** ግ ተጠቃች::

**ኣስረሽ ምችው** ሆይ ሆይታ፥ ዘፈን፥የበዛበት ሁኔታ፥ ፈንጠዝያ::

**ሰረሰረ** ግ 1. በቀጭኑ ቦረቦረ:: 2. በሳ፥ ነደለ:: 3. ቤትን፥ በርን ሰበረ (ለስርቆት):: 4. ውስጥ ውስጡን ኣመመ፤ ቆረቆረ(ለምሳሌ ኣፍንጫን):: 5. ውስጥ ለውስጥ ሄደ::

***መሰርሰሪያ*** ስ ለመብሳት ወይም ለመቦርቦር የሚያገለግል መሳሪያ::

**ሰርሳሪ** ስ (ስድብ) ሌባ::

**ተሰረሰረ** ግ ተዘረፈ፥ ተሰረቀ::

***ሰረሰረ**

**ተንሰረሰረ** ግ ተቀቀለ፥ በሰለ፥ ነፈረ፥ ፈላ::

**ኣንሰረሰረ** ግ በጣም ቀቀለ፥ ኣበሰለ፥ ኣነፈረ፥ ኣፈላ::

**ሰረሰር** ስ ውስጠ ክፍት የሆነ የኣፍንጫ ወይም የኣከርካሪ ኣጥንት::

**ሰረቀ**[1] ግ 1. የራሱ ያልሆነውን ነገር፥ ንብረት ደብቆ ወሰደ፥ ሞጨለፈ:: 2. ጠቀሰ:: *በኣይኑ ሰርቆት ሄደ*:: 3. ከትዳር ጓደኛው ደብቆ ከሌላ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀመ፤ ወይም በድብቅ የሌላን ሰው የትዳር ጓደኛ በግብረስጋ ተገናኘ::

**ስርቆሽ** ስ አንድን ነገር በሌብነት የመውሰድ ወይም የመፈፀም ድርጊት::

**ስርቆሽ በር** ስ ነገስታትና መኳንንት ከግቢያቸው ሲወጡና ሲገቡ እንዳይታዩ በሚፈልጉበት ጊዜ ብቻ ይገለገሉበት የነበረና ከዋናው የግቢ በር ይልቅ ከእይታ ገለል ባለው ኣቅጣጫ በኩል ይገኝ የነበረ በር::

**ስርቆት** ስ ሌብነት::

**ስርቅ ብሎ ሄደ** ሹልክ ብሎ ተሰውሮ ሄደ::

**ስርቅ ኣድርጎ ኣየ** ሳያዩት በትንሹ ዘወር ብሎ ተመለከተ::

**ተሰረቀ** ግ 1.ንብረቱን ተዘረፈ ወይም በስርቆት ተወሰደበት:: 2. በድብቅ ወይም ባለቤቱ ሳያውቅ ተወሰደ (እቃው ንብረቱ)::

**ተሰርቆ ሄደ** ተደብቆ ሄደ::

**ሰረቀ**[2] ግ ወጣ፥ ብቅ ኣለ (ጨረቃ፥ ፀሃይ)::

**ምስራቅ** በፊደል ተራው ተመ.

**ሰረበ**[1] ግ በውስጡ ደም ያዘ፥ ቋጠረ (ስጋ፥ ኣይን፥...)::

**ሰረበ**[2] ግ ኳስን ወደ ተቃራኒው ቡድን ለጋ ወይም መታ (በመረብ ኳስ፥ በጠረጴዛ ኳስ፥... ጨዋታ ላይ)::

**ሰርብ** ስ ኳስን ወደ ተቃራኒው ቡድን ለማድረስ የሚለጋ የመጀመሪያ ምት (በመረብ ኳስ፥ በጠረጴዛ ኳስ፥...ጨዋታ ላይ)::

**ሰረነቀ** ግ ወደ ሰርን ውስጥ ገባ፥ አፈነ፥ ትን አለ።

**ስርንቅ አደረገ** ግ ሰነግ፥ እንቅ አደረገ።

**ሰረዘ** ግ 1. በፅሁፍ ላይ አሰመረ፥ እንዳይነበብ አደረገ፥ አጠፋ። 2. ከፅሁፍ (ቃል፥ ሃረግ፥...) ስር መስመር አደረገ፥ አሰመረ (ከሌላው ይበልጥ እትኩሮት እንዲደረግበት)። 3. አፈረሰ፥ አስቀረ፥ ተወ፥ ሻረ።

**ሰረዝ** ስ 1. ከፅሁፍ ስር እንዲሁም ከቃላት በስተሂላ ወይም በስተፊት በኩል በትንሹ አግድም የሚደረግ መስመር። 2. የስርአተ ነጥቦች ምልክት (ለምሳሌ ነጠላ፥ ድርብ ሰረዝ)።

**ስርዝ** ስ 1. እንዳይነበብ ለማድረግ ወይም ለማጥፋት በፅሁፍ ላይ የተሰመረ መስመር። 2. አፅንኦት ለመስጠት ከፅሁፍ ግርጌ ወይም ስር የተሰመረ መስመር።

**ስርዝ ድልዝ** ስ ፅሁፍ እንዳይነበብ ለማድረግ ሲባል በፅሁፉ ላይ በተደጋጋሚ የተሰመረ መስመር እንዲሁም የነበረው ቃል ተፍቆ በሌላ ቃል የተተካ ፅሁፍ።

**ተሰረዘ** ግ 1.በፅሁፉ ላይ ተሰመረ፥ እንዳይነበብ ተደረገ፥ ጠፋ። 2. እንዲወጣ ተደረገ። *ከአባልነት ተሰረዘ።* 3. እንዲቀር ተደረገ፥ ተተወ። *የዛሬው የእግር ኳስ ጨዋታ ተሰርዟል።*

***ሰረየ**

**ስርየት** ስ ምህረት፥ ይቅርታ (የሃጢአት)።

**ተሰረየ** ግ ይቅርታ ተደረገ፥ ተተወ። *ሃጢአቱ ተሰረየለት።*

**አስተሰረየ** ግ ይቅርታ ወይም ምህረት አደረገ (ፈጣሪ)።

**ሰረገ**[1] ግ ደግሶ ዳረ።

**ሰርግ** ስ 1. የጋብቻን በአል ለማክበር የሚደረግ ድግስና የአከባበሩ ስነ ስርአት። 2. (ዘይ.) ደስታ።

**ሰርግና ምላሽ** ደስታ፥ ፈንጠዝያ።

**ሰርግ ቤት** ስ የሰርግ ድግስ የተደረገበት ቤት።

**የሰርግ ዘፈን** ስ ለሰርግ የሚዘፈን ዘፈን።

**ሰርገኛ** ስ የሙሽራውና የሙሽራዋ አጃቢ፥ እድምተኛ፥ ታዳሚዎች።

**ሰርገኛ [ጤፍ]** ስ ነጭና ቀይ የተቀላቀለበት ጤፍ።

**ተሰረገ** ግ 1. የሰርግ ድግስ ተዘጋጀ። 2. በሰርግ ተዳረ፥ አገባ።

**ሰረገ**[2] ግ 1. ወደ ውስጥ ገባ፥ ዘለቀ፥ ሰመጠ። 2. ኅደጎደ (አይን)።


**ስርጎ ገብ** ስ ለመሰለል፥ ለመምታት ወይም አደጋ ለማድረስ ማንነቱን ደብቆ ከጠላት ድርጅት፥ ሰፈር፥ አገር፥... የሚገባ ሰው።

**ተሰረገረገ** ግ ሰመጠ፥ ወደውስጥ ገባ፥ ተዋጠ።

**አሰረገ** ግ 1. አሰመጠ፥ ዋጠ። 2. ወደ ውስጥ አገባ፥ ወደ ውስጥ ወስዶ አስቀረ። 3. አከሰረ፥ አስጨረሰ፥ አቀለጠ (ገንዘብን)።

**አስርግ** ግ አክስር፥ አቅልጥ።

**ሰረገላ** ስ 1. ለመጓጓዣ የሚያገለግል በእንስሳት (በተለይ በፈረስ) የሚሳብ ጋሪ። 2. በድምድማት ላይ መሃል ለመሃል የሚጋደም ወፍራም እንጨት፥ ብረት፥ ግንዲላ።



ሰረገላ 1ኛ ፍቺ

**ሰረገላ ቁልፍ** ስ ባለዘንግ መክፈቻ ቁልፍ።(ስእሉን ቁልፍ ስር ተመ.)

**ሰረገበ** ግ ጠጣ፥ ጨለጠ።

**ሰረጎደ** ግ በመሰበር፥ በማጨራመት፥...አጎደጎደ።

**ስርጉድ** ቅ ጎድጓዳ፥ የተሰረጎደ።

**ስርጉዳት** ስ የጎደጎደ ቦታ።

**ተሰረጎደ** ግ በመሰበር፥ በመጨራመት፥ በመሟሸሽ ጎደጎደ።

***ሰረጨ**

**ስርጭት** ስ በተለያዩ ቦታዎች የመድረስ፥ የመዳረስ ወይም የማዳረስ ሁኔታ፥ ተግባር።

**ተሰራጨ** ግ ተራባ፥ ብዙ ቦታ ተዳረሰ፥ ተስፋፋ።

**አሰራጨ** ግ 1. አራባ፥ ብዙ ቦታ አዳረሰ። 2. አከፋፈለ፥ በተነ። 3. አስተላለፈ (ዜናን በሬዲዮ፥ በጋዜጣ፥...)።

**ሰረፀ** ግ 1. በቀለ፥ ወጣ፥ ለመለመ። 2. ዘለቀ፥ ገባ። *ትምህርቱ ሰርፆታል።*

**ሰራፂ** ቅ የተገኘ፥ የወጣ።

**አሰረፀ** ግ 1. አስገኘ። 2. (በአእምሮ) ዘልቆ እንዲገባ፥ እንዲቀረፅ አደረገ።

***ሰረፋ**

**ተንሰራፋ** ግ ተስፋፋ፥ ተደላደለ፥ ብዙ ስፍራ ያዘ።

**አንሰራፋ** ግ አስፋፋ፥ አደላደለ፥ ብዙ ስፍራ አስያዘ።

**ሰረሳራ** ስ በግንባር ግራና ቀኝ ከጉንጭ በላይ ያለ የሰውነት ክፍል(ሰእሉን ራስ ስር ተመ.)።

**ሰሬቲ(ሰሬቴ)** ስ አንጓ ያለውና እሾሃም የሆነ የእፅዋት አይነት፤ ቀስተንቻ።

**ሰራ**[1] ግ 1. አደረገ፥ ፈፀመ፥ አከናወነ፥ አዘጋጀ። 2. አቋቋመ፥ አበጀ፥ ገነባ፥ አስገነባ። *ትምህርት ቤት ሰራ።* 3. ተበላሽቶ የነበረውን አስተካከለ፥ አበጀ፥ ጠገነ። 4. ፈጠረ፥ ፈለሰፈ። *ላውሮፕላንን መጀመሪያ የሰሩት ሁለት ወንድማማቾች ናቸው።* 5. ተግባሩን በትክክል ማከናወን ጀመረ፥ አከናወነ። *ሰዓቱ ይሰራል።*

**__ሰሪት** በ__አገር የተሰራ። *ጃፓን ሰራት የሆነ መኪና።*

**የሰራ አካላት** መላ ሰውነት። *የሰራ ላካላቴን ላምኛል።*

**ሰራለት** መጥፎ ድርጊት ፈፀመበት።

**ሲሰራት የዋለ** በጣም ቆንጆ የሆነች።

**ሰርቶ አደር** ስ በማንኛውም የስራ መስክ ተሰማርቶ በሚያገኘው ገቢ የሚተዳደር ሰው።

**መስሪያ ቤት** ስ ማንኛውም የመንግስት ወይም የግል፥ የድርጅት ስራዎች የሚካሄዱበት፥ አመራር የሚሰጥበት ቦታ ወይም ቤት።

**መሳሪያ** ስ 1. አንድን ነገር ለመስራት፥ ለማምረት አጋዥ ሆኖ የሚያገለግል ማንኛውም እቃ። 2. የጦር መሳሪያ።

**መሳሪያ መዘዘ** ለማስፈራራት፥ ለመግደል፥... ጠበንጃ፥ ሽጉጥ አወጣ።

**ሰራተኛ** ስ 1. በተወሰነ የስራ መስክ ተሰማርቶ የሚያገለግል ሰው። ቅ 2. በስራው ላይ ብርቱ፥ ታታሪና ትጉህ የሆነ።

**የሰራተኛ ማህበር** ስ ሰራተኞች መብታቸውን ለማስከበር የሚያቋቁሙት ማህበር።

**__ሰሪ** ስራው __ን መስራት፥ ማበጀት የሆነ ወይም--ን በመስራት ላይ ያለ። *ፀጉር ሰሪ/ ቤት ሰሪ...።*

**ስራ** ስ 1. የአእምሮ ማሰላሰልንም ሆነ የጉልበት እንቅስቃሴን የሚሻና መደረግ፥ መፈፀም ያለበት ነገር፥ ተግባር። 2. አንድን ውጤት ለማስገኘት የሚደረግ የአእምሮ ማሰላሰልና የጉልበት እንቅስቃሴ፥ ክንዋኔ። 3. አገልግሎት፥ ጥቅም፥ ተግባር። ቅ 4. በአል ያልሆነ፥ የአዘቦት (ቀን)። *ዛሬ ስራ ነው፣ በአል ላይደለም።*

**ስራ ለወጠ** ወደሌላ መስሪያ ቤት ተዛወረ ወይም ሌላ ስራ ያዘ፤ ስራ ቀየረ።

**ስራ ያዘ** 1. በስራ ላይ ሆነ፥ በስራ ተጠመደ። 2. በአንድ አይነት ስራ ላይ ተሰማራ፥ ተቀጠረ፥ ተመደበ።

**ስራ ፈታ** 1. ሲሰራ የነበረውን ስራ አቆመ፥ ቦዘነ። 2. ስራ አጣ።

**ስራ ፈት** ቅ 1. ስራ አጥ፤ ስራ የሌለው። 2. ስራውን ትቶ በማይረባ ነገር ጊዜውን የሚያሳልፍ፤ ቦዘኔ።

**ስራ ማስኬጃ** ስ በአንድ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት፥ ...ውስጥ ለስራ ማከናወኛ የሚውል ገንዘብ።

**ስራ አስኪያጅ** ስ የአንድ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ስራ መሪ፥ ሃላፊ።

**ስራ አጥ** ቅ የመስራት ችሎታ እያለው ስራ የሌለው ወይም ስራ ያላገኘ፥ ያልተቀጠረ (ሰው)።

**ስራ አፈፃፀም** ስ ሰራተኛ ስራውን የሚያካሂድበት፥ የሚፈፅምበት ሁኔታ ወይም ብቃት።

**[የ]ስራ አፈፃፀም ቅፅ** ስ በመንግስት መስሪያ ቤት የሰራተኞች የስራ አፈፃፀም ግምገማ ውጤት በተቆጣጣሪው የሚመዘገብበት ቅፅ።

**የስራ ልምድ** ስ በአንድ የስራ መስክ ከስራው ሂደት የተገኘ እውቀት፥ ችሎታ።

**የስራ ሰአት** ስ እንደየመስሪያ ቤቱ ሁኔታ ሰራተኛ በስራ ገበታው ላይ የሚሆንበት፥ ስራ የሚሰራበት መደበኛው ጊዜ።

**የስራ ሰው** ስራ ወዳድ፥ ማጋጣ ያልሆነ።

**የስራ ቀን** ስ እንደየመስሪያ ቤቱ ሁኔታ መደበኛ ስራ የሚሰራበት፥ በአል ወይም እረፍት ያልሆነ ቀን።

**የስራ ቋንቋ** ስ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች የሚገለገሉበት ቋንቋ።

**የስራ ዝርዝር** ስ አንድ የስራ ክፍል፥ ሰራተኛ፥... እንዲያከናውናቸው በቅደም ተከተል የተመለከቱና የተመዘገቡ የስራ አይነቶች።

**ስር** ስ 1. የተሰራ፤ የተበጀ፥ የተመረተ፥ የተዘጋጀ። 2.የተሰራ፥ የተጎነጎነ(ፀጉር)።

**ተሰራ** ግ 1. ተደረገ፥ ተፈፀመ፥ ሆነ፥ ተከናወነ። 2. ተቋቋመ፥ ተበጀ፥ ተገነባ። 3.ተፈጠረ፥ ተፈለሰፈ፥ ተመረተ። 4. ተበላሽቶ የነበረው ተስተካከለ፥ ተበጀ።

**አሰራ** ግ 1.አቋቋመ፥ መሰረተ፥ አዘጋጀ፥ እንዲሰራ አደረገ። 2. አስጠገነ፤ የተበላሸው እንዲበጅ ወይም እንዲስተካከል አደረገ።

**አሰሪ** ስ 1. ስራን በበላይነት እየተቆጣጠረ የሚያሰራ ሃላፊ። 2. ሰራተኛን ቀጥሮ የሚያሰራ ድርጅት ወይም የድርጅት ባለቤት።

**አሰራር** ስ 1.የአበጃጀት፥ የአደራረግ፥ የአዘገጃጀት መንገድ ወይም ሁኔታ። 2.አንድ መሳሪያ የሚንቀሳቀስበት ስርአት ወይም ሁኔታ።

*የኣ፪ደሉ ምተር ኣሰራር ኣይገባኝም።*

**ሰራ**[2] ግ 1. ወሰነ፥ ደነገገ፥ ደነባ፥ ህግ ኣወጣ። 2. ሰበሰበ፥ ኣሰለፈ (ጦርን)። 3. መራ፥ ኣሰፈረ (የጦር ሰራዊትን)።

**ስሪት** ስ 1.ደንብ፥ ስርኣት፥ ህግ። 2. የመሬት ይዞታ ደንብ፥ ስርኣት፤ የመሬት ስሪትም ይባላል።

**ስር** ስ ደንብ፥ ህግ፥ ስርኣት።

**ተሰራ** ግ 1. ተደነገገ፥ ደንብ ወጣ። 2.ተመራ፥ ሰፍራ ያዘ፥ ተመደበ። *በኣገራችን ወታደር ተሰርቷል።*

**ተሰሪ** ስ በቀድሞው ጊዜ በገባር ቤት ተመድቦ፥ ተመርቶ የሚቀመጥ ወታደር።

**ሰራተኛ** "ሰራ[1]" ስር ተመ.

**ሰራን** ስ ነጭና ጠቆር ያለ ቀለም ያለው ዝንጉርጉር ፈረስ።

**ሰራዊት** ስ 1. በወታደራዊ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ኣባላት በሙሉ። 2. ለኣንድ ኣላማ በኣንድ ቡድን ስር የተሰባሰበ ብዙ ህዝብ።

**ሰርሳሪ** "ሰረሰረ" ስር ተመ.

**ሰርብ** "ሰረበ[2]" ስር ተመ.

**ሰርተፊኬት** ስ የምስክር ወረቀት።

**ሰርን** ስ የኣፍንጫ ቦይ።

**ሰርክ** ስ 1. የቀን መጨረሻ፥ ምሽት። 2.ዘወትር፥ ሁልጊዜ።

**የሰርክ ልብስ** ስ የዘወትር ልብስ።

**ሰርዲን** ስ ለምግብነት የሚሆኑ የትናንሽ ኣሳዎች ዘር፤ ከዚሁ የተዘጋጀና በቆርቆሮ የታሸገ ምግብም ሰርዲን ይባላል።

**ሰርዶ** ስ ብዙ ኣንጓ ያለው፥ መሬት ለመሬት ስር እየሰደደ የሚሳብ የሳር ኣይነት።

**ሰርገኛ** "ሰረገ[1]" ስር ተመ.

**ሰርግ** ዝ.ከ.

**ሰርጥ(ስርጥ)** ስ ቀጭን፥ ጠባብ የእግር መንገድ።

**ሰርፍ** ስ 1. ባለዘርፍ የኣልጋ ልብስ፥ ምንጣፍ። 2. የሬሳ ሳጥን የሚለብሰው ምንጣፍ፥ መጎናፀፊያ።

**ሰሰነ** "ሴሰነ" ን ተመ.

**ሰሳ (ሰስ)** ስ ኑሮው በገደላገደልና በተራራ የሆነ፥ ፍየል የሚመስል፥ ስጋው የሚበላ ትንሽ የዱር እንስሳ (ሰእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ሰቀለ** ግ 1.ኣነሳ፥ ከፍ ኣደረገ፥ ወደላይ ኣራቀ። 2. ኣንጠለጠለ። 3. በመስቀል ላይ በመቸንከር ወይም ኣንገቱን በገመድ በማንጠልጠል ገደለ።

**መስቀያ** ስ ከእንጨት ወይም ከሽቦ ወይም ከፕላስቲክ፥... የተሰራ የልብስ ማንጠልጠያ፤ የልብስ መስቀያም ይባላል።

**መስቀል** ስ 1. ቀጥ ባለ እንጨት ኣናት ኣካባቢ ሌላ ኣጠር ያለ እንጨት በማጋደምና ሁለቱን በማያያዝ የሚዘጋጅ፥ በጥንት እስራኤላውያንና ሮማውያን ጊዜ ወንጀለኞችን ኣሰቃይቶ ለመግደል ያገለግል የነበረ የሰው መስቀያ።2. ከላይ በተጠቀሰው ቅርፅ ከብረት፥ ከእንጨት፥... የሚዘጋጅ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ምሳሌ፤ የክርስትና እምነት ተከታዮች ምልክት። 3. በመስቀል መልክ የተሰራ ማንኛውም ኣይነት ምልክት። 4. የክርስቶስ መስቀል ከተቀበረበት ቦታ መገኘቱን ምክንያት በማድረግ መስከረም 17 ቀን የሚከበር በኣል። 5. የመስቀል ምልክት የሚደረግበት ወይም ማማተቢያ ጣት የሚያርፍበትና በኣፍንጫ ትክክል የሚገኘው የግንባር ክፍል።

**መስቀለኛ(መስቀልኛ)** ቅ እንደ መስቀል ያለ።

**መስቀለኛ መንገድ** ስ በመስቀል ቅርፅ ወደተለያየ ኣቅጣጫ የተከፋፈለ መንገድ፥ መስመር።

**መስቀለኛ ጥያቄ** ስ ኣንድ ሰው የሰጠውን ቃል ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከተቃራኒው ወገን በተለያየ መንገድ የሚቀርብ ጥያቄ።

**የመስቀል ወፍ** ስ 1. በመስከረም ወር የመስቀል በኣል በሚከበርበት ሰሞን የምትታይ ኣነስተኛ ወፍ (ሰእሉን ወፍ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) ኣልፎ ኣልፎ ብቻ የሚታይ ሰው። *ምነው የመስቀል ወፍ ሆንክ?*

**ሰቀላ** ስ ኣግድምና ሞለል ብሎ የተሰራ ትልቅ ቤት፥ ዳስ፥ ድንኳን።

**የሰቀላ መሬት** ስ ርስት ያልሆነ፥ በቀድሞ ጊዜ ኣንድ ሰው ሲሾም ለመተዳደሪያ እንዲሆን የሚሰጠው መሬት።

**ስቅለት** ስ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን እለት ምክንያት በማድረግ በየኣመቱ ከፋሲካ በፊት ባለው ኣርብ ቀን የሚከበር በኣል።

**ስቅላት** ስ ሰው ኣንገት ላይ ገመድ፥ ሸምቀቆ በማጥለቅና በማንጠልጠል የሚፈፀም የሞት ቅጣት።

**ተሰቀለ** ግ 1. ተንጠለጠለ፥ ወደላይ ከፍ ኣለ። 2. በገመድ ተንጠልጥሎ ሞተ።

**ኣሳቀለ** ግ 1. ነገርን፥ ጥልን ኣባባሰ፥ ኣጋነነ። 2. ኣዋደደ(ዋጋን)። 3. ኣሳጣ፥ በደሉን ነገረ (ለበላይ፥ ለፈጣሪ፥...)።

**ሰቀሰቀ** ግ ኣንድን ነገር ጨርሶ ለማንሳት ከስሩ ገብቶ ፈቀፈቀ፥ ሰረሰረ፥ ፈቀፈቀ፥ ጠረገ።

**ሰቀሰቀበት** በጦር ወይም በጩቤ ወጋው።

**መሰቅሰቂያ(መሰቅሰቂት)** ስ ከምጣድ ላይ እንጀራ ማላቀቂያ ስንጥር እንጨት።

***ሰቀሰቀ**

**ስቅስቅ አለ** ግ ምርር ብሎ አለቀሰ።

**ተንሰቀሰቀ** ግ ምርር ብሎ አለቀሰ፤ አነባ።

**ሰቀቀ**[1] ግ ሰቀጠጠ፤ ዘገነነ።

**ሰቀቀን** ስ 1. ተስፋ ያደረጉበትን ወይም ያሰቡትን በማጣት የሚሰማ የቅሬታ ስሜት፤ ሃዘን። 2. ናፍቆት።

**ሰቀቀናም** ቅ ችጋራም፤ ስግብግብ፤ ስስታም።

**ተሰቀቀ** ግ በፍርሃት ወይም በስጋት ተሸማቀቀ፤ ተሳቀየ፤ ተጨነቀ።

**ተሳቀቀ** ግ 1. በፍርሃት ወይም በስጋት ተጨነቀ፤ ተሸማቀቀ። 2. ተስፋ ያደረገበትን፤ ያሰበውን አጣ።

**አሰቃቂ** ቅ በጣም አስከፊ፤ ዘግናኝ፤ አሳዛኝ፤ ሰቅጣጭ።

**አሳቀቀ** ግ 1. በፍርሃት፤ በስጋት አሰቃየ፤ አስጨነቀ። 2. አሳይቶ፤ አጓጉቶ ነሳ፤ ከለከለ።

**ሰቀቀ**[2] ግ መጠቀ፤ ወደላይ ከፍ እያለ ራቀ፤ ሄደ።

**ሰቀቀናም** "ሰቀቀ[1]" ስር ተመ.

**ሰቀቀን** ዝ.ከ.

**ሰቀዘ** ግ ወጋ፤ ቀስፎ ያዘ፤ አስጨነቀ(ህመም)።

***ሰቀየ**

**ስቃይ** ስ በአካል ወይም በአእምሮ ላይ የሚደርስ ጭንቀት፤ መከራ፤ ህመም፤ ጉስቁልና።

**ተሰቃየ** ግ በህመም፤ በጉዳት፤ በጭንቀት፤ መከራ አየ፤ ስቃይ ተቀበለ።

**አሰቃየ** ግ አጎሳቆለ፤ በህመም ወይም በጉዳት መከራ አሳየ፤ ስቃይ አደረሰ።

**ሰቀጠ** ግ ዋሸ፤ አታለለ።

**ሰቃጢ** ቅ ውሸታም፤ አታላይ።

**ሰቀጠጠ** ግ ዘገነነ።

**ሰቅጣጭ** ቅ የሚዘገንን።

**ሰቃጢ** "ሰቀጠ" ስር ተመ.

**ሰቅ** ስ 1. መታጠቂያ፤ ቀበቶ። 2. ማቅ፤ በርኖስ።

**ሰቆረ** ግ በሳ፤ ሸነቆረ፤ ነደለ።

**መስቆር** ስ መብሻ፤ መሸንቆሪያ፤ ሹል ነገር።

**መስቆርት** ስ የጆሮ መብሻ።

**ሰቆቃ (ሰቆቃው)** ስ ጩሀት፤ ዋይታ፤ የመረረ ለቅሶ፤ ሙሾ።

**ሰበረ** ግ 1. አነከተ፤ ቀለጠመ፤ አደቀቀ፤ ሸረፈ። 2. ተበላሸ፤ ልክ አልመጣ አለ(ለዜማ፤ ለግጥም)። 3. ጥሶ አለፈ። 4. ሰርስሮ ወይም በህገ ወጥ መንገድ ከፍቶ ገባ (ቤትን)። 5.ሰነከለ፤ አጎበጠ፤ አደቀቀ(በሽታ)። 6. አጨደ፤ ቆረጠ። *ባቄላ ሰበረ።*

**ሰበር ሰካ አለ** የቄንጥ አካሄድ ሄደ።

**ሰበር** ስ በአሂዶ ጊዜ የከብቶች እግር ያደቀቀው የስንዴ፤ የገብስ፤... አገዳ።

**ሰበር** ስ አንድ ጉዳይ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ካገኘ በኋላ፤ መሰረታዊ የፍርድ ስህተት ሲኖረውና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሲታዘዝ፤ወይም በጠቅላይ አቃቤ ህጉ አቤቱታ ሲቀርብበት እንደገና የሚታይበት ሁኔታ።

**ሰባራ** ቅ 1. ጉድለት ያለው፤ የተበላሸ፤ በትክክል የማይሰራ። 2. የአካል ስብራት ያለበት (ሰው)። 3. የተሸረፈ፤ በከፊል የተሰበረ። 4.ሰባሪ፤ ሽራፊ።

**ሰባራ ሰንጣራ** ስ አነስተኛ፤ ጥቃቅን፤ መናኛ የቤት እቃ።

**ሰባሪ** ቅ ሽራፊ፤ ቁራጭ፤ ጉማጅ።

**ስብራት** ስ 1. የመሰበር አደጋ። 2. የአጥንት መሰበር።

**ሰባበረ** ግ አደከመ፤ አደቀቀ (ሰውነትን)።

**ስብርባሪ** ቅ ቁርጥራጭ፤ ድቃቂ።

**ስብርብር ያለ** ያልተስተካከለ። *ስብርብር ያለ አረፍተ ነገር።*

**ተሰበረ** ግ 1. ነከተ፤ ደቀቀ፤ ተሰነጠቀ። 2. ስብራት ደረሰበት።

**ተሰባሪ** ቅ 1. በቀላሉ ሊሰበር የሚችል። 2.(ዘይ.) ሚች። *ሰው ተሰባሪ ነው።*

**ተሰባበረ** ግ አንድን ነገር ለማግኘት ተጣጣረ፤ ታገለ፤ ተራኮተ።

**አሳበረ** ግ በአቋራጭ መንገድ ሄደ።

**ሰበሰበ** ግ 1. ለቀመ፤ አጋበሰ፤ ወደራሱ አደረገ። 2. አከማቸ፤ በአንድ አደረገ። 3. አጠፈ፤ ኮረተመ፤ መለሰ። *እግሩን ሰበሰበ።* 4. በስሩ አድርጎ አስተዳደረ፤ አኖረ (ዘመድን፤ ቤተሰብን)። 5. አጨደ፤ አስገባ፤ ከተተ(ሰብልን)። 6. ጠቅልሎ ወይም አጥፎ እንዳይንዘረፈፍ አደረገ(ልብስን፤...)። 7. ለጉባኤ ወይም ለውይይት ሰዎችን፤ ተሳታፊዎችን ጠራ፤ በአንድ አደረገ፤ ስብሰባውን መራ።

**ሰበሰብ (ስብሳብ)** ስ በቤት ዙሪያ በስተውጭው በኩል ያለ ቦታ፤ ታዛ።

**ሰብሳቢ** ቅ 1. የሚያኖር፤ የሚያስጠጋ፤ ረዳት። ስ 2. የስብሰባ መሪ፤ ሊቀመንበር።

**ሰብሳባ (ስብስብ)** ቅ ቆጣባ፤ የተቀጣ፤ ጨዋ።

**ስብሰባ** ስ ለአንድ አይነት ጉዳይ፤ ለውይይት፤ ...የሰዎች በአንድነት መገኘት፤ ጉባኤ።

**ስብሰባ ረግጦ ወጣ** በስብሰባው አጀንዳ

ወይም በተዘረዘሩት ሃሳቦች ባለመስማማት ስበሰባውን ያለፈቃድ አቋርጦ ወጣ።

**ስብሰባ ጠራ** ጉባኤ ጠራ፣ ለውይይት ሰዎችን በተወሰነ ቦታና ሰአት እንዲገኙ አደረገ።

**ስብሰባውን ከፈተ** ጉባኤውን ንግግር በማድረግ፥... ጀመረ።

**ስብስብ** ቅ ጥርቅም።

**ተሰበሰበ** ግ 1. ተለቀመ። 2. ተጠራቀመ፣ በአንድ ላይ ሆነ። 3. ተሸበሸበ። 4. በስብሰባ ላይ ተገኘ። 5. አርፎ፥ ተቆጥቦ ተቀመጠ። 6. ረዝሞ የነበረው ክትት አለ፥ ቅልብጭ አለ።

**መሰብሰቢያ** ስ መገናኛ ቦታ ወይም አዳራሽ።

**ተሰባሰበ** ግ ከያለበት መጣ፥በአንድ ላይ ሆነ፥ ተሰበሰበ።

**አሰባሰበ** ግ 1. በአንድ ላይ አደረገ፥ ከያለበት ሰበሰበ።2. ከሰዎች ሰበሰበ (መዋጮን)።

**ሰበቀ**[1] ግ 1. አማሰለ፥ በጠበጠ (እርጎን፥...)። 2. ወዘወዘ፥ ነቀነቀ(ጦርን)። 3. እሳትን ለማውጣት በመዳፎቹ መካከል እንጨትን፥ አስቴን አሽከረከረ፥ አሸ (ቀጠን ያለውን እንጨት ወፈር ካለው ላይ በማድረግ)።

**መስበቂያ** ስ ሶስት ጣት ያለው ማማሰያ፣ መበጥበጫ እንጨት።



መስበቂያ

**ሰበቃ** ስ ሁለት ነገሮችን የማፋጨት፥ የማፋተግ ሁኔታ፥ ስራ ወይም የሁለት ነገሮች መፋተግ፥ መፋጨት።

**ሰበቀ**[2] ግ የሚያጣላ፥ የሚያጋጭ ወሬን አቀበለ፣ አሳጣ።

**ሰባቂ** ቅ የሚያጣላ ወሬን አቀባይ፣ ወሬን እያቀበለ የሚያጣላ።

**ሰብቅ** ስ ሰዎችን ለማጣላት ከአንዱ ወደ ሌላው ተወስዶ የሚነገር ክፉ ወሬ።

**ሰብቀኛ** ስ ሰብቅ የሚወድ፥ ወሬ አቀባይ።

**ስብቀት** ስ ሰብቅ።

**አሳበቀ** ግ የሚያጣላ ክፉ ወሬ አቀበለ፣ ሰበቀ።

**አሳባቂ** ቅ የሚያጣላ ወሬን የሚያቀብል፣ ወሬኛ።

**ሰበቀለ** ግ ቆነጀ፣ ተዋበ፣ አማረ።

**ስብቅል** ቅ ቆንጆ፥ ውብ፣ የሚያምር።

***ሰበቀለ**

**ስብቅል** ቅ የተመሰቃቀለ።

**ተሰባቀለ** ግ ተመሳቀለ።

**አሰባቀለ** ግ አመሳቀለ።

**ሰበቃ** "ሰበቀ[1]" ስር ተመ.

***ሰበበ**

**ሰበብ(ሰበብ)** ስ ምክንያት (ብዙውን ጊዜ ማስተባበያ የሚሆን፣ ዋነኛ ምክንያት ያልሆነ)።

**ሰበብ አስባብ** ስ የሆነ ያልሆነ ወይም በቂ ያልሆነ ምክንያት።

**ሰበበኛ(ሰበበኛ)** ቅ 1. ጥቂት ምክንያት፣ ሰበብ የሚፈልግ። 2. ደካማ፣ አቅመቢስ።

**ተሳበበ** ግ ተመካኘ።

**አሳበበ** ግ አመካኘ።

**ሰበከ** ግ 1. አስተማረ ሃይማኖት ወይም እምነትን። 2. አግባባ፣ አታለለ፣ አባበለ። 3. ኢ.ኦ.ተ.ቤ. ቄሱ ወንጌል ከማንበቡ በፊት ዲያቆኑ ከዳዊት መዝሙር አዜመ

**ምስባክ(ምስማክ)** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በፍታት፣ በቅዳሴ ወይም በበሎት ጊዜ ወንጌል ከመነበቡ በፊት ዲያቆን ከዳዊት መዝሙር ውስጥ መርጦ የሚያዜመው ሶስት ስንኝ ያለው ጥቅስ። 2. ወንጌልን ማስተማሪያ፣ አዋጅን መንገሪያ ከፍ ያለ ቦታ ወይም መድረክ።

**ሰበካ** ስ አጥቢያ፣ ቀበሌ፣ አካባቢ፣ ዙሪያ (የቤተክርስቲያን)።

**ሰባኪ** ስ 1. ሃይማኖት አስተማሪ። ቅ 2.ሽንጋይ፣ ደላይ።

**ስብከት** ስ 1. ሃይማኖት ትምህርት፣ ህዝብ በተሰበሰበበት የሚሰጥ ወይም የሚነገር የሃይማኖት ቃል። 2.ለማግባባት፣ ለማባበል የሚነገር የመደለያ ወይም የመሸንገያ ቃል።

**ተሰበከ** ግ 1. የተሰጠውን የሃይማኖት፥ የርእዮተ አለም ትምህርት ተቀበለ። 2. ተታለለ፥ ተሞኘ፣ ተደለለ።

**ሰበከት** ስ የእንጀራ ወይም የቁርበት ጀርባ፤ እንጀራው ምጣድ ላይ ወይም ቁርበቱ መሬት ላይ የሚያርፍበት ወገን።

**ሰበካ** "ሰበከ" ስር ተመ.

**ሰበዘ** ግ ሰበዝን ሻጠ፥ ሸጎጠ።

**ሰበዘበት** ሻጠበት (ጦርን፣...)።

**ሰበዝ** ስ የተሰነጠቀ ስንደዶና አክርማ በላዩ ላይ እየተጠመጠመበት የሚሰፋና የሚያያዝ ያልተሰነጠቀ ስንደዶ፥ የስፌት ሳር፣ ሳሩም ሰበዝ ይባላል።

***ሰበደበደ**

**ሰበድባዳ(ስብድብድ)** ቅ ፈሪ፣ ቡቡ፣ ተርበድባጅ።

**ተሰበደበደ** ግ ፈራ፣ ባባ፣ ተርበደበደ።

**ሰበጠረ(ሰባጠረ)** ግ አወሳሰበ፣ አጠላለፈ።

**ሰበጢራ(ሰበጠራ)** ስ ከቀርከሃ፥ ከማሽላ አገዳ፣ ከሸምበቆና ከመሳሰሉት የሚሰራ የእንጀራ ቅርጫት ወይም ሰፌድ።

**ስብጥር** ቅ 1. ውስብስብ፣ ጥልፍልፍ። 2.ከየአይነቱ የተቀላቀለ፣ ቅልቅል የሆነ።

**ተሰባጠረ** ግ 1. ተጠላለፈ፥ ተወሳሰበ። 2.አልፎ አልፎ ጣልቃ ገባ፣ ተደባለቀ።

**አሰባጠረ** ግ 1. አስተላለፈ፣ አጠላለፈ፥ አወሳሰበ። 2. አልፎ አልፎ አስቀመጠ፥ ጣልቃ አስገባ።

**ሰባ** ስ 1. በስድሳ ዘጠኝና በሰባ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ። በአሃዝ ሲፃፍ ፸ ፥ 70 ነው። ቅ 2. ብዛቱ ሰባት አስሮችን የሆነ። *ሰባ ከብቶች።*

**ሰባ** ግ 1. ወፈረ፣ ደለበ፥ ጮማ ሆነ (እንስሳ)። 2. ለማ፥ ዳበረ (መሬት)።

**የሰባ መሬት** ስ ለም የሆነ መሬት ወይም አፈር።

**ስብ** ስ 1. ጮማ። ቅ 2. ለም፣ የዳበረ (መሬት)። 3. ወፍራም፣ ደንዳና (ለእንስሳት)።

**ስባት** ስ ውፍረት፣ ጮማነት (የእንስሳ)።

**አሰባ** ግ አወፈረ፥ አደነደነ፥ አደለበ።

**አስብቶ አራጅ** ወዳጅ መስሎ፥ አዘናግቶ አጥፊ ወይም አድፍጦ፥ አድብቶ የሚጎዳ።

**ሰባራ** "ሰበረ" ስር ተመ.

**ሰባሰገል** "ሰብአሰገል" ን ተመ.

**ሰባቂ** "ሰበቀ[2]" ስር ተመ.

**ሰባት** ስ 1.በስድስትና በስምንት መካከል ያለ ቁጥር። በአሃዝ ሲፃፍ ፯ ፥ 7 ነው። ቅ 2. ብዛቱ የአንድና የስድስት ድምር የሆነ። *ሰባት መፅሃፎች።*

**ሰባኪ** "ሰበከ" ስር ተመ.

**ሰባጠረ** "ሰበጠረ" ን ተመ.

**ሰብል** ስ እህል፥ የእርሻ ስራ ውጤት።

**የሰብል ጊዜ** ስ አዝመራ፣ እህል የሚሰበሰብበት ወቅት።

**ሰብራዳ** ስ ከጭቅና ጋር ያለ ሁለት የበሬ ጎድን።

**ሰብሳቢ** "ሰበሰበ" ስር ተመ.

**ሰብሳባ** ዝ.ክ.

**ሰብቀኛ** "ሰበቀ[2]" ስር ተመ.

**ሰብቅ** ዝ.ክ.

**ሰብአ ሰገል (ሰባሰገል)** ስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ኮከብ እየመራቸው ከምስራቅ መጥተው እጅ መንሻ (ወርቅ፣ ከርቤ፣ እጣን) በማቅረብ የሰገዱለት ሰዎች መጠሪያ።

**ሰብአ አይን** "ሰብእ" ስር ተመ.

**ሰብአዊ** ዝ.ክ.

**ሰብእ (ሰብ)**

**ሰብአ አይን** ስ ሰላይ።

**ሰብአዊ** ቅ 1.የሰው ልጅ ሊያደርገው ወይም ሊሆን የሚገባው። 2. የሰው፥ የሰው ልጅ። *ሰብአዊ ባህርይ፥ አካል፥...።*

**ሰብአዊ መብት** ስ ሰው በሰውነቱ ሊደረግለት የሚገባ እንክብካቤ፥ ሊሰጠው የሚገባ ነፃነት።

**ሰብአዊ መብት ረገጣ** ስ ሰብአዊ መብትን መንፈግ፥ የመከልከል አድራጎት፣ በሰብአዊ ክብር ላይ የሚደረግ ጭቆና፥ ግፍ።

**ሰብአዊ ርህራሄ** ስ ለሰው ልጅ የሚደረግ ሃዘኔታ፥ በጎ ተግባር።

**ሰብአዊ ርዳታ** ስ የእለት ደራሽ የሆነ እንደ ምግብ፥ መጠለያ፥ መድሃኒት የመሳሰለ እርዳታ።

**ኢሰብአዊ** ቅ ጭካኔ፥ አረመኔነት የተሞላበት፥ በሰው ልጅ ላይ መደረግ የማይገባው።

**ሰተረ[1]** ግ አሰጣ፥ ዘረጋ፥ ለፀሃይ ሰጠ።

**ሰተረ[2]** ግ ሸከፈ፥ ሰበሰበ፥ በስርአት አስቀመጠ (እቃን)።

**ተሰተረ** ግ ተሸከፈ፥ ተሰበሰበ፥ በስርአት እንዲቀመጥ ተደረገ።

***ሰተተ**

**ሰተቶ** ስ ያለ ጋብቻ ውል ወይም ፊርማ ሴት ቤት ገብቶ የሚኖር (ወንድ)።

**ስታታ** ቅ 1. ወጣ ገባነት የሌለው፥ ለጥ ያለ (ሜዳ)። 2. ገላጣ፥ ዝርግ።

**ስታቴ** ስ ትልቅና ሰፊ የሆነ የሸክላ ድስት።

**ሰተት አለ** ግ ያለችግር፥ ያለመሰናከል ወደ ውስጥ ገባ።

***ሰተፈ**

**ተሳተፈ** ግ የአንድ ስራ ተካፋይ ሆነ፥ የበኩሉን አስተዋፅኦ አደረገ፥ ድርሻውን አበረከተ፥ ተጋራ።

**ተሳታፊ** ቅ የአንድ ድርጊት ተካፋይ።

**ተሳትፎ** ስ በአንድ ስራ የመተባበር ወይም የመሳተፍ ተግባር።

**አሳተፈ** ግ በአንድ ስራ እንዲተባበር ወይም እንዲሳተፍ አደረገ።

***ሰነሰለ**

**ሰንሰለት** ስ እርስ በርስ ከተቆላለፉ ወይም ከተያያዙ ቀለበቶች የተበጀ ለማሰሪያነት የሚያገለግል የብረት ገመድ።

**ተሰናሰለ** ግ እርስ በርስ ተቆላለፈ፣ ተያያዘ፣ ተቆራኘ።

**ሰነቀ** ግ ለጉዞ ወይም ለመንገድ የሚሆን ምግብ አዘጋጀ።

**ስንቅ** ስ ለጉዞ ወይም ለመንገድ የተዘጋጀ ምግብ ወይም የምግብ መግዣ ገንዘብ።

**ስንቅና ትጥቅ** ስ ለዘመቻ የሚሆን ምግብ፣ ገንዘብ፥ የጦር መሳሪያ፥...።

**ተሰነቀ** ግ ለጉዞ ፥ ለመንገድ ወይም ለዘመቻ የሚሆን ምግብ ተዘጋጀ።

**ሰነቀረ** ግ 1. ሻጠ፥ ሰካ። 2. ወሸመጥ ወይም ስርዋፅ አገባ። 3. ወተፈ፥ ውሻል አገባ።

**ተሰነቀረ** ግ 1. ተሻጠ፣ ተሰካ፣ ተተከለ። 2. ያለአግባብ ጣልቃ ገባ።

**ሰነበተ** ግ 1. ለብዙ ቀን ወይም ጊዜ ቆየ፣ ኖረ፥ ከረመ። 2. አዲስነቱን፥ ትኩስነቱን አጣ (ለመብል፣ ለመጠጥ)።

**መሰንበቻ** ስ መቆያ (ቀለብ፣ ቦታ)። 2.ሰሞኑን። *መሰንበቻዬን እመጣለሁ።*

**ሰንበቴ (ሰምበቴ)** (ኢ.ኦ.ተ.ቤ) ስ ሰንበትን ምክንያት በማድረግ ምእመናን በየሳምንቱ ዳቦ፥ ጠላ፣ ቆሎ ወደ ቤተክርስቲያን ይዘው ሄደው የሚዘክሩት ዝክር።

**ሰንበት** ስ የሳምንት መጨረሻና እረፍት የሚደረግበት ሰባተኛ ቀን፣ እሁድ።

**ስንብት** ስ 1. ከስራ መልቀቅ ወይም መባረር። 2. የመለያየት ስነ ስርአት ወይም የመለያያ ሰላምታ።

**የስንብት ደብዳቤ** ስ አንድ ሰው አንድን መስሪያ ቤት ለቆ ሲሄድ ወይም ከመስሪያ ቤቱ ሲባረር የሚፃፍለት ደብዳቤ።

**ተሰነባበተ** ግ የመሰነባበቻ፣ የመለያያ ቃል ተለዋወጠ።

**ተሰናበተ** ግ 1. ተባረረ፥ ተወገደ። 2. ደህና ሁን ተባብሎ ተለያየ። 3. ለቅሶ ደርሶ እግዜር ያጥናህ ብሎ ሄደ። 4.(ዘይ.) ሞተ።

**የመሰናበቻ ግብዣ** ስ የመሸኛ ግብዣ።

**አሰነበተ** ግ አቆየ፣ አከረመ።

**አሰናበተ** ግ 1. አባረረ፣ አስወገደ(ከስራ፣...)። 2. ሸኘ፥ እንዲሄድ አደረገ። 3. ለቅሶ የደረሱትን ሰዎች ሸኘ፣ ስንብት ሰጠ።

**ሰነበጠ** ግ በጣ፥ ቆረጠ፥ ቀደደ፣ ሰነጠቀ፣ ከፈለ (ብርቱካን፥ ሎሚ፥ ወዘተ.)።

**ስንባጭ** ቅ ትንሽ ቁራጭ፥ ክፋይ።

**ተሰነበጠ** ግ ተበጣ፥ ተቆረጠ፥ ተቀደደ፥ ተሰነጠቀ፥ ተከፈለ።

**ሰነተረ** ግ ሸነተረ፥ በጣ፥ ቀደደ።

**ስንትር** ስ ሽንትር።

**ሰነነ** ግ 1. በጣም ቀጠነ (ለሰውነት)። 2. በጣም ላመ፥ ደቀቀ (እህል፥...)።

**ስናና** ቅ 1.ቀጭን፣ ስላላ፣ ቀጫጫ። 2. (ዘይ.) ሞኝ፣ ቂል፣ ፈዛዛ።

***ሰነኘ**

**ስንኝ** ስ የግጥም አንድ መስመር።

**ተሰናኘ** ግ ተስማማ፣ ተገጣጠመ (ስንኝ)።

**አሰናኘ** ግ አጋጠመ፣ አስማማ (ለግጥም፣ ለዜማ)።

**ሰነከለ** ግ 1. ሰበረ(እግርን)። 2. አሰረ፣ ቀየደ፣ እንደልቡ እንዳይሄድ አደረገ።

**ስንካላ** ቅ 1. እግሩ የተሰበረ፣ አንካሳ። 2.(ዘይ.) ደካማ፣ ብቁ ያልሆነ።

**ስንኩል** ዝ.ከ.

**ተሰናከለ** ግ ተጨናጎለ፣ ተጨናገፈ፣ ተደናቀፈ፣ ተጓጎለ።

**መሰናክል** ስ 1. እንቅፋት። 2. (ዘይ.) አንድ ነገር በተሳካ ሁኔታ እንዳይሰራ የሚያደርግ ሁኔታ።

**የመሰናክል ሩጫ** ስ በየተወሰነ ርቀት ላይ የተደረደሩና ከፍታ ያላቸውን አግዳሚ እንጨቶች በዝላይ ተሻግረው እያለፉ የሚያደርጉት የሩጫ ውድድር።

**አሰናከለ** ግ 1. ጠለፈ፣ እንቅፋት ሆነ። 2. አጨናጎለ፣ አጨናገፈ፣ አደናቀፈ፣ አስተጓጎለ።

**ሰነዘረ**[1] ግ 1. በስንዝር ለካ፥ መጠነ። 2. በበትር ወይም በእጅ ለመምታት ቃጣ። 3. (ዘይ.) ሰጠ (ሃሳብን)።

**ስንዝር** ስ የአውራ ጣት ጫፍ እስከ መካከለኛ ጣት ጫፍ ድረስ ሲዘረጋ ያለው የርዝመት መጠን ወይም ልክ።

**ስንዝር የሚያህል** አነስተኛ፥ ትንሽ።

**ተሰነዘረ** ግ ተሰጠ (ሃሳብ)።

**ተሰናዘረ** ግ ተላወሰ፥ ወዲያ ወዲህ ሄደ፥ ተንቀሳቀሰ።

**መሰናዘሪያ** ስ ወዲያ ወዲህ መላወሻ፥ መንቀሳቀሻ (ቦታ፥ ገንዘብ)።

**አያሰናዝርም** 1. አያላውስም፥ አያንቀሳቅስም። 2. አያወላዳም።

**ሰነዘረ**[2] ግ ቆዳን ለመግፈፍ እንዲያመች ከጅራት እስከ ጉሮሮ፥ ከቀኝ እግር ጫፍ እስከ ግራ እግር ጫፍ ቆዳውን በመስመር ሰነጠቀ።

**ሰነደቀ** ግ በአንድነት አሰረ፣ ሰበሰበ፥ አጠራቀመ (ነዶን)።

**ስንድቅ** ቅ በአንድ ላይ የተሰበሰበ፥ የታሰረ

(ነዶ)።

***ሰነዳ**

**ስንዱ** ቅ ዝግጁ።

**ተሰናዳ** ግ ተዘጋጀ።

**መሰናዶ** ስ ዝግጅት።

**አሰናዳ** ግ አዘጋጀ።

**ሰነድ** ስ ስለ አንድ ጉዳይ መረጃዎችን የያዘ ፅሁፍ፡ መዝገብ፡ ማስረጃ።

**ሰነገ**[1] ግ 1. በአፍንጫ ቀዳዳ ወደ ጎን ሽቦን ወይም ላባን አስገባ (በከብት፡ በዶሮ)። 2. አጥብቆ፡ ወጥሮ ያዘ።

**ስናግ** ስ በአፍንጫ ላይ የተሰካ ላባ፡ ሽቦ (በከብት፡ በዶሮ)።

**ተሰነገ** ግ በሚያስጨንቅ ሁኔታ ውስጥ ገባ፥ ተያዘ።

**ሰነገ**[2] **(ሰነጋ)** ግ በቃሪያ ውስጥ ያለን ፍሬ አውጥቶ ሽንኩርት፣ ጨውና የመሳሰሉትን ነገሮች ጨመረ።

**ስንግ ቃሪያ** ስ ፍሬው ወጥቶ ሽንኩርት፣ ጨው፥...የገባበት ቃሪያ።

**ተሰነገ(ተሰነጋ)** ግ ፍሬው ከወጣለት በሗላ ሽንኩርት፥ ጨው፥...ገባበት (ቃሪያ)።

**ሰነጋ**[1] ግ የፈረስን፡ የበሬን፥ የበቅሎን፥ የወይፈንን፥...አባለ ዘር አኮላሸ፥ ቀጠቀጠ።

**ሰንጋ** ስ 1. የተቀለበ፥ የሰባ ድልብ በሬ። ቅ 2. የተኮላሸ፡ የተቀጠቀጠ (ከብት)።

**ሰንጋ ፈረስ** ስ የተቀለበ የግልቢያ ፈረስ።

**ሰንጎ መገን** ስ 1. የግጥም አይነት፣ በተለይ ጀግኖችን ለማሞገስ አዝማሪዎች በዜማ የሚያረድሩት ግጥም። 2. የማሲንቆ ወይም የክራር ቅኝት አይነት።

**ሰነጋ**[2] **"ሰነገ**[2]**"** ን ተመ.

**ሰነጠረ** ግ በቀጭኑ ሰንጥቆ አወጣ(ለእንጨት)።

**ስንጣሪ** ቅ የተሰነጠረ፡ በቀጭኑ ተሰንጥቆ የወጣ (እንጨት፡...)።

**ስንጥር** ስንጣሪ።

**ሰነጠቀ** ግ 1. ከፈለ፡ አለያየ፥ ገመሰ። 2. እየጣሰ አለፈ። *ላውሮፕላኑ ላየሩን ሰንጥቆ ሄደ።* 3 ከፍተኛ ድምፅ፡ ጩሀት አሰማ። *እሪታውን ሰነጠቀው።* 4. መስመር አወጣ (የመንገድ)። *ላውራ ጎዳና በዚህ በኩል ሰንጥቆ አስፋልት ሰራ።*

**ስንጣቃ** ቅ ስንጥቅ።

**ስንጣቂ** ቅ ከአንድ ነገር ተሰንጥቆ የወጣ ክፋይ።

**ስንጥቅ** ቅ መከፈል፥ መሰበር፥ መለያየት የጀመረ፥ የተሰነጠቀ፡ የነቃ (እቃ፥ግድግዳ፥...)። ስ 2. እየተሰበረ፥ እየተሰነጠቀ፥ እየተከፋፈለ ባለ ነገር ላይ የሚታየው ክፍተት፣ ንቃቃት።

**ስንጥቅ አተረፈ** የዋናውን ያህል አተረፈ።

**ተሰነጠቀ** ግ 1. ለመከፈል፥ ለመለያየት፥ ለመሰበር መንገድ አወጣ፥ መላቀቅ ጀመረ፥ ተገመሰ፣ ነቃ። 2. በሃይል ጮሀ (በሳቅ፥ በንግግር፥ በቁጣ)። 3.(ዘይ.) በጣም ዋሸ።

**ተሰነጣጠቀ** ግ ከውርጭ፥ ከድርቀት፥...የተነሳ ንቃቃት ወይም ስንጥቅ አወጣ (ለምሳሌ ከንፈር፥...)።

**ሰነፈ** ግ 1.ደካማ ሆነ፣ ብርታት፥ ሃይል አጣ። 2. አንድን ነገር ከመስራት፥ ከማድረግ ቸል አለ፥ ስራን ጠላ። 3. ደደበ፥ ትምህርት የማይገባው ሆነ።

**ሰነፍ** ቅ 1. አቅመቢስ፥ ደካማ፥ ቆራጥነት ያነሰው። 2. ቸልተኛ። 3. ስራ የማይወድ።

**ሰነፍ መረቅ** ስ ከጨው በስተቀር ቅቤና ቅመም ያልገባበት መረቅ።

**ሰነፍ ምርት** ስ ገለባው ከፍሬው ያልተለየ ወይም ያልጠራ ምርት።

**ሰነፍ ቆሎ** ስ አሰሩ ወይም ገለባው ሲያሹት በቀላሉ ከሚለቅ የገብስ አይነት የሚዘጋጅ ቆሎ።

**ሰነፍ እርቅ** ስ ዘላቂነት ወይም መሰረት የሌለውና በቀላሉ ሊፈርስ የሚችል እርቅ።

**ስንፍና** ስ ስራ ጠልነት፣ ቸልተኝነት።

**ተሳነፈ** ግ ሰነፈ፥ ተዘናጋ።

**አሰነፈ** ግ ቸል እንዲል አደረገ፥ አቦዘነ።

**አሳነፈ** ዝ.ከ.

**ሰነፈጠ** ግ ሰረሰረ፥ ፈጀ፥ ለበለበ (አፍንጫን)።

**ሰናፍጭ** ስ ፍሬው እንደጎመን ዘር ያለና አፍንጫን የሚለበልብ ወይም የሚሰነፍጥ ቅመም።

**ሰነፍ "ሰነፈ"** ስር ተመ.

**ሰናና "ሰነነ"** ስር ተመ.

**ሰናድር** ስ ጥንታዊ የሆነ የጠበንጃ አይነት።

**ሰናጋ** ስ ጨርሶ እንዳይለያይ በልጥ የታሰረ ሰባራ አሞሌ ጨው።

**ሰናፊል** ስ ጥንታዊ ሱሪ፣ ተነፋነፍ።.

**ሰናፍጭ "ሰነፈጠ"** ስር ተመ.

**ሰኔ** ስ ከግንቦት ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ አስረኛ ወር ስም።

**ሰን** ስ ከነሃስ ወይም ከመዳብ የተሰራ የእጅ መታጠቢያ፣ ኩስኩስት።

**ሰንሰለት "*ሰነሰለ"** ስር ተመ.

**ሰንሰል** ስ እጅብ ብሎ የሚበቅል የእፅዋት አይነት፣ ስሚዛ።

**ሰንበሌጥ (ሰምበሌጥ)** ስ ለቤት ክዳን የሚያገለግል ረዥም የሳር ኣይነት።

**ሰንበር(ሰምበር)** ስ 1. በ ሚ ሻ ክ ር ፥ በሚጎረብጥ ነገር ላይ ከመተኛት ወይም በግርፊያ የተነሳ በአካል ላይ የሚጋደም ምልክት፡ መስመር። 2. በጨርቅ ወይም በሌላ ነገር ላይ የሚደረግ የሰንበር ቅርፅ የያዘ መስመር። 3. በእንስሳት ጨጓራ መገጣጠሚያ ላይ የሚገኝ እንደ ደንደስ ያለ ወፍራምና ልሙጥ የሆነው ክፍል።

**ሰንበቴ "ሰነበተ"** ስር ተመ.

**ሰንበት** ዝ.ከ.

**ሰንቡላ [መሬት]** ስ በነሃሴ የሚወጣ ኮከብ። በተጨማሪ "**ኮከብ ቆጠራ**"ን ተመ.

**ሰንተራ** ስ የወንጭፍ ድንጋይ ኣቃፊው ቆዳ።

**ሰንካላ "ሰነከለ"** ስር ተመ.

**ሰንኬሎ (ሽንኬሎ)** ስ ባልዲ።

**ሰንኬቶ** ስ ትንሽ ጣት ላይ የሚደረግ ቀለበት።

**ሰንኮፍ(ሽንኮፍ)** ስ 1.ልባስ፤ ከረጢት (ለምሳሌ ሰውነት ውስጥ የገባ ሙጀሌ የተሸፈነበት)። 2. ያልተገረዘ የወንድ ብልት ሸፋን፤ ቆለፈት፥ ሸለፈት።

**ሰንደል**[1] ስ ሲያጨሱት ጥሩ ሽታ ያለውና በቀጭን ዘንግ መልክ የሚዘጋጅ የቤት ማጠኛ እንጨት፤ ነድ።

**ሰንደል**[2] ስ የነጠላ ጫማ ኣይነት፤ ሰንደል ጫማም ይባላል።

**ሰንደቅ** ስ የባንዲራ መስቀያ ዘንግ።


**ሰንደቅ ኣላማ** ስ ባንዲራ።

**የሰንደቅ ኣላማ መዝሙር** ስ ባንዲራ ሲወጣና ሲወርድ የሚዘመር መዝሙር።

**ሰንጋ "ሰነጋ**[1]**"** ስር ተመ.

**ሰንጎ መገን** ዝ.ከ.

**ሰንጠረዥ** ስ 1. ልዩ ልዩ ጉዳዮችን በየመደቡ ለመመዝገብ ኣግድምና ቁልቁል ተሰምሮበት የሚዘጋጅ ወረቀት፥ ሰሌዳ። 2. ባለ ኣራት ማእዘን የሆኑ ስድሳ ኣራት መደቦች ባሉት ዝርግ የእንጨት፥የፕላስቲክ፥... ሰሌዳ ላይ፥ ሁለት ሰዎች እያንዳንዳቸው በኣስራ ስድስት የመጫወቻ ቅርፆች ኣማካይነት ለኣጨዋወቱ በተወሰነው ህግ መሰረት የሚጫወቱትና ስልትን የሚጠይቅ ጨዋታ፤ ቼዝ።



ሰንጠረዥ

**ሰንጢ(ሴንጢ)** ስ 1. ታጣፊ የሆነ ኣነስተኛ ቢላዋ። 2. (ዘይ.) ሁ- ብልሀ፡ ነገር ኣዋቂ። ለ- (ስድብ) ነገረኛ።

**ሰንጣ** ስ ወለል ያለ ሰፊ ሜዳ።

***ሰኘ**

**ተሰኘ** ግ ተባለ፥ ተሰየመ፥ ተጠራ።

**ኣሰኘ** ግ 1. ኣሰባለ፡ ኣስጠራ፡ ኣሰየመ። 2. ኣስመኘ፥ ኣስፈለገ። *ምግብ ኣሰኝቶኛል።*

**ሰኞ** ስ በእሁድና በማክሰኞ መካከል ያለው ቀን ስም፤ ከእሁድ ጀምሮ ሲቆጠር የሳምንቱ ሁለተኛው ቀን።

**ሰኣሊ "ሳለ**[1]**"** ስር ተመ.

**ሰኣልናክ (ሳሊነክ)** ስ ለሰንበቴና ለማህበር ከሚጋገሩት ሁለት ዳቦዎች ኣንዱና ትንሹ (ሰኣልናክ የተባለው ፀሎት ከተፀለየ በሗላ ማህበርተኞቹ ብቻ የሚቀምሱት)።

**ሰኣት** ስ 1. ጊዜን በደቂቃ፡ በሰኮንድ እየከፈለ የሚያሳይ የጊዜ መቁጠሪያ መሳሪያ። 2. የስድሳ ደቂቃዎች ርዝመት ያለው የጊዜ መጠን። 3. ጊዜ። *ብዙ ሰኣት ፈጀ።* 4- ቀጠሮ፡ እኩለ ቀን። 5. ወቅት።

**ሰኣት ኣደረሰ** የተወሰነው የምግብ ሰኣት እስኪደርስ ቆይቶ በላ (በየም ቀን)። *ቆይና ሰኣት ኣድርሰህ ትሄዳለህ።*

**ያለሰኣት** ያለወቅቱ፡ ያለጊዜው።

**ሰኣት ማሰሪያ** ስ የእጅ ሰኣትን እጅ ላይ ለማሰር ከብረት ወይም ከቆዳ፡... የሚሰራ ማሰሪያ።

**ሰኣት ቆጣሪ** ስ በእጅ፡ በጠረጴዛ ወይም በግድግዳ ሰኣት ላይ ከደቂቃ ቆጣሪው ኣነስ ያለውና ሙሉ ሰኣትን የሚጠቁመው ኣመልካች ቀስት ወይም ዘንግ።

**ሰኣት እላፊ** ስ ከተወሰነው ሰኣት በሗላ መዘዋወር ወይም መንቀሳቀስ የሚከለከልበት የጊዜ ገደብ።

**ሰኣት እላፊ ተነሳ** የሰኣት እላፊ ኣዋጅ ተሻረ፡ ቀረ።

**ሰኣት እላፊ ታወጀ** ከተወሰነ ሰኣት በሗላ መዘዋወር የሚከለክል የጊዜ ወይም የሰኣት ገደብ ህግ ወጣ፡

**ከሰኣት [በሃላ]** ተው.ግ. ከቀትር፡ ከእኩለቀን በሗላ።

**ከሰኣት በፊት** ተው.ግ. ከቀትር፡ ከእኩለ ቀን በፊት።

**ሰኣታት (ሳታት)** (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ስ ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሊት በዜማ የሚያደርሱት ፀሎት።

**ሰኣታት ቆመ** የሰኣታትን ፀሎት በዜማ

አደረሰ፡ ፀለየ።

**የስአታት መፅሃፍ** ስ የስአታት ፀሎት መፅሃፍ።

**ተሲአት (ተሲያት)** ስ ቀትር።

**ሰከም**

**ሰከም ሰከም አለ** ግ ጠደፍ ጠደፍ እያለ ሄደ።

**ሰከረ** ግ በአልኮል መጠጥ፥ በእፅ፥... ምክንያት ስሜቱን፥ የሚሰራውን መቆጣጠር አቃተው።

**ሰካራም** ቅ 1. አልኮል መጠጥ አዘውትሮ የሚጠጣ፥ ጠጪ። 2. አልኮል መጠጥ ጠጥቶ የሰከረ።

**ስካር** ስ የአልኮል መጠጥን ወይም ሌላ አስካሪ ነገርን በመውሰድ የሚፈጠር ራስን ያለመቆጣጠር ስሜት።

**ተሳከረ** ግ 1. በአንድ ላይ በመሆንና አልኮል በመጠጣት ሁሉም ሰከረ። 2. ተምታታ፥ ተዘበራረቀ።

**አሰከረ** ግ ስሜትን መቆጣጠር እንዲሳን አደረገ፥ ራስ አዞረ (መጠጥ፥ እፅ፥...)

**አስካሪ** ቅ የሚያሰክር (መጠጥ)።

**አሳከረ** ግ አዘበራረቀ፥ አምታታ።

**ሰከሰከ** ግ 1. ተስገበገበ፥ ጠራርጎ በላ። 2. ሰረረ። 3. ሸቀሸቀ፥ አመቀ፥ ሰገሰገ።

**ሰከነ** ግ 1. ወረደ፥ ዘቀጠ፥ ረጋ (የቡና አተላ)። 2. ጨመተ፥ ረጋ አለ፥ አደብ ገዛ። 3. የተለመደ፥ የታወቀ ሆነ። *የሰከነ ቃል መጠቀም ያስፈልጋል።*

**ሰካ** ግ 1. ሻጠ፥ ተከለ፥ አገባ። 2. አጠለቀ።

**ስኬት** ስ የአላማ ወይም የድርጊት ክንዋኔ በጥሩ ሁኔታ እንደታቀደው መፈፀም።

**ስኬታማ** ቅ የተሳካ፥ ጥሩ ውጤት ያለው።

**ስክ** ቅ የሚሰካካ፥ የሚገጣጠም።

**ስክ ሳህን** ስ የሚገጣጠም ሳህን።

**ተሰካ** ግ ተሻጠ፥ ተተከለ፥ ተሸጎጠ።

**ተሰካካ** ግ ተገጣጠመ።

**ተሳካ** ግ ተሟላ፥ ተቃና፥ ተስተካከለ፥ በሚፈለገው መልክ ተከናወነ።

**አሳካ** ግ 1. አቃና፥ አሟላ፥ በሚፈለገው መልክ እንዲከናወን አደረገ። 2. አቀናበረ፥ አስተካከለ (ለአረፍተ ነገር፥ ለንግግር)።

**ሰኮና** "ሸሆና" ን ተመ.

**ሰከንድ(ሴኮንድ)** ስ የሰአት አነስተኛ ክፍልፋይ። አንድ ሰከንድ የደቂቃ አንድ ስድሳኛ ነው።

**ሰከንድ ቆጣሪ** ስ በእጅ፥ በጠረጴዛ ወይም በግድግዳ ሰአት ላይ ከሙሉ ሰአት ቆጣሪው ረዥምም የሆነውና የሰከንድን መጠን አመልካች የሆነው ቀጭን አመልካች ዘንግ።

***ሰወለለ**

**ተንሰዋለለ** ግ ተንቀዋለለ።

**አንሰዋለለ** ግ አንቀዋለለ።

**ሰወረ** ግ 1. ደበቀ፥ ጋረደ፥ ሸፈነ፥ ሸሸገ። 2. አይንን አወረ፥ ጋረደ።

**ሰዋራ** ቅ ሽሽግ፥ ድብቅ (ቦታ)።

**ስውር** ቅ ሽሽግ፥ ድብቅ፥ የማይታይ።

**ስውር ስፌት** ስ ክሩ እንዳይታይ ሆኖ የተሰፋ ስፌት።

**ተሰወረ** ግ 1. ተደበቀ፥ ተሸሸገ። 2. ታወረ።

**ሰዋ** ግ 1. አረደ። 2. ሰጠ (ህይወትን ለሃገር፥ ለሃይማኖት)። 3. አቀረበ፥ ሰጠ (መስዋእትን ለአምላክ)።

**መስዋእት** ስ 1. ለአምልኮ የሚሰጥ፥ የሚቀርብ ስጦታ። 2. (ክር.) ስጋ ወደሙ።

**መስዋእት ሆነ** ህይወቱን አሳልፎ ሰጠ (ለአገሩ፥ ለእምነቱ)።

**መስዋእት አደረገ** ሰዋ፥ መስዋእት አቀረበ።

**መስዋእት ከፈለ** ለአላማው፥ ለእምነቱ መስዋእት ሆነ፤ ለህይወቱ ሳይሳሳ ታገለ።

**ተሰዋ** ግ ህይወቱን አሳልፎ ሰጠ (ለሃገሩ፥ ለአላማው፥ ለሃይማኖቱ)።

**ሰዋራ** "ሰወረ" ስር ተመ.

**ሰዋስው** ስ የቃላት አመሰራረትና የአረፍተ ነገር አሰካክ ስርአት ወይም ህግ። *የሰዋሰው ስህተቶችን አርም።*

**ሰው** ስ 1. ማሰብና ማመዛዘን የሚችል፥ ሰብአዊ ፍጡር። 2. በሶስተኛ መደብ የሚጠራ፥ ሌላ ግለሰብ። *ሰው መጣ /ሰው ነገረኝ/ ሰው እንዳይሰማ።* 3. ዘመድ፥ አጋር፥...። *ሰው ስለሌለኝ ስራ ላጥ ሆኜ ቀረሁ።*

**ሰው ሆነ** ራሱን ቻለ፥ በረታ፥ አእምሮ ገዛ፥ ጎበዝ ሆነ።

**ሰው ለየ** 1.አወቀ። *ህፃኑ ሰው ለይቷል።*2. አዳላ። *ይህም ጥቅም ሆኖ ሰው ይለይበታል።*

**ሰው አይሆንም** 1.ከደረሰበት ሃዘን፥ ብስጭት፥ጉዳት፥ መከራ፥... የተነሳ በጣም ይጎዳል። 2. ለቁም ነገር፥ ለጥሩ ውጤት አይበቃም።

**ሰው አይደለም** በጣም መጥፎ ሰው ነው።

**ሰው መሳይ በሸንጎ** በሩቅ ለሚያውቀው ጥሩ ሰው መስሎ የሚታይ።

**ሰው ሰራሽ** ቅ የተፈጥሮ ያልሆነና ሰው

የሰራው።

**ሰው በላ /በሌ** ቅ ጨካኝ፡ አረመኔ።

**ሰው በሰው** በሌላ ሰው እርዳታ።

**ሰው ጤፉ** ሰው የሚንቅ፥ ያለ እኔ ማን አለ የሚል።

**ሰውዬ** 1.አንድ ሰው። *ለአንድ ሰውዬ ውጭ ቆሟል።* 2. አንተ ሰው (ለጥሪ)።

**የሰው** የሌላ ግለሰብ። *መኪናው የኔ አይደለም፤ የሰው ነው።*

**የሰው ልክ አያውቅም** ሰውን ያለአግባብ ይደፍራል።

**የሰው መጨረሻ ነው** በጣም ጥሩ ሰው ነው።

**የሰው ነጭ ታየ** ቁጥሩ የበዛ ሰው ታየ፡ ወይም ተገኘ።

**የሰው ሃይል** ስ ሰራተኛ። *ለስራው መፋጠን ተጨማሪ የሰው ሃይል ያስፈልጋል።*

**የሰው ልጅ** ሰው የተባለ ፍጡር በጠቅላላ።

**የሰው አይን** ባየው ነገር ላይ ጉዳት፡ ጠንቅ የሚያደርስ ወይም የሚያስከትል አይን።

**የሰው አይን በላው** ሞተ ወይም ሌላ ጉዳት ደረሰበት (በቡዳ፡... ምክንያት)።

**የሰው አገር ሰው** ባይተዋር፥ እንግዳ።

**የሰው ዘር** ሰው የተባለው ፍጡር ሁሉ።

**ሰውነት** ስ ገላ፡ አካላት(አከላት)ስእለንየሚቀተለውገዐ

**ሰውነቱ ላመ** ከድካም የተነሳ ሰውነቱ ደቀቀ፥ ዛለ።

**ሰውነቱን ጠበቀ** ለሰውነቱ እንክብካቤ ወይም ጥንቃቄ አደረገ።

**ሰውኛ** ስ ሰው ያልሆነውን ነገር እንደሰው በማናገር ወይም የሰው ባህርይ በመስጠት የሚነገር የዘይቤ መንገድ።

**ሰውር [መሬት]** ስ በሚያዝያ የሚወጣ የከከብ አይነት፤ በተጨማሪ "ኮከብ ቆጠራ" ን ተመ.

**ሰየ** ግ ሳመጀ፥ ተመኘ።

**ሰያቱ** ቅ ስግብግብ፥ ሁሉ ነገር የሚያምረው።

**ሰየመ** ግ 1. ስም ሰጠ፤ ስም አወጣ። 2. አስቀመጠ፥ አዘጋጀ፥ አቀረበ።

**ስያሜ** ስ 1. ስም፤ መጠሪያ። 2. የመሰየም ስራ፥ አንድን ነገር ወይም ሃሳብ የሚወክል ቃል የመፍጠር ተግባር።

**ስያሜ ቃላት** ስ ለውጭ ወይም ለአዳዲስ ፅንሰ ሃሳቦች በሃገርኛ ቋንቋ መጠሪያ የመስጠት ስርአት፥ ተግባር።

**ተሰየመ** ግ 1. ስም ወይም መጠሪያ ወጣለት። 2. ተቀመጠ (ለስብሰባ፥ ለፍርድ፥...)።

***ሰየረ (*ሴረ)**

**ሴራ** ስ አድማ፡ ዱለታ።

**ሴራ ቆረጠ** አድማ አደረገ፡ ዶለተ።

**ሴራ ጠነሰሰ** ተንኮል፡ ሴራ፡ አድማ ወጠነ ።


**ሴረኛ** ቅ አድመኛ፡ አድማ አቀነባባሪ።

**አሴረ** ግ አደመ፡ ዶለተ፡ ሴራ ጠነሰሰ።

**ሰየፈ** ግ 1. በጎራዴ ወይም በሰይፍ መታ፥ ቀነጠሰ፤ በጠሰ። 2. አጋደመ፥ በሰያፍ አደረገ።

**ሰያፍ** ቅ 1. አግድም፡ የጎንዮሽ የሆነ። 2. (ዘይ.) በማስታከክ የተነገረ፡ ፊት ለፊት ያልሆነ (ለንግግር)።

**ሰይፍ** ስ በሁለት በኩል ስለት ያለው ቀጥ ያለና ከወደጫፉ ሾጣጣ የሆነ የጦር መሳሪያ።



ሰይፍ

**ተሰየፈ** ግ በሰይፍ ተመታ፥ ተቀላ፡ ተቆረጠ።

**አሰየፈ** ግ በሰይፍ ቅርፅ ወይም በስላች ሆነ።

**ሰያቱ** "ሰየ" ስር ተመ.

**ሰያፍ** "ሰየፈ" ስር ተመ.

**ሰይጣን** ስ 1. ተግባሩ መጥፎ የሆነ፥ እርኩስ መንፈስ፡ ጋኔን፥...። 2. (ዘይ.) ክፉ፥ መጥፎ (ሰው)።

**ሰይጣኑ መጣ** ተናደደ፥ ተቆጣ።

**ሰይጣን አትሁንብኝ** እንድናደድ፡ እንድቆጣና መጥፎ ስራ እንድሰራ ምክንያት አትሁንብኝ።

**ሰይጣን የለከፈው** ክፉ፡ መጥፎ (ሰው)።

**ሰይጣን ያጋለው/የጋለበው** ሰይጣን የተጠናወተው፡ እኩይ ሰው።

**የሰይጣን ቁራኛ** ቅ ክፉ፡ መጥፎ።

**የሰይጣን ቁራጭ** ቅ ክፉ፡ መጥፎ፡ አሳሳች፡ ሰይጣን የሆነ (ለሰው)።

**የሰይጣን ዶሮ** ስ ባህር ውስጥ ጠልቆ መቆየት የሚችልና ጠቃጠቆነት ያለው የአሞራ አይነት።


**የሰይጣን ፈረስ** ቅ ግልፍተኛ፡ ቁጡ፡ ጠብ ጫሪ።

**ሰይጣናም** ቅ ተናዳጅ፥ ግልፍተኛ፡ ቁጡ።


**ሰይፍ** "ሰየፈ" ስር ተመ.

**ሰደረ** ግ ደረደረ፥ በረድፍ፥ በተራ አስቀመጠ።

**ተሰደረ** ግ ተደረደረ፤ በረድፍ፥ በተራ ተቀመጠ።




1. ፊት
2. እልቅት
3. ደረት
4. ጡት
5. ብብት
6. እምብርት
7. በገርድ
8. ሙሃኚት
9. እምስ
10. ፍርንትት
11. ቁላ
12. ጭን
13. ጉልበት
14. ቅልጥም
15. የእግር ጣት
16. አንገት




1. ትከሻ
2. ጀርባ
3. ሽንጥ
4. ዳሌ
5. ቂጥ
6. ክርን
7. ታፋ
8. ቋንጃ
9. ባት
10. ቁርጭምጭሚት
11. ተረከዝ
12. ኮቴ
13. ጫንቃ
14. ብራኳ
15. ክንድ

**ሰደርያ** ስ ክኮት ስር፥ ከሸሚዝ በላይ የሚለበስ እጅጌና አንገትጌ የሌለው ልብስ።

**ሰደቃ** ስ 1. ገበታ፥ መሰብ። 2. የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ለድሆች የሚያበሉት ተዝካር።

**ሰደበ** ግ ዘለፈ፥ ወረፈ፥ አዋረደ፥ አረከሰ፥ ክፍ ዝቅ አድርጎ ተናገረ።

**ስድብ** ስ ዘለፋ፥ ለማዋረድ ወይም ለማክሰስ የሚነገር መጥፎ ቃል።

**ስድብ ቀመሰ** ተሰደበ።

**በስድብ ተለቀቀበት** በጣም ሰደበው፥ የስድብ ናዳ አወረደበት።

**ተሰደበ** ግ ተዘለፈ፥ ተዋረደ።

**ተሳደበ** ግ አዋረደ፥ ዘለፈ።

**ተሳዳቢ** ቅ አዋራጅ፥ መሳደብ ልማዱ የሆነ።

**አሰደበ** ግ ለመዋረድ፥ ለመነቀፍ ምክንያት ሆነ።

**አሰዳቢ** ቅ ለመሰደብ ምክንያት የሚሆን (ተግባር፥ ጠባይ)።

**ሰደደ** ግ 1. ላከ። 2. አባረረ፥ አሰናበተ። 3.ለቀቀ፥ ፈታ። 4. ከተተ፥ አገባ። *በሰው ቀስል እንጨት ሰደድበት እንዲሉ።* 5. የሰደድ እሳትን አቀጣጠለ ወይም ለኮሰ።

**ሰደድ እሳት** ስ ሃይለኛ የሆነና ጫካ ውስጥ ወይም ቀጥቋጦና ደረቅ ሳር ባለበት የሚነሳ እሳት፥ ቃጠሎ።

**ስደት** ስ በመባረር፥ በፖለቲካ ወይም በሌላ ችግር ምክንያት አገርን ለቆ መሄድ፥ ፍልሰት።

**ስደተኛ** ስ አገሩን ያለፈቃዱ ለቆ በሌላ አገር የሚኖር ሰው።

**ስድ** ቅ 1. ልቅ፥ ያልተከፋፈለ፥ ሰፊ (ቤት)። 2. (ስድብ) ባለጌ።

**ስድ ንባብ** ስ ግጥም ያልሆነ ንባብ።

**ስድ አደግ** ስ ባለጌ።

**ተሰደደ** ግ በፖለቲካ ወይም በሌላ ችግር ምክንያት አገሩን ለቆ ሄደ።

**ተሳደደ** ግ ተባረረ።

**አሳደደ** ግ 1. እየተከታተለ አባረረ። 2. ስራዬ ብሎ አንድን ነገር ተከታተለ።

**አሳዳጅ** ቅ አንድን ነገር ከመውደዱ ወይም ከመፈለጉ የተነሳ ስራዬ ብሎ የሚከታተል።

**ሰደፍ**[1] ስ የጠመንጃ እግር፥ ላት (ሰእሉን ጠመንጃ ስር ተመ.)።

**ሰደፍ**[2] ስ እንቁ ወይም ሉልን የምትወልድ የባህር ፍጥረት።

**ሰገለበ** ግ ተስገበገበ፥ ተጣደፈ፥ ቸኮለ (አንድን ነገር ለማግኘት ወይም ለማድረግ)።

**ስግላባ** ቅ ችኩል፥ ስግብግብ።

**ሰገረ** ግ በአጫጭር እርምጃ እየፈጠነ በማይነቀንቅ አካሄድ ሄደ፥ ፈሰሰ (ለበቅሎ፥ ለፈረስ)።

**ሰጋር** ቅ ሲሄድ ወይም ሲራመድ ጋላቢውን የማይነቀንቅ (ብዙውን ጊዜ ለበቅሎ)።

**ሰገራ** ስ (ነውር) አይነ ምድር።

**ሰገራ ወጣ** ተፀዳዳ።

**ሰገሰገ** ግ 1. ጠቀጠቀ፥ በክፍት ቦታ ሞላ፥ ሰካ። 2.ጠቀጠቀ፥ አጠጋጋ (የጨርቅን ጥለት ወይም ማግ ለመቋጨት)። 3. በብዛት አስገባ፥ ሞላ።

**ስግስግ** ቅ ጥቅጥቅ፥ በደንብ ተጠጋግቶ የተሰራ።

**ተሰገሰገ** ግ 1. ተጠቀጠቀ፥ በክፍት ቦታ ገባ፥ ተሰካ። 2. በብዛት ገባ፥ ሞላ።

***ሰገበገበ**

**ስግብግብ (ሰገብጋባ)** ቅ ስስታም፥ ቅቅታም።

**ተስገበገበ** ግ በጣም ጓጓ፥ ሰፍ አለ (ለምግብ ወይም ለሌላ ነገር)።

**አስገበገበ** ግ በጣም አጓጓ፥ አንሰፈሰፈ፥ ሰፍ አደረገ። *ምን ያስገበግብሃል? ቀስ ብለህ ታገኘዋለህ።*

**ሰገባ** ስ አፎት፥ የሰይፍ ማህደር።

**ሰገብጋባ** "*ሰገበገበ" ስር "ስግብግብ"ን ተመ.

**ሰገነት** ስ 1. የፎቅ ቤት በረንዳ። 2. በአካባቢው ካሉት ነገሮች ሁሉ በጣም ከፍ ብሎ የተሰራ ቦታ (ለመመልከቻ የሚሆን)። 3. ባለአንድ ፎቅ የገጠር ቤት።

**ሰገደ** ግ 1. ተንበረከከ፥ አጎነበሰ፥ ተደፋ (ለአምላክ ፀሎት፥ ምስጋና ለማቅረብ)። 2. ተሸነፈ፥ እጅ ሰጠ፥ የሌላውን የበላይነት አወቀ። 2. (ዘይ.) አጎበደደ።

**ስግደት** ስ 1. ለአምላክ ክብርና ምስጋናን ለማቅረብ፥ ይቅርታን ለመጠየቅ እየፀለዩ የሚያደርጉት የማጎንበስ፥ የመንበርከክ ስርአት። 2. በክርስትና ሃይማኖት መሰረት በህማማት ውስጥ በተለይም የስቅለት እለት እየሰገዱ የሚያከናውኑት የፀሎት ስርአት።

**አስገደ** ግ ሰጥ ለጥ አድርጎ ገዛ።

***ሰገደደ**

**ስግዳዳ** ቅ 1. ደባቃ፥ ሰዋራ (ቦታ)። 2. ጎንባሳ፥ ጎበጥ ያለ። 3. ረባዳ።

**ስግደድ አለ** ግ 1. ረባዳ ሆነ። 2. ጎንበስ፥ ጎበጥ አለ።

**ሰገድ** ስ ከወይራ ጋራ ተመሳሳይነት ያለው የዛፍ አይነት።

**ሰገገ** ግ ቀጭንና ረዥምም ሆነ (አንገቱ)።

**ሰጋጋ** ቅ አንገተ ረዥም።

**ስግግ አለ** ግ በጣም ቀጥኖ ረዘመ (አንገቱ)።

**ስግግ አደረገ** ግ መዘዘ፥ አስረዘመ (አንገቱን)።

**አሰገገ** ግ አንገቱን መዘዘ፥ አስረዘመ።

**ሰገጠ** ግ 1. ሸለመ፥ ቀመቀመ፥ አስጌጠ፥ ዘመዘመ። 2. አጠቆረ፥ ቋጠረ፥ አስከፋ (ፊትን)።

**ሰገጥ** ስ ዝምዝማት፥ ጌጥ፥ ቅምቅማት፥ ሸልማት፥ ንቅሳት (የካባ፥ የቀል፥...)።

**ተሰገጠ** ግ ተዘመዘመ፥ ተቀመቀመ፥ ተሸለመ።

**ሰገጥ[1] (ሰጎጥ)** ስ መሬት ውስጥ የተተከለና ለመንቀል የሚያስቸግር ድንጋይ፥ የዛፍ ስር፥...።

**ሰገጥ[2]** "**ሰገጠ**" ስር ተመ.

**ሰጋ** ግ ፈራ፥ መጥፎ ነገር ይደርሳል ብሎ ጠረጠረ፥ ተጨነቀ።

**ስጉ** ቅ ብዙ ጊዜ አንዳች መጥፎ አደጋ፥ ክፉ ነገር፥... ይደርሳል ብሎ የሚፈራ።

**ስጋት** ስ ፍርሃት፥ ጥርጣሬ።

**አሰጋ** ግ አስፈራ፥ አስጨነቀ።

**አስጊ** ቅ አደገኛ፥ አስፈሪ።

**ሰጋር** "**ሰገረ**" ስር ተመ.

**ሰጋጋ** "**ሰገገ**" ስር ተመ.

**ሰግላባ** "**ሰገለበ**" ስር ተመ.

**ሰግዳዳ** "***ሰገደደ**" ስር ተመ.

**ሰጎን** ስ አንገቱና እግሮቹ ረጃጅምም፥ አካሉም ግዙፍ የሆነና የማይበር በአፍሪቃ የሚገኝ የአእዋፍ አይነት (ሰእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

**ሰጎደ** ግ 1. መታ፥ ጠሰቀ። 2. አጎደጎደ፥ ሰረጎደ። 3. አበጀ (ጋሻን)።

**ሰጎጥ** "**ሰገጥ[1]**" ን ተመ.

**ሰጠ** ግ 1. አደለ፥ አቀበለ። 2. ቸረ፥ ለገሰ። *እግዜ ለተቸገረ ይሰጣል*። 3. ሸለመ፥ በቋሚነት አበረከተ። 4. ተመቸ፥ ጥሩ ሆነ። *ቁመቱ ለቅርጫት ኳስ ጨዋታ የሰጠ ነው*። 5. ከፈለ፥ በለውጡ ሌላ እንዲወስድ አደረገ። ለመፅሃፉ አስር ብር ብሰጠው አያዋጣኝም አለ። 6.አስገኘ። *ፀሃይ ብርሃን ትሰጣለች*። 7.መስዋእት አደረገ፥ መስዋእትነት ከፈለ። *ለአላማው ሀየወቱን ሰጠ*። 8. አዋለ፥ ለመስዋእትነት አዘጋጀ። *ሀይወቱን ለመልካም ተግባር የሰጠ ነው*። 9.አስረከበ። *ደብዳቤውን ዛሬ ሰጠሁት*። 10. እንዲደርሰው አደረገ፡*መልእክቱን ሰጠው*። 11. ነገሩን አሳወቀ፥ ገለፀ፥ እንዲያውቅ አደረገ።*መልስ ሰጠ።* 12. አሳየ፥ ገለፀ፥ ነገረ። *ምልክት ሰጠ*። 13. እንዲያገኝ አደረገ። *ስልጣን ሰጠ።*

**እሰጥ አገባ** ስ 1. የቀድሞ ጊዜ የሙግት ወይም የክርክር መንገድ። 2. አስፈላጊ ያልሆነ ሙግት፥ ጭቅጭቅ።

**ሰጥ** ቅ ቸር፥ ለጋስ፥ ደግ።

**ስጦታ** ስ 1.ገፀ በረከት። 2. ችሎታ።

**ሰጭ** ቅ 1. ቸር፥ ለጋስ። 2. አዳይ፥ አከፋፋይ (በካርታ ጨዋታ)።

**ተሰጠ** ግ 1. ታደለ። 2. ተበረከተ። 3. እንዲደርስ ተደረገ፥ ተነገረ። *ምስጋና ተሰጠው።*

**ተሰጥኦ** ስ 1.ልዩ ችሎታ። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቤተ ክርስቲያን ህዝቡ ከዲያቆንና ከቄስ እየተቀበለ የሚያዜመው የቅዳሴ ዜማ፥ ፀሎት።

**ሰጠመ** "**ሰመጠ**" ን ተመ.

**ሰጠሰጠ** ግ 1. ደበደበ፥ ገረፈ፥ መታ፥ ወቀጠ። 2. በሃይል ጣለ፥ ወረደ። *ዝናቡ ትናንት ሲሰጠስጠው አደረ*። 3. በብዛት ፃፈ።

***ሰጠጠ**

**ሲጢጥ አለ** ግ በር ሲከፈትና ሲዘጋ ማጠፊያዎች የሚያሰሙትን አይነት ድምፅ አሰማ።

**ሲጢጥ አደረገ** ዝ..ክ.

**ተንሲያጠጠ** ግ ሲጢጥ የሚል አይነት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ።

**አንሲያጠጠ** ግ ሲጢጥ የሚል ድምፅ አሰማ።

***ሰጣ**

**ስጥ** ስ ፀሃይ እንዲመታው የተዘረረ ወይም የተዘረጋ እህል።

**ተሰጣ** ግ ፀሃይ ላይ ተዘረረ ወይም ተዘረጋ (እህል፥ ልብስ፥...)።

**አሰጣ** ግ ለፀሃይ ሰጠ፥ ዘረረ፥ ዘረጋ (እህልን፥ ልብስን፥...)።

**ማስጫ** ስ 1. እህልን ፀሃይ ላይ ለማስጣት የሚያገለግል እንደሰፌድ፥ ኪሻ፥... ያለ እቃ። 2. ልብስ የሚሰጣበት ገመድ፥ ሽቦ፥...።

**አሰጣጣ** ግ ስጡን አገለባበጠ።

**ሰጥ[1]**

**ሰጥ ለጥ አለ** ግ ተሸቆጥቆጠ፥ እሺ፥ አሜን ብሎ ተገዛ፥ ተዳደረ።

**ሰጥ[2]** "**ሰጠ**" ስር ተመ.

**ሰጥር** ስ ቀጭን የጎድን አጥንት።

**ሰጭ** "**ሰጠ**" ስር ተመ.

**ሰፈረ[1]** ግ 1. ለካ፥ መጠነ (መጠኑን ለማወቅ)። 2. በተለያዩ መስፈሪያዎች እየለካ፥ እየመጠነ ሰጠ። 3. ከአፍ እስከገደፉ ጢም አድርጎ ሞላ፥ ከሚገባው በላይ ጨመረ፥ ቀዳ፥...።

**በሰፈረው ቁና ተሰፈረ** ለፈፀመው ክፉ ስራ ዋጋውን አገኘ፥ ተከፈለ።

**መስፈሪያ** ስ መለኪያ፥ መመዘኛ እቃ (እንደ ቁና፥ ሰሃን፥ ሜትር፥ ...ያለ)።

**መስፈርት** ስ መሟላት ያለበት አስፈላጊ ነጥብ፤ መለኪያ። *እዚህ መስሪያ ቤት ለመቀጠር የምታሟላቸው መስፈርቶች አሉ።*

**ስፍር** ቅ 1. የተለካ፥ የተመጠነ። ስ 2. ልክ፥ መጠን።

**ስፍር ቁጥር የለውም** እጅግ በጣም ብዙ ነው።

**ተሰፈረ** ግ 1. ተለካ፥ ተመጠነ። 2. ተቀበለ (የቀለብ እህልን)።

**ሰፈረ**[2] ግ 1. መኖሪያ ቦታ ያዘ፥ ኗሪ ሆነ። 2- አረፈ፥ ተቀመጠ። 3. ቆጥ ላይ ወጣ፥ ማደሪያውን ያዘ (ዶሮ)። 4. ተፃፈ፥ ተመዘገበ።

**ሰፈረበት** 1. ለመምታት፥ ለመደብደብ ያዘው፥ ጣለው፥ እላዩ ላይ ወጣ። 2. ያዘው፤ አደረበት። *ጋኔን ሰፈረበት።*

**ሰፈራ** ስ ቀድሞ ከነበሩበት መኖሪያ ተነስቶ ሌላ ቦታ የመኖር ድርጊት።

**ሰፈራ ጣቢያ** ስ ከሌላ ቦታ የመጡ ሰዎች እየሰሩ እንዲኖሩበት የተዘጋጀ ቦታ።

**ሰፈረተኛ** ስ የአንድ አካባቢ መንደር ኗሪ (ህዝብ)።

**ሰፋሪ** ቅ ቀድሞ የነበረበትን መኖሪያ ለቆ በሰፈራ ሌላ መኖሪያ ቦታ ይዞ የሚቀመጥ።

**ሰፈር** ስ 1. በጉዞ ላይ ያሉ ሰዎች ወይም ወታደሮች ጊዜያዊ መኖሪያ። 2. የመኖሪያ አካባቢ።

**ስፍራ** ስ ቦታ።

**ስፍራ ያዘ** 1. ቦታ አጣበበ። 2. መቀመጫ ቦታ አግኝቶ ተቀመጠ።

**ተሳፈረ** ግ መኪና፥ አውሮፕላን፥ መርከብ ላይ ወጣ (ለጉዞ)።

**ተሳፋሪ** ስ ተጓዥ፥ መንገደኛ (በመጓጓዣ)።

**አሰፈረ** ግ 1. ቦታ አስያዘ፤ የመኖሪያ ቦታ፥ ከልል ሰጠ። 2. ፃፈ፥ መዘገበ።

**አሳፈረ** ግ 1. ለማጓጓዝ ጫነ (አውሮፕላኑ፥ መርከቡ፥...)። 2. ተሳፋሪን፥ መንገደኛን ሸኘ (መኪና፥ ባቡር፥... ውስጥ እስከሚገባ)።

***ሰፈሰፈ**

**ስፍሳፋ** ቅ 1. ገብጋባ። 2. አለመጠን ችኩል፥ ጉጉ።

**ስፍስፍ አለ** ግ. 1. በጣም ተንገበገበ። 2.ተንዘፈዘፈ፥ ተንቀጠቀጠ። 3. ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። 4. ተሰቃየ።

**ተንሰፈሰፈ** ግ 1.ተንገበገበ፥ ጓጓ። 2.ተንዘፈዘፈ፥ ተንቀጠቀጠ፥ ተርገበገበ። 3. ተንሰቀሰቀ፥ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። 4. የስቃይ፥ የህመም ስሜት ክፉኛ ተሰማው።

**አሰፈሰፈ** ግ አቁበቀበ፥ ተዘጋጀ፥ በጉጉት ጠበቀ።

**አንሰፈሰፈ** ግ 1. አንዘፈዘፈ፥ አንቀጠቀጠ። 2. አንገበገበ።

**ሰፈነ** ግ መላ፥ ከዳር እስከ ዳር ሆነ። *ፀጥታ ሰፈነ።*

**አሰፈነ** ግ ከዳር እስከ ዳር እንዲሆን አደረገ፥ መላ። *በሃገሪቱ ሰላምን አሰፈኑ።*

**ሰፈፈ** ግ ከፈሳሽ ነገር ላይ ከላይ ሆኖ ሳይሰጥም ተገኘ ወይም ታየ።

**ሰፈፍ** ስ የማር አሰር፥ ምጣጭ፤ የጠጅ ገፈት (ሰም የሚሆን)።

**ሰፈፍ የለውም** እንከን፥ ነውር፥ ክፋት የለውም።

**ተንሳፈፈ** ግ 1. ከላይ ሆነ፥ ዋኘ፥ ከፈሳሽ ነገር ላይ ሆኖ ሳይሰጥም ከላይ ቀረ ወይም ታየ። 2. አንዣበበ፥ በአየር ላይ በረረ። 3. የነበረበት መስሪያ ቤት የመዋቅር ለውጥ በማድረጉና በአዲሱ መዋቅርም ባለመታቀፉ ከስራ ተወገደ።

**ተንሳፎ ቀረ** ከማንኛውም ወገን ሳይሆን ቀረ።

**አሰፈፈ** ግ ሰፈፈ፥ ተንሳፈፈ።

**አንሳፈፈ** ግ 1. አሰፈፈ፥ በላይ አደረገ፥ ሳያስጥም ቀረ። 2. በአየር ላይ አበረረ።

**ሰፌ** "ሰፋ[2]" ስር ተመ.

**ሰፋ** ስ ቀጥና መለል ብሎ የሚበቅል፥ ለዘንግ የሚሆን የእፅዋት አይነት፤ ጠፎ፤ ሶማያም ይባላል።

**ሰፋ**[1] ግ 1. በመርፌና በክር አያያዘ፥ ጠቀመ፥ ዘመዘመ፥ ወሰወሰ (ለምሳሌ ልብስን)። 2. አዘጋጀ፥ አበጀ፥ ሰራ (ሰፌድን፥ ጫማን፥ ...በመርፌና በክር፥ በስንደዶ፥... በማያያዝ)። 3.ወጋ፥ ሰነገ፥ አስጨነቀ፥ ቀሰፈ። *ውጋት ሰፍቶ ያዘኝ።*

**ሰፊታ** ስ የመሶብንና የሌላውንም የስፌት ስራ በደንብ የምታውቅ ባለሙያ።

**ስፌት** ስ 1. የመስፋት ስራ ወይም ሙያ። 2. ልብስ፥ ጫማ ወዘተ. በመርፌና በክር የተያያዘበት ቦታ። 3. እንደመሶብ፥ ሙዳይ፥ ሰፌድ የመሰለውና ብዙውን ጊዜ ከስንደዶ፥ ከአክርማ፥ ከግራምጣ የሚዘጋጅ የቤት እቃ።

**የስፌት መኪና** ስ ጨርቃ ጨርቅን፥ ቆዳን፥ ሸራን፥... ለመስፋት የሚያገለግል ዘመናዊ መሳሪያ።

**አሰፋ** ግ በልኩ እንዲሰፋለት አደረገ (ልብስን)።

**ሰፋ**[2] ግ 1. በጎን ወይም በወርድ ወይም ዙሪያውን መጠኑ ጨመረ፥ አደገ፥ ሰፊ ሆነ፥ ተለቀ። 2.ከልክ በላይ ሆነ፥ ተለጠጠ (ለልብስ፥ ለጫማ፥...)። 3. ተንቦረቀቀ (ቀዳዳው፥ ክፍተቱ፥ አፉ)። 4. ጨመረ፥ አደገ፥ ከፍ አለ። *እውቀቱ ሰፋ / ድርጅቱ ሰፋ።*

**ሰፊ** (ብ.ቁ. **ሰፋፊ**) ቅ 1. የተንጣለለ፥ ዙሪያው፥ ወርዱ ወይም ጎኑ ስፋት ያለው። 2. ከልክ በላይ የሆነ (ልብስ፥ ጫማ ፥...)። 3. ቦርቃቃ፤ ቀዳዳው፥ ክፍተቱ፥ አፉ የሰፋ። 4. ጥልቅ፥ ብዙ ፥ ከፍ ያለ፥ ትልቅ። *ስለመዛግብተ ቃላት አሰራር ሰፊ እውቀት አለው።*

**ሰፊው ህዝብ** ስ ብዙሃኑ ህዝብ።

**ስፋት** ስ 1. ወርድ ወይም ጎን። *ሜዳው ስፋት እንጂ ቁመት የለውም።* 2. አንድ ነገር በቁመቱና በጎኑ በአጠቃላይ የሚይዘው፥ የሚጠቀልለው ቦታ። 3. ብዛት፥ ጥልቀት።

**[የ]ስፌት እቃ** ስ እንደ ሰፌድ፥ መሶብ፥... ያለ ከሰንደዶ፥ ከአክርማ፥ከገራምጣ የሚሰራ የቤት እቃ (ስእሉን በሚቀተለው ገፅ ተመ)።

**ተስፋፋ** ግ 1. ተንሰራፋ፤ ተመቻቸቶ፥ ብዙ ቦታ ይዞ ተቀመጠ፥ ተደላደለ። 2. አደገ፤ ተጠናከረ፤ ተደራጀ። *ኢንዱስትሪ በሃገሪቱ ተስፋፍቷል።* 3. ተዛመተ፥ ተራባ፥ ተዳረሰ፥ ተሰራጨ። *በሽታ ተስፋፋ።*

**ተስፋፊ** ቅ የራሱን ክልልና ድንበር አልፎ ግዛትን የማስፋፋት እቅድ ወይም ፖሊሲ ያለው።

**አሰፋ** ግ 1. በጎን ወይም በወርድ ወይም ዙሪያውን መጠኑን ጨመረ፥ አሳደገ፥ አተለቀ። 2. ከልክ በላይ አደረገ፥ ለጠጠ (ለልብስ፥ ለጫማ፥...)። 3. አምቦረቀቀ። 4. ጨመረ፥ አሳደገ፥ከፍ አደረገ (ለእውቀት፥ ለድርጅት፥...)። 5. የእንጀራ ሊጥን በምጣድ ላይ አፈሰሰ፥ አዞረ።

**አስፋፋ** ግ 1. አሳደገ፥ ከፍ አደረገ። *የንግድ ድርጅቱን አስፋፋ።* 2. አብራራ፥ ተነተነ። 3. አዛመተ፥ አራባ። *ወሬውን አስፋፋ/ በሽታን አስፋፋ።*

**ሰፋሪ** "ሰፈረ[2]" ስር ተመ.

**ሰፋድል** ስ በግህፀን ውስጥ ሽል የሚቀመጥበት ስስ የሆነ ከረጢት፤ ከርታስም ይባላል።

**ሰፌድ** ስ ከአክርማ፥ ከሰንደዶና ከገራምጣ የሚሰራና ለእህል ማበጠሪያና ማንፊሻ እንዲሁም ከምጣድ ላይ ለእንጀራ ማውጫ የሚያገለግል ስፌት (ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)።

**ሰፌድ እግር** ቅ ውስጥ እግሩ ጠፍጣፋ የሆነ (ሰው)።

**ሰፍሳፋ** "*ሰፈሰፈ" ስር ተመ.

**ሰፍነግ** ስ 1. ውሃን በውስጡ መቋጠር የሚችልና በባህር ውስጥ የሚገኝ እንደ ስፖንጅ ያለ የእፅዋት አይነት። 2. ስፖንጅ።

**ሱ** የ"ሰ" ፊደል ካእብ ዘር።

**ሱልጣን** ስ በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ሃይማኖታዊ ስልጣን ያለው ሹም ወይም ለሹሙ የሚሰጠው የማእረግ ስም።

**ሱረት** ስ በጉንጭ የሚያዝ ወይም በአፍንጫ የሚሸተት የትምባሆ ዱቄት።

**ሱሪ** ስ እያንዳንዱን እግር ለየብቻ እንዲሸፍን ሆኖ የተዘጋጀ ከወገብ እስከ ቁርጭምጭሚት ወይም እስከ ጉልበት የሚደርስ ልብስ (ስእሉን ልብስ ስር ተመ.)።

**ሱስ** ስ 1. አንዱ ከተለመደ በሃላ በየጊዜው ውል የሚል ወይም የሚያሰኝ እንደትምባሆ፥ ቡና የመሳሰሉት ነገሮች ልማድ፥ አመል፥ አምሮት። 2. (ዘይ.) ልማድ፥ አመል፥ ፍቅር (አንድን ነገር የማድረግ)።

**ሱሰኛ** ቅ ሱስ ያለበት፥ ሱስ የያዘው።

**ሱቅ** ስ ልዩ ልዩ ሸቀጣሸቀጦች ወይም እቃዎች የሚሸጡበት ቤት፤ መደብር።

**ሱቅ በደረቴ** ስ ሸቀጣ ሸቀጦችን በሻንጣ ወይም በአነስተኛ ሳጥን እየያዘ በመዘዋወር የሚሸጥ አነስተኛ ነጋዴ።

**ሱባኤ** ስ 1. ለተወሰነ ጊዜ ከሰው ተለይቶ የሚደረግ ፆም፥ ፀሎትና ስግደት፤ ቀኖና። 2. (ቤ.ክህ.) የሰባት ቀን ጊዜ።

**ሱባኤ ገባ/ያዘ** 1.ለተወሰነ ጊዜ ከሰው ተለይቶ ፆምና ፀሎት፥ ስግደት አደረገ፥ ቀኖና ያዘ። 2. ከሰው ተለይቶ ተቀመጠ፥ ተደበቀ።

**ሱቲ** ስ ዝንጉርጉርና መናኛ የጨርቅ አይነት።

**ሱጎ** "ስጎ" ን ተመ.

**ሱፋጭ** ስ ስለት ያለው ድንጋይ፤ ሻፎ።

**ሱፍ**[1] ስ ቢጫ አበባ ያለውና ፍሬው የመብል ዘይት የሚወጣው ሰብል። ከዚሁ ሰብል የሚገኘው ነጭ ፍሬም ሱፍ ይባላል።

**የሱፍ ውሃ** ስ ከተወቀጠና ከተቀቀለ የሱፍ ፍሬ የሚዘጋጅ፥ ለመጠጥነትና ለማባያነት የሚያገለግል ፈሳሽ።

**ሱፍ**[2] ስ ከበግ ፀጉር የሚሰራ ጨርቅ።

**ሲ** የ"ሰ" ፊደል ሳልስ ዘር።

**ሲ** - "ስ-" ን ተመ.

**ሲሊንደር** ስ ሞላላ ቅርፅ ያለውና ቡታጋዝ፥ ኦክስጅን፥...የሚሞላበት ከብረት የተሰራ እቃ።


**ሲላ** ስ ጫጩትን፥ ርግቦችን፥ ወፎችን እየጠለፈ የሚበላ የጭልፊት አይነት፤ አሞራ። (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

**ሲል**

2



3




1




4



5



6





9



7



10



1.ሙሙ
2.ወንፊት
3.ሙዳይ
4.መሶብ ወርቅ
5.ቃጤ

6.ሌማት
7.ቁና
8.አገልግል
9.እርቦ
10.ሰፌድ

**ሲል አለ** ግ ታንቆ፥ ተንጠልጥሎ፥ ተሰቅሎ ሞተ::

**ሲሚንቶ (ስሚንቶ)** ስ ከኖራና ከሸክላ አፈር በፋብሪካ ውስጥ ተዘጋጅቶ የሚወጣና ለግንባታ ስራ የሚያገለግል ዱቄት::

**ሲምፎኒ** ስ በተለያዩ ብዙ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚቀነባበርና 3 ወይም 4 ክፍሎች የሚኖሩት የሙዚቃ ድርሰት::

**ሲሪንጅ (ሲሪንጋ)** ስ ቱቦ የሚመስልና ጫፉ ሹል የሆነ፥ በውስጡ ፈሳሽ መድሃኒትን ለመያዝና በደም ስር ለማስተላለፍ የሚያገለግል የህክምና መሳሪያ::



ሲሪንጅ

**ሲራራ**

**ሲራራ ነጋዴ** ስ የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦችን በአጋሰስ፥... ጭኖ ከሃገር ወደ ሃገር እየሄደ የሚነግድ (ነጋዴ)::

**ሲራክ[1]** ቅ ብልህ፥ አዋቂ::

**ሲራክ[2]** ስ በወረቀትና በብራና ገፅ ላይ ፅሁፍ የሚያርፍበት ቦታ ወይም መስመር::

**ሲር** ስ ከተለፋ ቆዳ በቀጭኑ ተቀዶ የሚወጣ የኮርቻ፥ የስልቻ ወይም ሌላ የቆዳ እቃ መስፊያ ወይም ከበሬ ማጅራት ላይ የሚወጣ ጅማት::

**ሲርሲርታ** ስ 1. ሲር ሲር የሚል ድምፅ:: 2. ከሳል ወይም ከ[illegible] የጉሮሮ ህመም የተነሳ የሚመጣ ሲር ሲር የሚል የአተነፋፈስ ሁኔታ::

**ሲሳይ** ስ 1. ምግብና መጠጥ፥ ሃብት የመሳሰለው ጠቀሜታ ያለው ነገር:: 2. ጥሩ እድል::

**ሲስተር** ስ ሴት ነርሶች የሚጠሩበት ሙያን የሚያመለክት ስም::

**ሲሶ** ቅ ከሶስት አንድ እጅ ወይም አንድ ሶስተኛ::

**ሲሶ አራሽ** ስ ከተገኘው ምርት ከሶስት አንድ እጅ ለመስጠት በመዋዋል የሌላን ሰው መሬት የሚያርስ ገበሬ::

**ሲቃ** ስ ከመሮጥና ከመድከም፥ ከንዴት፥... የተነሳ የሚመጣ እንቅ እንቅ የሚያደርግ አተነፋፈስ::

**ሲቃ ያዘው** ከመሮጥ፥ ከመድከም፥ ከእልህ፥... የተነሳ ትንፋሹ እንቅ እንቅ አለ::

**ሲቢጣ** ቅ በጣም ቀጭንና አጭር የሆነ፥ ለአይን የማይሞላ (ሰው)::

**ሲባጎ** ስ 1. ቀጭንና ጠንካራ ገመድ:: 2. (ዘይ.) ቀጭንና መጣጣ የሆነ (ሰው)::

**ሲኒ (ስኒ)** ስ ለቡና፥ ለሻይ፥... መጠጫ የሚያገለግል የሸክላ እቃ::

**ሲኒ ማስቀመጫ** ስ ሲኒን በላዩ ላይ ለማስቀመጥ ከሲኒው ጋር አብሮ የሚዘጋጅ ሰሃን መሰል እቃ::

**ሲኒማ** ስ በፊልም ተቀርፆ በፕሮጀክተር አማካይነት በኤሌትሪክ ሃይል እየተንፀባረቀ በነጭ ሰሌዳ ላይ የሚታይ የማንኛውም ነገር የሚንቀሳቀስ ምስል::

**ሲኒማ ቤት** ስ ህዝብ እየተሰበሰበ ገንዘብ ከፍሎ ሲኒማ እንዲመለከትበት የተዘጋጀ አዳራሽ፣ ፊልም ቤትም ይባላል::

**ሲናር** ስ ከገብስ ጋር የሚበቅልና ገብስ የሚመስል አረም::

**ሲኖዶስ** ስ 1. ጳጳሳትና ካህናት ስለቤተክርስቲያን አገልግሎት፥ ህግና ስርአት ለመወያየትና ውሳኔ ለመስጠት የሚያደርጉት ስብሰባ ወይም ጉባኤ:: ውሳኔውም ሲኖዶስ ይባላል:: 2. እስከ መካከለኛው ዘመን የተደረጉትን የሲኖዶስ ውሳኔዎች ይዞ የሚገኝ መፅሃፍ::

**ሲኦል** ስ 1. ክፉ የሰሩ ሰዎች እስከ እለተምፅአት ይኖሩበታል የሚባል የስቃይና የመከራ ቦታ:: 2. (ዘይ.) አስፈሪ፥ አስጨናቂ፥ መጥፎ ጨለማ፥... የሆነ::

**ሲካካ [ዶሮ]** ስ እንቁላል የምትጥልና የምታስካካ ዶሮ::

**ሲውሲዋ** ስ ከፍ ያለ የዶሮ ጫጩት::

**ሲጋራ(ሲጃራ)** ስ በስስ ወረቀት ተጠቅሎ የሚጨስ ደረቅ ትምባሆ::

**ሲጋራ ያጨሳል/ ይጠጣል** ሲጋራን በእሳት በመለኮስ ጪሱን ይምጋል::

**ሲጋራ መተርኮሻ** ስ የሲጋራን አመድ ለማራገፍና ቁራጩን ለመጣያ እንዲሆን ተብሎ የተዘጋጀ እቃ::

**ሲጢጥ አለ** ግ "*ሰጠጠ" ስር ተመ.

**ሲጥ**

**ሲጥ አለ** ግ 1.አይጥ እንደምታሰማው ያለ ጩሀት አሰማ:: 2. ሞተ::

**ሲጥ[2]**

**ሳ** የ "ሰ" ፊደል ራብእ ዘር::

**ሳ__** "ስ-" ን ተመ.

**-ሳ** "-ስ" ን ተመ.

**ሳህን (ሰሃን)** ስ ከሸክላ ወይም ከቆርቆሮ ወይም ከፕላስቲክና ከመሳሰሉት የሚሰራ የምግብ ማቅረቢያ እቃ::

**ሳለ[1]** ግ የአንድን ነገር መልክ፥ ቅርፅ ወይም አንድን አይነት ሃሳብ በስእል አሳየ፣ ምስሉን በወረቀት፥ በሸራ፥ በግድግዳ፥ ወዘተ. ላይ ቀረፀ፥ አሰፈረ፥ ነደፈ::

**ሰአሊ** ስ የስእል ባለሙያ::

**ስእል** ስ ለአይን እንዲታይ ተደርጎ በወረቀት፥ በሸራ፥ በግድግዳ ወዘተ. ላይ በእርሳስ፥ በብሩሽ ፥በብእር...የተሰራ፥ የተነደፈ ወይም ከጠጣር ነገር የተቀረፀ የአንድ ነገር ወይም ሃሳብ፥ መልክ፥ ቅርፅ፥ ምስል።

**ስእል ሰራ** ስእልን በወረቀት፥ በሸራ፥... ላይ ነደፈ፥ ሳለ።

**ስእል አነሳ** አንድን መልክ፥ ፎቶግራፍ፥... አስመስሎ ነደፈ፥ ሳለ።

**ስእል የመሰለች** እጅግ ቆንጆ፥ መልከ መልካም (ሴት)።

**ሳለ**[2] ግ ሞረደ፥ አሾለ፥ አተባ፥ ስለት አወጣ።

**መሳል** ስ ለመሳያ፥ ለመሞረጃና ለስለት ማውጫ የሚያገለግል ሻካራ ድንጋይ፤ ለሆቴ።

**ስል** ቅ የተሳለ፥ የተሞረደ፥ ስለት ያለው።

**ስለት** ስ 1. የቢላዋ፥ የጎራዴ፥... አፍ ወይም የሚቆርጠው ወገን። 2. እንደቢላዋና ሰንጢ የመሳሰለ ለመቁረጥ የሚያገለግል መሳሪያ።

**ስለት አወጣ** 1. ስል አደረገ፥ አተባ፥ ሞረደ። 2. ስል ሆነ፥ ተባ።

**ስለታም** ቅ ስለት ያለው፥ በቀላሉ መቁረጥ የሚችል (ቢላዋ፥ ሰንጢ፥...)።

**ሳለ**[3] ግ ከጉንፋን ወይም ከሌላ ሁኔታ የተነሳ ከጉሮሮ አየርን በሃይልና በተደጋጋሚነት አስወጣ፤ ኡሁ ኡሁ አለ።

**ሳል** ስ ከጉንፋን ወይም ከሌላ በሽታ የተነሳ ትክ ትክ የሚያደርግ፥ ኡሁ ኡሁ የሚያሰኝ ህመም።

**ሳል ተከለበት** ሳል ፈጠረበት፥ ሳል ያዘው።

**አሳለ** ግ ትክትክ አደረገ፥ ኡሁ ኡሁ አሰኘ፤ ሳለ። *ጉንፋኑ በጣም አሳለው።*

***ሳለ**

**ስእለት(ስለት)** ስ ይህን ካደረክልኝ ይህን አደርግልሃለሁ በማለት ለአምላክ፥ ለመላእክት፥... የሚቀርብ ልመና፥ ብፅአት።

**ስለቱ ደረሰ** የለመነው፥ የጠየቀው ተሟላለት።

**የስለት ልጅ** በብፅአት፥ በልመና፥ በስለት የተወለደ ልጅ።

**ተሳለ** ግ ይህን ካደረክልኝ ይህን አደርግልሃለሁ በማለት ለአምላክ፥ ለመላእክት፥... ልመና፥ ብፅአት አቀረበ።

**ሳለ (ካለ)**

**ሳለ አይሰጥ (ካለ አይሰጥ)** ስ ስጋውን ከላዩ ላይ እንደ ልብ ለመጋጥ የማያመች የአከርካሪ አጥንት።

**ሳሳ** ስ ቀጥ ብሎ የረዘመና የሾለ ባለከርከራት ቀንድ ያለው ሳረበል የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ሳሳይሽ** ስ በፋብሪካ የተመረተ የማግ አይነት።

**ሳሌ** ስ ከጋን አነስ ከእንስራ ተለቅ የሚል የሸክላ እቃ።

**ሳል** "ሳለ[3]" ስር ተመ.

**ሳልሳ** ስ በቆርቆሮ የታሸገ የቲማቲም ድልህ።

**ሳልሳዊ** "ሰለሰ" ስር "ሳልሳይ"ን ተመ.

**ሳልሳይ** "ሰለሰ" ስር ተመ.

**ሳልስ** ዝ.ክ.

**ሳልስት** "ሰለሰ" ስር "ሰልስት" ን ተመ.

**ሳልስትና** "ሰለሰ" ስር ተመ.

**ሳሎን** ስ በዘመናዊ ቤት ውስጥ ለእንግዳ መቀበያ የተሰራ ክፍል።

**ሳመ** ግ ፍቅርን፥ ናፍቆትን፥ አክብሮትን፥ ሰላምታን ለመግለፅ ወይም ለመማፀን የሌላን አካል በከንፈሩ ነካ፥ ጨመጨመ።

**ሳሙና** ግ 1. ከሞራና ከልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች የሚሰራ፥ ቆሻሻን ለማስለቀቅ የሚረዳ አረፋ የሚወጣው የገላ፥ የልብስና የሌላም እቃ ማጠቢያ። ቅ 2. ፈገግ ያለ (የበቅሎ መልክ)። 3. (ዘይ.) ሞላጫ፥ አታላይ።

**ሳሙና መታ** ሳሙና ቀባ፥ በሳሙና ፈገፈገ።

**ሳማ** ስ ቅጠሉ የሚለበልብ ጥቃቅን እሾህ ያለበትና በአንዳንድ አካባቢ እየተቀቀለ የሚበላ የእፅዋት አይነት።

**ሳምቡሳ** "ሳንቡሳ" ን ተመ.

**ሳምባ** " ሳንባ" ን ተመ.

**ሳምንት** ስ 1. የሰባት ተከታታይ ቀናት ጊዜ። 2. ከሰኞ ጀምሮ እስከ እሁድ የሰባት ቀናት ጊዜ። 3. ስምንተኛ ቀን።

**ሳምንታዊ** ቅ በየሳምንቱ የሚደረግ፥ የሚወጣ፥...።

**ሳር** ስ ለከብት ግጦሽና ለቤት ክዳን፥ ለጉዝጓዝ፥... የሚውል እንደ እንግጫ፥ ሰርዶ፥ ሙጃና ስንበሌጥ የመሳሰለው ሁሉ።

**ሳረበል** ቅ ሳር የሚበላ (እንስሳ)።

**ሳርቅጠሉ** ሁሉም ነገር፥ ሁሉም ሰው።

**ሳር ቤት** ስ ብዙውን ጊዜ ግርግዳው ክብ ሆኖ የሚሰራ ጣሪያው በሳር የሚከደን ጎጆ።

**ሳርያን** ስ የኮት ቅድና አሰፋፍ አይነት።

**ሳሳ**[1] ግ 1. ስስ ሆነ፥ ቀጠነ። 2. ተራራቀ (የዘር አዘራር ወይም የሰብል አበቃቀል)። 3. በመነቃቀል፥ በማለቅ፥ ለመመለጥ ደረሰ (ፀጉር)።

**ስስ** ቅ 1. ውፍረት የሌለው፥ ደንዳና ያልሆነ፥ ቀጭን። 2. የተራራቀ (የቡቃያ አበቃቀል)።

**ኣሳሳ** ግ 1. ስስ አደረገ። 2. አራራቀ (ዝሪትን)። 3. ፈለቀቀ፥ ጥጥፍሬውን በማውጣት አፀሰለሰ (ጥጥን)።

**ሳሳ**[2] ግ 1. ሰሰተ፥ ተስገበገበ። 2. አዘነ፥ ራራ።

**ስሱ** ቅ 1. ንፉግ፥ ስግብግብ፥ ስስታም።2. አዛኝ፥ ሩህሩህ።

**ስስት** ስ ንፍገት።

**ስስታም** ቅ ንፉግ፥ ቀብቃባ።

**ኣሳሳ** ግ 1. ኣጓጓ፥ አስጎመጀ። 2. ኣሳዘነ።

**ሳቀ** ግ ፊቱን ፈገግ በማድረግና ድምፅ በማሰማት ደስታውን ገለፀ፥ ፈነደቀ፥ ተንከተከተ።

**መሳቂያ** ቅ ማፌዣ፥ ማላገጫ፥ ማሾፊያ።

**ሳቂታ** ቅ ሳቅ የሚያበዛ፥ ደስተኛ።

**ሳቅ** ስ ፈገግ በማለት፥ በመንከትከት፥...የሚገለፅ የደስታ፥ የመገረም፥...ስሜት።

**በሳቅ ፈረሰ** በጣም ሳቀ፥ ተንከተከተ።

**ሳቁ መጣ** ሊያስቀኝ ደረሰ።

**በሳቅ ፈነዳ** በጣም ሳቀ፥ተንከተከተ።

**ተሳቀበት** በተናገረው፥ ባደረገው ነገር አድማጩ ወይም ተመልካቹ መደሰቱን፥ መገረሙን በመሳቅ ገለፀለት።

**ተሳቀበት** ተፌዘበት፥ ተላገጠበት።

**ኣሳቀ** ግ 1. ሳቅ ፈጠረ፥ አንከተከተ። 2. (የምፀት አነጋገር) አስገረመ፥ አስደነቀ።

**ኣስቂኝ** ቅ 1. የሚያስቅ፥ የሚያንከተክት፥ ሳቅ የሚያስመጣ። 2. ቧልተኛ፥ ቀልደኛ።

**ኣሳሳቀ** ግ 1. ኣጫወተ፥ አዝናና። 2. አዋዛ፥ አታለለ።

**ሳበ** ግ 1. ጎተተ፥ ወደራሱ አስጠጋ። 2. እየጎተተ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ኣጓጓዘ። 3. ስሜትን ያዘ፥ አማረ፥ ማረከ። 4. መጠጠ፥ ማገ። 5. ጠራ፥ አመጣ (ሰይጣንን)። 6. ወጠረ፥ ገተረ።

**መሳቢያ** ስ 1. እንደኮመዲኖ፥ ጠረጴዛ፥ ቁምሳጥን በመሳሰሉ እቃዎች ላይ የሚገጠም፥ እየተሳበ የሚወጣና እየተገፋ የሚገባ እጀታ ያለው የእቃ ማስቀመጫ ኪስ። 2. ለአረቄ ማውጫ የሚያገለግል በገመድ የተጠቀለለ ቀርቀሃ።

**ሳቢዘር** ስ (ሰዋ.) ኣኳሂንን ወይም አደራረግን የሚገልፁ ቃላት። ኣየፍ፥ አካሄድ፥ አያያዝ፥... የመሳሰሉት ቃላት ቅርፅ ሳቢ ዘር ይባላል።

**ሳቢያ** ስ 1. ሰበብ፥ መነሻ ምክንያት። *በእሱ ሳቢያ መጣ።* 2. ዋናው አረቄ ከወጣ በሂላ ዳግመኛ የሚወጣው የአረቄ ቅራሪ። 3. የክረምቱን ጊዜ ረዘም አድርጎ በተጨማሪ የሚዘንብ ዝናብ። *ዘንድሮ ሳቢያ ዝናብ ኣለ።*

**ስበት** ስ 1. ኣንድን አካል ከላይ ወደታች የሚያመጣ፥ የሚስብ ሃይል። 2. ማግኔትነት ያለው ነገር ወይም አካል፥ ብረትን ወይም ሌላ አካልን የመጎተት ወይም የመሳብ ሃይል።

**ተሳበ** ግ 1. ቀስ እያለ እየተጎተተ ተጓዘ፥ ተጠጋ። 2. ተማረከ፥ ስሜቱ ተያዘ። 3. እየተወጠረ እንደ ፕላስቲክ ተለጠጠ። 4. እየተጎተተ ወይም እየተንሰራፋ ሄደ፥ረዘመ (የሃረግነት ፀባይ ያለው እንደ ዱባ፥ ቅል ያለ ተክል)።

**ተሳቢ** ስ 1. የተሻጋሪ ግስ ድርጊት የሚያርፍበት ወይም የሚፈፀምበት ስም ወይም ተውላጠ ስም።"ተማሪው "መፅሃፉን ኣነበበ" በሚለው ኣረፍተ ነገር ውስጥ "መፅሃፍ" ተሳቢ ነው። 2. በመኪና ሂላ የሚቀጠል የእቃ ማጓጓዣ፥ ተጎታች።

**ተሳሳበ** ግ በዝምድና፥ በወዳጅነት፥...ተጠራራ፥ ተገናኘ፥ ተደጋገፈ።

**ሳቢሳ** ስ ብዙ እየሆነ ከከብት ጋር ወንዝ ዳርና ውሃማ በሆነ ቦታ ላይ የሚሰማራ፥ መልኩ ነጭ፥ ቅልጥሙ ዘለግ ያለ ኣሞራ (ስእሉን ኣሞራ ስር ተመ.)።

**ሳቢያ "ሳበ"** ስር ተመ.

**ሳብእ** ስ እንደ "ሆ"፥ "ሎ"፥ "ሞ"፥... ያሉና ከሳድስ ዘር ቀጥሎ የሚገኙ ሰባተኛዎቹ የፊደላት ዘሮች መጠሪያ ወይም የድምፅ ምልክት።

**ሳተ** ግ 1. ኣላማውን፥ ኢላማውን ሳይመታ፥ ሳያገኝ ቀረ። 2. ረሳ፥ ዘነጋ። 3. (ዘይ.) ከእርጅና፥ ከህመም የተነሳ ሽንትን፥ አይነ ምድርን መቆጣጠር ኣልቻል ኣለ። 4. ትክክለኛ አቅጣጫውን፥ መንገዱን፥ ቦታውን፥ አድራሻውን አጣ።5. ሃጢኣት ሰራ።6. ኣእምሮውን፥ ራሱን፥...መቆጣጠር፥ ማወቅ፥ መግዛት፥... ተሳነው። *በደረሰበት ኣደጋ ሀሊናውን ሳተ።*

**ስህተት** ስ 1. ትክክለኛ ያልሆነ ስራ፥ መልስ፥ ነገር፥...። 2. ጥፋት፥ እንከን።

**ስህተቱን ኣረመ** የተሳሳተውን አስተካከለ።

**ስህተት ሰራ** ተሳሳተ።

**ስህተተኛ** ቅ 1. ትክክለኛ ያልሆነ። 2. ጥፋተኛ፥ ሃጢኣተኛ፥ በደለኛ።

**ተሳተ** ግ 1.ተረሳ፥ ተዘነጋ። 2. ታለፈ፥ ተዘለለ።

**ተሳሳተ** ግ 1. ትክክለኛ ያልሆነ መልስ ሰጠ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ስራ ሰራ። 2. ትክክለኛ ኣድራሻውን ኣጣ። 3. ተሳከረ፥ ተፋለሰ፥ ተዛነፈ። 4. ስህተተኛ ሆነ። 5. ሃጢኣት፥ በደል፥ ጥፋት ሰራ።

**ኣሳተ** ግ ሃጢኣት እንዲሰራ አደረገ።

**አሳቻ** ቅ 1.የሚያሳስት፥ አደናጋሪ (አቅጣጫ፥ በታ፥ መንገድ፥...)። 2. አይን የማይገባ፥ ለአይን የማይመስል። 3. ሰዋራ፥ ድብቅ (በታ)።

**አሳሳተ** ግ 1. ስህተት እንዲሰራ አደረገ፥ ገፋፋ፥ አደፋፈረ። 2. አዛባ፥ አሳከረ። 3. አደናገረ፥ አጭበረበረ፥ አወናበደ። 4. ሃጢአት፥ ስህተት፥ በደል አሰራ ወይም እንዲሰራ አደረገ።

**አሳሳች** ቅ 1. የሚያሳስት፣ ሃጢአት፥ ክፉ ነገር እንዲሰራ የሚገፋፋ። 2. ትክክለኛ ያልሆነ ነገር እንዲሰራ የሚያደርግ፥ የሚገፋፋ። 3. ውስብስብ፣ ተመሳሳይ የሆነና ለመረዳት፥ አንዱን ከአንዱ ለመለየት፥ ለማስታወስ ወይም በትክክል ለመስራት የሚያስቸግር፥ የሚያደናግር። ስ 4. የንጉስ ልብስ ወይም የሙሽራ ልብስ የሚመስል በመልበስ ከንጉሱ ወይም ከሙሽራው ጎን በመቆም ትክክለኛው እንዳይታወቅ የሚያደናግር ሰው።

**ሳተላይት** ስ 1. በመሬትና ሌሎች ፕላኔቶች ዙሪያ የሚሽከረከር፥ ተፈጥሯዊ አካል። ጨረቃ በመባልም ይታወቃል። 2.በመሬትና በህዋ ውስጥ በሚገኙ አካላት ዙሪያ የሚሽከረከር፥ ለመገናኛ፥ ለምርምርና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውል ሰው ሰራሽ አካል።

**ሳተርን** ስ ከፀሃይ ጀምሮ ሲቆጠር በርቀት ስድስተኛ ተራ ላይ የሚገኝና በዙሪያው ቀለበቶች ያሉት፥ በፀሃይ ዙሪያ ከሚሽከረከሩት ፕላኔቶች አንዱ (በተጨማሪ ፕላኔትን ተመ.)።

**ሳተነ** ግ ፈጠነ፣ ተንቀዠቀዠ።

**ሳተና(ሳታና)** ቅ ፈጣን፥ ቀልጣፋ፥ ከተፍ፣ ቀዥቃዣ።

**ሳታት** "ሰአት" ስር "ሰአታት" ን ተመ.

**ሳታና** "ሳተነ" ስር "ሳተና" ን ተመ.

**ሳንሱር** ስ ፅሁፎች፥ ፊልሞች፥ ሙዚቃዎች፥... ለህዝብ ከመቅረባቸው በፊት በፖለቲካና በሞራል በኩል የሚያስከትሉት ችግር እንዳለ የሚደረግ ምርምራ፥ ቁጥጥር፣ ቁጥጥሩን የሚያደርገው ክፍልም ሳንሱር ይባላል።

**ሳንሳ (ወሳንሳ)** ስ 1. ለሁለት ወይም ከዚያ በላይ በአንድነት ሆነው በአጣና ወይም በቃሬዛ የሚሸከሙት ሸክም። 2. ለአንድ ሰው የሚከብድን ነገር (ሀመምተኛን፥ ሬሳን፥...) ለሁለት ለማንሳትና በትከሻ ለማጓጓዝ የሚያስችል መሸከሚያ እንጨት፣ ቃሬዛ።

**ሳንቃ**[1] ስ ለመዝጊያ፥ ለወለል ወይም ለሌላ የእንጨት ስራ እንዲሆን ከትልቅ ዛፍ በስሱ እየተሰነጠቀ ወይም እየተጠረበና እየተላገ የሚወጣ እንጨት።

**ሳንቃ**[2] ስ ከብር፥ ከወርቅ፥... የሚሰራና በደረት በኩል የሚሆን የለምድ ወይም የካባ ማያያዣ።

**ሳንቡሳ (ሳምቡሳ)** ስ የፋርኖ ዱቄት ሊጥ ተዳመጠ ከበሰለ በሃላ በውስጡ ብዙውን ጊዜ የበሰለ ምስር ወይም ስጋ እየተደረገና በሶስት ማእዘን እየተጠቀለለ በዘይት ተጠብሶ የሚዘጋጅ ምግብ።

**ሳንባ (ሳምባ)** ስ በሰውና በእንስሳት ደረት ውስጥ የሚገኝ፥ አየር ለመሳብና ለማስወጣት የሚረዳ የመተንፈሻ አካል።



ሳንባ (ሳምባ)

**ሳንባ ቀለም** ስ የሳንባን መልክ የሚመስል ቀለም።

**ሳንባ ነቀርሳ** ስ ሳንባን የሚያቆስል ተላላፊ በሽታ።

**ሳንባ አቃፊ** ስ ሳንባን አቅፎ የሚይዝ የሰውነት ውስጣዊ አካል።

**ሳንቲ ሜትር** "ሴንቲ ሜትር" ን ተመ.

**ሳንቲም** ስ 1. በጥቅል ወይም በዝርዝር የሚገኝ የብር ክፍልፋይ (መቶ ሳንቲም አንድ ብር ይሆናል)። 2. ገንዘብ። *ሳንቲም የለኝም።*

**ሳንቲም የለውም** ምንም ገንዘብ የለውም።

**ሳንካ (ሳንክ)** ስ ጥፋት፥ እንከን።

**ሳንዱቅ (ሰንዱቅ)** ስ የልብስ፥ የእቃ ማስቀመጫ ሳጥን።

**ሳንድዊች** ስ ዳቦ ከሁለት በታ ላይ ተሰንጥቆ የተጠበሰ ስጋ ወይም እንቁላል ወይም ልዩ ልዩ አትክልቶች በውስጡ ተጨምረውበት የሚዘጋጅ የምግብ አይነት።

**ሳንጃ** ስ በጠመንጃ ጫፍ ላይ የሚሰካና ጫፉ ሹል የሆነ ስለታም ጩቤ።

**ሳካ** ስ እንከን፥ ጉድለት፥ ነውር፣ ሳንካ፥ ሳንክ።

**ሳክስፎን** አፉ አካባቢ ባለች ቀጭን ተውለብላቢ ብረት አማካይነት ለሚፈጠረው ድምፅ ልዩ ልዩ ቃና ለመስጠት የሚያስችሉ ቁልፎች ያሉት በትንፋሽ የሚሰራ የሙዚቃ መሳሪያ (ስእሉን ሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

**ሳይንስ** ስ 1. ንድፈ ሃሳቦች፥ ህጎች፥ መላምቶች፥... ተጨባጭ በሆነ መንገድ በምክንያታዊነት እየተረጋገጡ ስለ ተፈጥሮና ስለ ህብረተሰብ ጥናት የሚደረግበትና የሚከማችበት የእውቀት ዘርፍ።2. ስለተፈጥሮ ማስተዋልና ሙከራ የሚደረግበት የትምህርት፥ የእውቀት፥ የምርምር መስክ።

**ሳይንሳዊ** ቅ ትክክለኛ የሆነ፥ በሙከራ፥

በማስተዋል፥በምክንያታዊነት የተደገፈ የአጠናንና የምርምር መንገድን የተከተለ።

**ኢሳይንሳዊ** ቅ ሳይንሳዊ የሆነ መንገድን ያልተከተለ።

**ሳይኮሎጂ** ስ ስለ አእምሮ ሁኔታና ጠባይ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ፤ ስነ አእምሮ፥ ስነ ልቡና።

**ሳዱላ** ስ 1. በገጠር አካባቢ ልጃገረዶች መሃል ራሳቸው ላይ በክቡ የሚላጩት አለማጨት። 2. ላለማግባቷ ምልክት እንዲሆን መሃል ራሷ ላይ ፀጉሯን በክቡ የተላጨች ልጃገረድ። 3. ልጃገረድ።

**ሳድስ** ስ እንደ ሀ፥ ል፥ ም፥ ... ያሉ በሃምስና በሳብእ መካከል የሚገኙ ስድስተኛዎቹ የፊደላት ዘሮች መጠሪያ ወይም የድምፅ ምልክት።

**ሳገ** ግ ሸጠ፥ ሰካ።

**ሳጋ** ስ ክፍተት ባላቸው በግድግዳ እንጨቶች መካከል የሚሰካ ወይም የሚሸጥ አጠር ያለ እንጨት፥...። 2. ለቤት ግድግዳ የሚሆን ፍልጥ።

**ተሳገ** ግ ተሸጠ፥ ተሰካ።

**ሳጠራ** ስ 1. ከሸንበቆ ወይም ከቀርከሃ የሚሰራ ምንጣፍ፤ አቴና። 2. ከሸንበቆ ወይም ከቀርከሃ የሚሰራ እንደ ወንበር፥ ጠረጴዛ፥ ሌማት፥... ያለ እቃ።

**ሳጥን** ስ 1. ከእንጨት ወይም ከብረት ወይም ከሌላ ነገር የተበጀና ብዙውን ጊዜ አራት ማእዘንነት ያለው የልብስ፥ የእቃ፥... ማስቀመጫ፤ ሳንዱቅ። 2. በሳጥን መልክ ወይም ቅርፅ የተዘጋጀ ሌላ ማንኛውም ነገር። 3. በውስጡ እንዲፃፍበት፥ ለተለያዩ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥበት ወይም ምልክት እንዲደረግበት በወረቀት ላይ የተዘጋጀና በአራት ማ እ ዘ ን የተከበበ ወይም የታጠረ ክፍት ቦታ (□)።

**ሳፊ** ቅ 1.ሙሉ፥ ያልጎደለ።2. ያልተበረዘ፥ ያልተቀላቀለ።

**ሳፊ ወተት** ስ ከሻይ ወይም ከቡና ጋር ያልተደባለቀ ንፁህ የፈላ ወተት።

**ሳፋ** ስ ለልብስ ማጠቢያ የሚያገለግል ሰፊና ጎድጓዳ የሆነ የቆርቆሮ ሳህን።

**ሴ** የ "ሰ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**ሴል** ስ ህይወት ባላቸው አካላት ውስጥ የሚገኝ፥ ከህይወት ክፍልፋዮች ውስጥ የመጨረሻው ትንሹ ክፍል የሆነና ያለ ማጉያ መነፅር የማይታይ ህዋስ።

**ሴሚናር** ስ በተወሰኑ ርእሶች ላይ የጥናት ፅሁፎችን በማቅረብ ከተሳታፊዎቹ ጋር ውይይት ለማካሄድ ወይም በተወሰነ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ፥ ገለፃ ለማድረግ የሚደረግ ስብሰባ።

**ሴረኛ** "*ሰየረ" ስር ተመ.

**ሴራ** ዝ.ከ.

**ሴሰነ** ግ አመነዘረ፥ ሸረሞጠ።

**ሴሰኛ** ቅ አመንዝራ፥ ሸርሙጣ፥ ቅንዝረኛ።

**ሴት** ስ 1. እንስት፤ ከወንዱ የተለዩ የተፈጥሮ ምልክቶችና ባህርያት ያሏት ሰው። 2. የልጃገረድነት ወጓን የጨረሰች ወይም ድንግልና የሌላት ሰው። ቅ 3. የተፈጥሮ የእንስትነት ምልክቶችና ባህርያት ያሏት (እንስሳ፥ ወፍ፥...)። 4. (ዘይ.) ፈሪ።

**ሴት ተወ** የግብረ ስጋ ግንኙነት አቆመ።

**ከሴት ደረሰ** የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀመ (ወንድ)።

**ሴተላጤ** ስ ያለባል ብቻዋን የምትኖር ሴት።

**ሴታሴት** ወንድ ሆኖ የሴትነት ጠባይ የሚታይበትና መሽቀርቀርና መኳኳል የሚያበዛ።

**ሴት አኩሪ** ስ እንደ ኮባ ለዳቦ መጋገሪያነት የሚያገለግልና ቅጠሉ መጠነኛ ስፋት ያለው አነስተኛ የተክል አይነት።

**ሴት አውል** ስ ብዙውን ጊዜ ከሴቶች ጋር መሆን ወይም መዋል የሚወድ (ወንድ)።

**ሴት አያት** ስ የአባት ወይም የእናት እናት።

**የሴቶች ገና** ስ ከገና በፊት ያለው ቀን ወይም የገና ዋዜማ።

**ሴተኛ አዳሪ** ስ በሽርሙጥና የምትተዳደር ሴት፥ ሸርሙጣ ።

**ሴቴ** ቅ ያታዋ ሴት የሆነ (እፅ፥ ተክል፥...)።

**ሴቴ ዘር** ስ ከወንዱው ዘር ጋር ተዋህዶ ፅንስ ለማፍራት የሚችል ከሴቷ የሚገኘው ዘር።

**ሴትነት** ስ የሴት ሙያ ወይም ባልትና።

**ሴንቲሜትር (ሳንቲ ሜትር)** ስ የርዝመት መለኪያ። 100 ሴንቲ ሜትር 1 ሜትር ይሆናል።

**ሴንቲ ግሬድ** ስ የሙቀት ወይም የቅዝቃዜ መጠን መለኪያ። $100^0$ ሴንቲ ግሬድ $212^0$ ፋራናይት ይሆናል።

**ሴንጢ** "ሰንጢ" ን ተመ.

**ሴኮንድ** "ሰኮንድ" ን ተመ.

**ሴደር** ስ የቀደና የነጭ መቀነትማ ምልክት ያለው የከብት መልክ።

**ስ** የ "ሰ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**ስ-** ከ "ይ" ድምፅ በፊት ሲገባ "ሲ-"፥ ከ"ኣ" ድምፅ በፊት ሲገባ "ሳ" ይሆናል። በግስ ላይ በስተመነሻ እየገባ ግስን ከማሰር የሚያስቀር ምእላድ። *ስፈልግ/ ሲመጣ/ ሳያልፍ*።

**- ስ** 1. ጥያቄን ለማስከተል በተፈለገ ጊዜ በቃል መጨረሻ የሚገባ ምእላድ።"-ሳ"ም ይሆናል። *እርሳሱን አገኘሁት፥ መፅሃፉስ/ቢመጣስ ምን አደርጋለሁ*። 2. አፍራሽን ወይም የአወዳዳሪ ሃሳብን

በሚያስከትሉ ቃላት መጨረሻ የሚገባ ምእላድ:: *መስማትስ ትሰማላችሁ ግን ልብ አታደርጉም /ዝግጅትስ የበሬቱ ይበልጣል::*

**ስሃ** "ስሃ" ን ተመ.

**ስህተተኛ** "ሳተ" ስር ተመ.

**ስህተት** ዝ.ከ.

**ስለ** 1. ቀጥሎ ወይም ተከትሎ "ለተጠቀሰው ነገር÷ ሃሳብ ሲባል" ለማለት የሚገባ ምእላድ:: *ስለ እግዚአብሄር ብለህ አታስቸግር::* (ብዙውን ጊዜ ከግስ ወይም ከስም ጋር እየተጣመረ የሚነገር):: 2. ቀጥሎ ወይም ተከትሎ "የተጠቀሰውን ቃል ወይም ርእስ" በሚመለከት የሚገባ ምእላድ:: *ስለሃይማኖት ብዙ ተነጋግረናል/ ስለመፅሃፉ ጉዳይ በእኔ ጣለው::* 3. ምክንያትን ለመግለፅ ወይም ለማመልከት የሚገባ ምእላድ:: *መኪና ስለተበላሸ ዛሬ ልንሄድ አንችልም::* 4."እንደ" ለማለት የሚገባ:: *ይህ የማሽላ እንጀራ እንዴት ጥሩ ነው! ስለ ጤፍ ይቆጠራል::* 5. በአንድ ነገር ወይም ሰው ምትክ መደረጉን ለማመልከት የሚያገለግል:: *ስለእኛ ሞተ::*

**ስለምን** ተው.ግ. በምን ምክንያት÷ በምን መልኩ÷ ለምን::

**ስለዚህ** መ.ዓ. 1. ይህንን በሚመለከት÷ በዚህ ርእስ:: *ስለዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት ተወያይተናል::* 2. በዚህ ምክንያት:: *ሰአቱ ደርሷል፤ ስለዚህ መሄድ አለብኝ::*

**ስለላ** "ሰለለ[2]" ስር ተመ.

**ስለታም** "ሳለ[2]" ስር ተመ.

**ስለት[1]** ዝ.ከ.

**ስለት[2]** "ሳለ" ስር "ስእለት" ን ተመ.

**ስሉስ** "ሰለሰ" ስር ተመ.

**ስሉጥ** ቅ ስልጡን÷ ከተፎ::

**ስላሴ** "ሰለሰ" ስር ተመ.

**ስላቅ** "*ሰለቀ" ስር ተመ.

**ስላች** ስ ቀጭን÷ አቋራጭ መንገድ::

**ስሌት** "*ሰላ" ስር ተመ.

**ስል[1]** "ሰላ[1]" ስር ተመ.

**ስል[2]** "ሰላ[3]" ስር ተመ.

**ስል[3]** "ሳለ[2]" ስር ተመ.

**ስልል**

**ስልል አይገባውም** ዘወር ያለ አነጋገር አይገባውም::

**ስልምልም** "ሰለመ[2]" ስር ተመ.

**ስልሳ(ስድሳ)** ስ 1. በሃምሳ ዘጠኝና በስልሳ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ:: በአሃዝ ሲፃፍ ፷ ÷ 60 ነው:: ቅ 2. የስድስት አስሮች ድምር የሆነ::

**ስልስ** ስ በቲማቲምና በሽንኩርት የሚሰራ እንደ ወጥ ያለ ማባያ::

**ስልቅ** "ሰለቀ" ስር ተመ.

**ስልባቦት** ስ ከፈላ ወተት አናት ላይ የሚጋገር የወተት ቅባት::

**ስልብ** "ሰለበ" ስር ተመ.

**ስልት** ስ 1. ዘዴ÷ ብልሃት÷ መንገድ (የአሰራር÷ የነገር÷...):: 2. ምት (የሙዚቃ÷ የዳንስ÷...):: 3. ክፍል÷ አይነት÷ ወገን:: *እቃውን በስልት በስልቱ አስቀመጠ::*

**ስልተ ምርት** ስ አንድ ህብረተሰብ ምርት የሚያመርትበትና የተመረተውንም የሚከፋፈልበት መንገድ ወይም ስርአት::

**ስልቹ** "ሰለቸ" ስር ተመ.

**ስልቻ** ስ ከፍየል ወይም ከበግ÷... ቆዳ ተለፍቶ የሚዘጋጅ ከረጢት፤ አቁማዳ::

**ስልክ** ስ ሩቅ ለሩቅ ያሉ ሰዎች ድምፅን በሽቦ ወይም በአየር በማስተላለፍ የሚነጋገሩበት የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ፤ ቴሌፎንም ይባላል::

**ስልክ ደወለ** በስልክ አማካይነት ከሚፈልገው ሰው÷ ድርጅት÷...ጋር መገናኘት የሚያስችል ጥሪ አደረገ::

**ስልክ ቁጥር** ስ ለእያንዳንዱ ስልክ መስመር የሚሰጥ የጥሪ መለያ ቁጥር::

**ስልክ እንጨት** ስ የስልክ ሽቦ ወይም መስመር የተዘረጋበት ረጅም ምሰሶ::

**የስልክ መስመር** ስ የስልክ መገናኛ::

**የስልክ ማውጫ** ስ የስልክ ደንበኞችን ስም÷ አድራሻና የስልክ ቁጥራቸውን የያዘ መዝገብ::

**የስልክ ጥሪ** ስ በስልክ አማካይነት የሚደረግ ግንኙነት::

**ስልከኛ** ስ የስልክ ጥሪዎችን የሚቀበልና የሚያገናኝ ወይም መልእክት የሚያስተላልፍ ሰራተኛ::

**ስልክልክ** "*ሰለከለከ" ስር "ሰለክላካ" ን ተመ.

**ስልጆ** ስ ከባቄላ ዱቄትና ከሰናፍጭ የሚዘጋጅ እንደ ወጥ ያለ ማባያ::

**ስልጡን** "ሰለጠነ" ስር ተመ.

**ስልጣኔ** ዝ.ከ.

**ስልጣን** ዝ.ከ.

**ስመኛ** "ስም" ስር ተመ.

**ስሙኒ** ስ የብር አንድ አራተኛ፤ ሃያ አምስት ሳንቲም::

**ስሚ** "ሰማ[1]" ስር ተመ.

**ስሚንቶ** "ሲሚንቶ"ን ተመ.

**ስሚዛ** ስ ግንዱ አንጓ ያለውና በቀላሉ ሊሰበር የሚችል፥ ቅጠሉ ሰፋ ሰፋ ያለ የእፅዋት አይነት፤ ሰንሰል::

**ስማርድ** ስ የአውሬ ወጥመድ::

**ስማ በለው** "ሰማ[1]" ስር ተመ.

**ስሜታዊ** "ሰማ[1]" ስር ተመ.

**ስሜት** ዝ.ከ.

**ስም** ስ 1. ለማንኛውም ሰው፥ ነገር፥ ቦታ፥... የሚሰጥ መጠሪያ:: 2.(ሰዋ.) ለግሱ እንደ ባለቤት ወይም ተሳቢ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል የሰው፥ የቦታ፥ የነገር፥ መጠሪያ ቃል:: 3. አንድ ሰው ወይም ድርጅት የሚታወቅበት ስራ፥ ተግባር፥...::*በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ጥሩ ስም የለውም::*

**ለስሙ** 1. ለይስሙላ ያህል፥ ለወሬው ያህል:: *ለስሙ የሃብታም ቤት ነው፥ ነገር ግን ጥሩ ኑሮ ሳይኖሩም*:: 2. ለክብር፥ ለዝና ሲባል:: *ለስሟ መጠሪያ ቀና ሰፋች::*

**በ__ ስም** 1. __ን ሽፋን በማድረግ:: *በህዝብ ስም ማጭበርበር አይገባም*:: 2. ስለ_:: *በእግዚአብሄር ስም የተባረከ ይሁን*: 3. __ን በመወከል:: *በስራ አስኪያጁ ስም ገንዘቡን ያንቀሳቅሳል::* 4. ለ__ እንዲሆን፤ ለ__ተብሎ:: *በእርዳታ ስም ብዙ እህል ተላከ::*

**ስሙ ጠፋ** በክፉ ተነሳ፥ ተጠራ::

**ስም ሰበረ** የሰውን ስም አጠፋ፥ አጎደፈ፥ በመጥፎ አነሳ::

**ስም ሰጠ** 1. በመጥፎ አነሳ፥ ስም አጠፋ፥ አማ:: 2. ሰየመ፥ መጠሪያ አወጣ:: 3. አፃፈ፥ አስመዘገበ (ስሙን)::

**ስም ተከለ** በየጊዜው ስሙ እንዲጠራ፥ እንዲታወስ አደረገ(ብዙውን ጊዜ በጥሩ ስራ)::

**ስም አስጠራ** 1. ታዋቂ፥ ዝነኛ እንዲሆን አደረገ፥ አስመሰገነ:: 2. የሟችን የክርስትና ስም በማውሳትና በማስጠራት አስቀረበ፥ አስቀደሰ፤ ዘከረ::

**ስም አወጣ** ሰየመ፥ መጠሪያ ሰጠ::

**ስም አጠፋ** የሰውን ታሪክ ወይም ዝና በመጥፎ አነሳ፥ አጎደፈ፥ ያልሆነውን ሆነ በማለት አወራ፥ አማ::

**ስም አጥፊ** ቅ የሰውን ታሪክ፥ ዝና፥... በመጥፎ የሚያነሳ፥ የሚያጎድፍ፥ ሃሜተኛ::

**ስም ጠራ** 1. የተመዘገበ የስም ዝርዝር ጠራ:: 2. በፀሎት ላይ የሟችን የክርስትና ስም አነሳ::

**ስመጥር (ስመጥሩ)** ቅ የታወቀ፥ ዝነኛ (በጀግንነቱ፥ በሃብቱ ወይም በሌላ ስራው)::

**ስም አይጠሬ** ስ ስሙን በግልፅ መጥራት መጥፎ ነው ተብሎ የሚታነመንበትን እንደ እባብ፥ ጉንዳን፥ አባጨጓሬ፥... ያለን ነገር ለመጥራት የሚያገለግል ተለዋጭ ስም:: *ስም አይጠሬ መጣ::*

**ስም ጠሪ** ስ የሰዎችን የስም ዝርዝር ይዞ ስም በመጥራት፥ያለውንና የሌለውን ሰው የሚቆጣጠር (ሰው)::

**የስም መጥሪያ** ስ የስም ዝርዝር ያለበት መዝገብ ወይም ወረቀት::

**ስመኛ** ቅ ስም አጥፊ፥ ሃሜተኛ::

**ስምሙ** "ሰማ[1]" ስር ተመ.

**ስምም** ዝ.ከ.

**ስምምነት** ዝ.ከ.

**ስምረት** "ሰመረ" ስር ተመ.

**ስምሪት** "*ሰማራ" ስር ተመ.

**ስምንት** ስ 1. በሰባትና በዘጠኝ መካከል ያለ ቁጥር:: በአሃዝ ሲፃፍ ፰ ፥ 8 ነው:: ቅ 2. ብዛቱ ሁለት አራቶችን የሆነ::

**ስምንተኛው ሺህ** ስ ክፋትና ተንኮል የሚበዛበት የአለም መጨረሻ ወይም የምፅአት ጊዜ ይሆናል ተብሎ የሚታመንበት ዘመን::

**ስምጥ** "ሰመጠ" ስር ተመ.

**ስሞተኛ** "ሰማ[1]" ስር ተመ.

**ስሞታ** ዝ.ከ.

**ስረ_** "ስር[1]" ስር ተመ.

**ስሪት** "ሰራ[2]" ስር ተመ.

**ስሪያ** "ሰረረ" ስር ተመ.

**ስራ** "ሰራ[1]" ስር ተመ.

**ስራይ** ስ 1. በሰው ላይ ጉዳት የሚያደርስ መድሃኒት ወይም መርዝ:: 2. እንደ ጨጓራ በሽታ ያለ የሆድ ውስጥ ህመም፤ ደዌ::

**ስር[1]** ስ 1. ማንኛውም እፅዋት ምግቡን ከአፈር ውስጥ የሚወስድበትና ከመሬት ወለል በታች የሚውለው የተክሉ አካል:: 2. በሰው፥ በእንስሳትና በአእዋፍ አካል ውስጥ የደም ማመላለሻ ሆኖ የሚያገለግል ቀጫጭን ጅማት:: 3. ታችኛ ስፍራ:: 4. መነሻ፥ መጀመሪያ፥ መሰረት:: *ነገር ከስሩ ውሃ ከጥሩ:* 5. አጠገብ:: *ከስሬ አይጠፋም::*

**በ__ ስር** መዋ. 1. በ _ በታች:: 2. በ ___ ውስጥ:: *በጭቃና ስር ይማቅቃሉ::*

**ከ__ ስር** መዋ. ከ _ በታች::

**ስር ሰደደ** 1. ፀደቀ፥ ስሩ ወደታች ረዘመ፥ ጠለቀ:: 2. ተደላደለ፥ መሰረት ያዘ፥ ፀና::

**ስር ያዘ** 1. መሰረት ያዘ:: 2. ስር ሰደደ፥ ፀደቀ (ተክል)::

**ከስር** ከመነሻ፥ ከመሰረት፥ ከመጀመሪያ።

**ስረ መሰረት** ስ መነሻ፥ መጀመሪያ (የሃሳብ፥ የነገር፥...)።

**ስረ ነገር** ስ የነገር መነሻ።

**ስረ ወጥ** ቅ ቅጥያ የሌለውና አንድ ወጥ ሆኖ የተሰራ።

**ስረ ብዙ** ስ ስሩ ለጉንፋንና ለሳል መድሃኒት ይሆናል የሚባል አነስተኛ የሆነ የእፅዋት አይነት።

**ስራስር** ስ 1. እንደ ድንች የመሳሰሉና በምግብነት የሚያገለግሉ፥ ወፍራም ስር (ፍሬ) ያላቸው የተክል አይነቶች። 2. ለመድሃኒትነት የሚያገለግል የእፅዋት ስር።

**ስር ሚዜ** ስ አንደኛ ሚዜ።

**ስር ማሽ** ስ የስራስር መድሃኒት አዋቂ፣ ጠንቋይ፥ መድሃኒተኛ፥ መተተኛ።

**ስርነቀል** ቅ ከስር ከመሰረቱ ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጣ።

**ስርነቀል ለውጥ** ስ በአንድ ነገር ላይ የሚታይ ፈጣንና መሰረታዊ የሆነ የአይነት ለውጥ።

**ስርኩል** ስ ተፈጭቶ የሚዘጋጅ የኩል አይነት።

**ስር ጠምዛዥ** ስ መተተኛ፣ በአስማት ወይም በመተት ሰው ይገላል የሚባል።

**የስር ፍርድ ቤት** ስ አንድን ጉዳይ ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፊት በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት።

**ስርቻ** ስ የማይታይ፥ ሰዋራ፥ ደባቃ ቦታ።

**ስር**[2] “ስራ[1]” ስር ተመ.

**ስር**[3] “ስራ[2]” ስር ተመ.

**ስርቅ**

**ስርቅታ (ስቅታ)** ስ 1. ለመተንፈሻነት የሚያገለግለው ጡንቻና (ዲያፍራም) የአየር ቧንቧ እየተደጋገመ ሲኮማተር የሚፈጠር፥ ጉሮሮን እንቅ እያደረገ የሚወጣ ድምፅ፥ ሀቅታ። 2. የመጨረሻ የህይወት ትንፋሽ።

**ስርቅ (ስቅ) አለው** ሀቅ አለው፥ ስርቅታ ያዘው።

**ስርአት** ስ 1. አንድ ነገር የሚሰራበት ወይም የሚከናወንበት ደንብ፥ ህግ። 2. ወግ፥ ባህል።

**ስርአት ያዘ** ተስተካከለ፥ ጥሩ መልክ ያዘ።

**ስርአተ ማህበር** ስ በተወሰነ የእድገት ደረጃ የሚገኝ ህብረተሰብ ስልተ ምርትና ማህበራዊ ግንኙነት የተመሰረተበት ሁኔታ፥ የማህበረሰቡ የአመራረት፥ የአኗኗርና የአመለካከት ዘይቤ መሰረት።

**ስርአተ ቀብር** ስ በቀብር ጊዜ የሚከናወን ስነስርአት።

**ስርአተ ትምህርት** ስ ለትምህርት አላማ ግብ መምታት በእቅድ እየተዘጋጀ በት/ቤቶች በየደረጃው የሚሰጥ አጠቃላይ የትምህርት ይዘት።

**ስርአተ ንግስ** ስ ታቦት ወይም ንጉስ በሚነግስ ጊዜ የሚደረግ ፀሎትና ስነ ስርአት።

**ስርአት አልበኛ** ቅ 1. የመንግስትን፥ የደንብንና የስነ ስርአትን መኖር የሚቃረን ወይም የሚቃወም። 2. በጥባጭ፥ አዋኪ።

**ስርቅታ** “ስርቅ” ስር ተመ.

**ስርቆሽ** “ስረቀ[1]” ስር ተመ.

**ስርቻ** “ስር[1]” ስር ተመ.

**ስርወ**

**ስርወ መንግስት** ስ በዘር ግንድ ላይ የተመሰረተ ተከታታይነት ያለው የንግስና ሃረግ።

**ስርወ ቃል** ስ ለሌላው መገኛ የሚሆን ወይም ሌላ ምእላድ የሚቀጠልበት መሰረታዊ ወይም መነሻ ቃል።

**ስርዋፅ** ስ 1. እንደማስረጃ ሆኖ በነገር መካከል የሚገባ ተጨማሪ ቃል። 2. ሽብልቅ፥ ውሻል።

**ስርዝ** “ሰረዘ” ስር ተመ.

**ስርየት** “*ሰረየ” ስር ተመ.

**ስርጓጉጥ** ቅ ወጣ ገባ የሆነ (ቦታ)።

**ስርጥ** “ሰርጥ” ን ተመ.

**ስርጭት** “*ሰረጨ” ስር ተመ.

**ስሱ** “ሳሳ[2]” ስር ተመ.

**ስስ** “ሳሳ[1]” ስር ተመ.

**ስስታም** “ሳሳ[2]” ስር ተመ.

**ስስት** ዝ.ከ.

**ስቃይ** “*ሰቀየ” ስር ተመ.

**ስቅለት** “ሰቀለ” ስር ተመ.

**ስቅላት** ዝ.ከ.

**ስቅታ** “ስርቅ” ስር “ስርቅታ” ን ተመ.

**ስበበኛ** “*ሰበበ” ስር “ሰበበኛ” ን ተመ.

**ስበብ** “*ሰበበ” ስር “ሰበብ” ን ተመ.

**ስበት** “ሳበ” ስር ተመ.

**ስባሪ** “ሰበረ” ስር ተመ.

**ስባት** “ሰባ” ስር ተመ.

**ስብ** ዝ.ከ.

**ስብራት** “ሰበረ” ስር ተመ.

**ስብርባሪ** ዝ.ከ.

**ስብሰባ** “ሰበሰበ” ስር ተመ.

**ስብሳብ** “ሰበሰበ” ስር “ሰበሰብ” ን ተመ.

**ስብስብ** “ሰበሰበ” ስር ተመ.

**ስብስብ** “ሰበሰበ” ስር “ስብሰባ”ን ተመ.

**ስብቀት** “ሰበቀ[2]” ስር ተመ.

**ስብቅል[1]** ቅ ያማረ፥ የተዋበ::

**ስብቅል[2]** “*ሰበቀለ” ስር ተመ.

**ስብከት** “ሰበከ” ስር ተመ.

**ስብድብድ** “*ሰበደበደ” ስር “ሰበድባዳ”ን ተመ.

**ስብጥር** “ሰበጠረ” ስር ተመ.

**ስቱኮ (እስቱኮ)** ስ 1. የበር ወይም የመስኮት መስታወት እንዳይንገጫገጭ መስተዋቱ በገባበት ስንጥቅ ውስጥ የሚጠቀጠቅ እንደ ጭቃ ያለ ማጣበቂያ:: 2. ከቀለም ቅብ በፊት ስንጥቃትን ለመድፈንና ቀለም እንዲቀበል ለማድረግ ግርግዳ ላይ የሚቀባ ኖራ መሰል ነገር::

**ስቴንስል** ስ በላዩ ላይ ፅሁፍ ከተቀረፀበት በሂላ የተቀረፀውን ፅሁፍ በማባዣ መኪና አማካይነት በሌላ ወረቀት ላይ በተፈለገው ብዛት እያተሙ ለማውጣት የሚያስችል ልዩ የወረቀት አይነት::

**ስቴዲዮም(እስታዲዮም)** ስ ተመልካቾችንና ተወዳዳሪዎችን እንዲይዝ ተደርጎ የተከለለ፥ የተለያዩ ስፖርታዊ ክንውኖች (ብዙውን ጊዜ እግር ኳስ ጨዋታ) የሚካሄድበት ቅጥረ ግቢ፥ ሜዳ፤ ካምቦሎጆም ይባላል::

**ስቴፕለር(እስቴፕለር)** ስ የስቴፕለር መርፌ በውስጡ ተጨምሮበት ወረቀትን ለማያያዝ ወይም ለመስፋት የሚያገለግል መሳሪያ (ስእሉን የፅህፈት መሳሪያ ስር ተመ.)::

**ስቴፕለር መርፌ** ስ በስቴፕለር ውስጥ ተጨምሮ ወረቀት ለማያያዣ ወይም ለመስፊያ የሚያገለግል ሽቦ (ስእሉን የፅህፈት መሳሪያ ስር ተመ.)::

**ስነ—**1. ውበትን የሚያመለክትና ከቃል በስተመነሻ ላይ የሚቀጠል ተጣማሪ ምእላድ:: *ስነ ግጥም*:: 2. ጥናት፥ ሳይንስ የሚለውን ለማመልከት ከቃል በስተመነሻ ላይ የሚቀጠል ተጣማሪ ምእላድ:: *ስነልሳን፥ ስነልቦና፥*...::

**ስነልሳን** ስ ቋንቋን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያጠና የእውቀት ዘርፍ::

**ስነልቦና** ስ 1. የአንድ ህዝብ የአስተሳሰብ ሁኔታ:: 2. የአእምሮን፥ የአስተሳሰብን፥ የሰውን ባህርይ ሁኔታ የሚያጠና ሳይንስ፤ ስነ አእምሮም (ሳይኮሎጂ) ይባላል::

**ስነልቦናዊ ዘይቤ** ስ አንድ ህዝብ ወይም ህብረሰተብ ከአኗኗሩ፥ ከልምዱ የተነሳ በአእምሮው ውስጥ ያለው ስሜት፥ አስተሳሰብ፥ አመለካከት::

**ስነ መለኮት** ስ የአምላክን ባህርይና ተግባራት የሚያጠና የሃይማኖታዊ ትምህርት ዘርፍ፤ ትምህርተ መለኮት::

**ስነ ምግባር** ስ 1.መልካም ጠባይ ወይም አድራጎት:: 2. በአንድ የሙያ መስክ ከባለሙያው የሚጠበቅ መልካም አድራጎት ወይም አሰራር:: 3. መልካምም ሆነ መጥፎ ባህርይ ወይም አድራጎት::

**ስነ ስርአት** ስ 1. ዲሲፕሊን፥ ስነ ምግባር:: 2. ደንብ፥ ህግ:: 3.አንድን ድርጊት በተመለከተ የተለመደ ስርአትን ወይም ደንብን ተከትሎ የሚሄድ ክንውን::

**ስነ ስቅለት** ስ የክርስቶስን ስቅለት የሚያሳይ ስእል ወይም ቅርፅ::

**ስነቃል** ስ እንደ ተረት፥ እንቆቅልሽ፥ ምሳሌያዊ አነጋገር፥ የሰርግ፥ የለቅሶ ግጥም፥... ያለ ከትውልድ ወደትውልድ በቃል የሚተላለፍ አፍአዊ ስነፅሁፍ፤ ኪነ ቃልም (ኪነተ ቃልም) ይባላል::

**ስነአእምሮ** የ “ስነልቦና” ን ሁለተኛ ፍቺ ተመ.

**ስነውበት** ስ ስለውበት ምንነት፥ አመጣጥ፥ እድገት፥ ህግና ሚና በማጥናት ስለኪነጥበብ አጠቃላይ ግንዛቤ የሚሰጥ የፍልስፍና ዘርፍ ::

**ስነጥበብ** ስ ስእልን፥ ቅርፃ ቅርፅን፥ ሙዚቃንና ስነ ፅሁፍን የመሳሰሉ ውበትን የሚያሳዩ የፈጠራ ስራዎች ሙያ::

**ስነፅሁፍ** ስ 1.በልብ ወለድ ወይም በግጥም መልክ የሚዘጋጅና ህይወትን ውብ በሆነ መልክ የሚያንፀባርቅ የፈጠራ ስራ:: 2. በአንድ ሃገር ውስጥ ባሉ ቋንቋዎች ተፅፎ የሚገኝ ማናቸውም የፅሁፍ ስራ::

**ስነፈለክ** ስ ስለከዋክብት ሁኔታና በልዩ ልዩ ነገሮች ባህርይ ወይም እጣ ላይ ስለሚያሳድሩት ተፅዕኖ የሚያጠና የሳይንስ ዘርፍ::

**ስነፍጥረት** ስ 1. በምድርም ሆነ በሰማይ ላይ ያሉ ፍጥረታት በሙሉ:: 2. በአለም ላይ ስላሉት ፍጥረታት የሚያጠና ሳይንስ::

**ስኒ** “ሲኒ” ን ተመ.

**ስናር በቅሎ** ስ ፈጣንና ሰጋር የሆነ ረዥም በቅሎ (ከሱዳን ይመጣ የነበረ)::

**ስናግ** “ሰነገ[1]” ስር ተመ.

**ስንቀን** ስ የተፈጨ ወይም የተደቆሰ ትንባሆ፤ ሱረት::

**ስንቅ** “ሰነቀ” ስር ተመ.

**ስንቆ** ስ እንደ ጎመን ያለና ተቀቅሎ የሚበላ የቅጠል አይነት::

**ስንቡል** ስ ጥሩ መአዛ ያለው የሽቶ አይነት::

**ስንባጭ** "ሰነበጠ" ስር ተመ.

**ስንብት** "ሰነበተ" ስር ተመ.

**ስንት** ቅ ቁጥርን፥ መጠንን፥ ብዛትን መጠየቂያ ቃል (ምን ያህል? ማለት ነው)።

**ስንትና ስንት** ብዙ።*ስራዎቹ ስንትና ስንት ነው።*

**ስንተኛ** ቅ 1. የአንድን ነገር የጥራቱን ወይምየአመጣጡን ቅደም ተከተል ወይም ያለውን ደረጃ ለማወቅ የመጠየቂያ ቃል። *በትምህርትህ ስንተኛ ወጣህ/ ስንተኛ ደረጃ ቡና ነው።* 2. ተራን፥ የድግግም ብዛትን መጠየቂያ ቃል። *ስንተኛ ነህ / እዚህ ስትመጣ ስንተኛህ ነው።*

**ስንቴ(ስንትዬ)** ስንት ጊዜ።

**ስንትር** "ሰነተረ" ስር ተመ.

**ስንኝ** "*ሰነኘ" ስር ተመ.

**ስንኩል** "ሰነከለ" ስር ተመ.

**ስንክሳር** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) 1. የመላእክትን፥ የነቢያትን፥ የሃዋርያትን፥ የፃድቃንን፥ የሰማእታትን፥ የደናግልን፥ የመነኮሳትን፥ ወዘተ. የህይወት ታሪክ አጠናቅሮና አካቶ የያዘ ከአመት እስከ አመት የየእለቱን የገድል ታሪክ የሚናገር መጠነ ትልቅ የቤተ ክርስቲያን መፅሃፍ። 2. (ዘይ.) ሀ- ሃተታ የበዛበት፥ የተንዛዛ ነገር። ለ- ጣጣ። *ስንክሳርሩ በዛ።*

**ስንኳን** "እንኳን[1]" ን ተመ.

**ስንዝር** "ሰነዘረ[1]" ስር ተመ.

**ስንደዶ** ስ ለስፌት እቃና ለገመድ መስሪያ የሚያገለግል ረዘም ያለና ጠንካራ የሆነ የሳር አይነት።

**ስንደዶ አፍንጫ** ስ ቀጥ ያለና የተዋበ አፍንጫ።

**ስንዱ** "*ሰነደ" ስር ተመ.

**ስንዴ** ስ ፍሬው ተቆልቶ፥ ተቀቅሎ የሚበላ ወይም ተፈጭቶ፥ ተከክቶ ልዩ ልዩ የምግብ አይነቶችን ለማዘጋጀት የሚሆን የእህል አይነት።

**ስንድቅ** "ሰነደቀ" ስር ተመ.

**ስንድድ** ስ ሴቶች በእግራቸው ላይ የሚያደርጉት የወሎ ጌጥ።

**ስንግ[1]** ስ የእንግዴ ልጅ።

**ስንግ[2]** "ሰነገ[2]" ስር ተመ.

**ስንጣሪ** "ሰነጠረ" ስር ተመ.

**ስንጣቂ** "ሰነጠቀ" ስር ተመ.

**ስንጥሬ** ስ ፈዥምና ሹል መንቆር ያለውና ረግረጋማ በሆነ ቦታ የሚኖር የወፍ አይነት።

**ስንጥር** "ሰነጠረ" ስር ተመ.

**ስንጥቅ** "ሰነጠቀ" ስር ተመ.

**ስንፍና** "ሰነፈ" ስር ተመ.

**ስእለት** "*ሳለ" ስር ተመ.

**ስእል** "ሳለ[1]" ስር ተመ.

**ስካር** "ሰከረ" ስር ተመ.

**ስካቶላ** ስ በተበረበረ ግድግዳ ውስጥ ገብቶ የሚጣበቅ የስልክ ወይም የኤሌክትሪክ ሶኬት አቃፊ።

**ስኬታማ** "ሰካ" ስር ተመ.

**ስኬት** ዝ.ከ.

**ስክ** ዝ.ከ.

**ስክሪቢቶ (እስክሪብቶ)** ስ ለመፃፊያ የሚሆን የጭቃ ቀለም ብእር።

**ስኮላርሺፕ (እስኮላርሺፕ)** ስ በመንግስት ወይም በሌላ ድርጅት እርዳታ አማካይነት የሚሰጥ የነፃ ትምህርት እድል።

**ስኮላርሺፕ አገኘ** ነፃ የከፍተኛ ትምህርት እድል ተሰጠው።

**ስኮችቴፕ (እስኮች ቴፕ)** ስ በአንድ በኩል ሙጫነት ያለው ከፕላስቲክ የሚሰራ ማጣበቂያ።

**ስኳር** ስ በሻይ፥ በኬክ፥...ውስጥ የሚገባ ከሸንኮራ አገዳ ወይም ከሌላ ነገር የሚሰራና ጣፋጭነት ያለው ነጭ የሆነ ደቃቅ ነገር።

**ስኳር ድንች** ስ ጣፋጭነት ያለው የድንች አይነት።

**የስኳር በሽታ** ስ በጣፊያ መታወክ ምክንያት በደም ውስጥ ከሚፈለገው በላይ ወይም ተመጣጣኝ ያልሆነ ስኳር እንዲገኝ የሚያደርግ በሽታ።

**ስውር** "ሰወረ" ስር ተመ.

**ስያሜ** "ሰየመ" ስር ተመ.

**ስደተኛ** "ሰደደ" ስር ተመ.

**ስደት** ዝ.ከ.

**ስድ** ዝ.ከ.

**ስድሳ** "ስልሳ" ን ተመ.

**ስድስት** ስ 1. በአምስትና በሰባት መካከል ያለ ቁጥር ሞጠሪያ። በአሃዝ ሲፃፍ ፮፥ 6 ነው። ቅ 2. ብዛቱ ሁለት ሶስቶችን የሆነ። *ስድስት ቤቶች።*

**ስድስቶ(ስድስቶሽ)** ስ በአንድነት እጅብ ብለው በሰማይ ላይ የሚታዩ የስድስት ከዋክብት መጠሪያ።

**ስድብ** "ሰደበ" ስር ተመ.

**ስጉ** "ሰጋ" ስር ተመ.

**ስጋ** ስ 1. የሰውን፥ የእራዊትን፥ የአእዋፍን፥... አጥንት ሸፍኖ ከቆዳ በታች የሚገኘው ስብና

ጡንቻ ቅልቅል ያለበት ገላ:: 2. ለምግብነት የሚያገለግል የእንስሳ ስጋ፤ ብልት:: *የበሬ ስጋ/የበግ ስጋ::* 3. ዘመድ፥ ወገን::

**ስጋ ሆነ** ሰው ሆኖ ታየ ወይም ተገለጠ፥ የሰውን ባህርይ ያዘ (ክርስቶስ)::

**ስጋ ለበሰ** 1. ዝ.ከ.:: 2. በስጋ ተሸፈነ (እሾህ)::

**ስጋ ለባሲ** ቅ ስጋ የለበሰ (ሰው)::

**ስጋዋን ሸጠች** ሸረሞጠች (ገንዘብ ለማግኘት)::

**ስጋ ያዘ** ወፈረ፥ ደለበ (ከብቱ)::

**የ __ ን ስጋ** እውነትነትን ለማረጋገጥ የሚደረግ መሃላ (የአባቴን ስጋ፥ የእናቴን ስጋ እንደማለት)::

**ስጋ መብላት** ማማት:: *በሆነ ባልሆነው የሰው ስጋ መብላት ይወዳል::*

**ስጋ በል** ቅ ስጋ ብቻ የሚመገቡ እንስሳት (እንደ አንበሳ፥ ነብር ያሉ)::

**ስጋ ቤት** ስ 1. የስጋ ክፍል ሹም:: 2. ስጋ የሚሸጥበት ቤት፤ ልኳንዳም ይባላል::

**ስጋ ወደሙ** ስ በህብስትና በወይን መልክ የሚቀርብ የኢየሱስ ክርስቶስ ስጋና ደም፤ ቁርባን፤ መስዋእት::

**ስጋ ወደሙ ተቀበለ** ቆረበ::

**ስጋደዌ (ደዌስጋ)** ስ የቁምጥና በሽታ::

**የስጋ ትል** ስ ባልተዘለዘለና በቂ አየር ባላገኘ ወይም የሚደርቅበት አመቺ ሁኔታ ባልተፈጠረለት ስጋ ላይ የሚፈጠር ትል::

**የስጋ ዘመድ** ስ በደም ወይም በትውልድ የሚገናኙት ዘመድ::

**ስጋዊ** ቅ አለማዊ፤ መንፈሳዊ ያልሆነ::

**ስግነት** ዝምድና::

**ስጋት** "ስጋ" ስር ተመ .

**ስጋዊ** "ስጋ" ስር ተመ.

**ስጋጃ** ስ ከእንስሳት ፀጉር ወይም ከቃጫ ወይም ከክር፥... የሚሰራ ምንጣፍ::

**ስግስግ** "ሰገሰገ" ስር ተመ.

**ስግብግብ** "*ሰገበገበ" ስር ተመ.

**ስግነት** "ስጋ" ስር ተመ.

**ስግደት** "ሰገደ" ስር ተመ.

**ስጎ(ሱጎ)** ስ ለፓስታ፥ ለማካሮኒ፥... ማባያ የሚሆንና ከቲማቲም፥ ከስጋ፥...እና ሌሎች ማጣፈጫዎች የሚዘጋጅ የወጥ አይነት::

**ስጥ** "*ሰጣ" ስር ተመ.

**ስጦታ** "ሰጠ" ስር ተመ.

**ስፋት** "ሰፋ[2]" ስር ተመ.

**ስፌት** "ሰፋ[1]" ስር ተመ.

**ስፍራ** "ሰፈረ[2]" ስር ተመ.

**ስፒል(እስፒል)** ስ ምስማር መሰል የወረቀት ማያያዣ ቀጭን መርፌ::

**ስፓጌቲ(እስፓጌቲ)** ስ ፓስታ::

**ስፖርት** ስ እንደ ዳማና ቼዝ የመሳሰለ የቤት ውስጥ ውድድር እንዲሁም የሰውነትን ቅልጥፍና የሚጠይቅ እንደ እግር ኳስ፥ ሜዳ ቴኒስ ያለ ጨዋታ ወይም የአካል ማጠንከሪያ እንቅስቃሴ::

**ስፖርት ይሰራል** የስፖርት እንቅስቃሴ ያካሄዳል::

**ስፖርት ሜዳ** ስ ስፖርት የሚሰራበት ቦታ::

**የስፖርት ማዘውተሪያ [ስፍራ]** ስ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱበት ቦታ::

**ስፖርተኛ** ቅ በስፖርት ግጥሚያ ወይም በአካል ማሰልጠኛ እንቅስቃሴ ተሳትፎ ያለው::

**ስፖንዳ** ስ የከረምቦላ መጫወቻ ጠረጴዛ::

**ስፖንጅ** ስ ናይለን መሰል ከሆነ ነገር በፋብሪካ የሚሰራና ውሃ የመምጠጥ ባህርይ ያለው፥ ለፍራሽ፥ ለመቀመጫ፥ ለእቃ ማጠቢያ፥... የሚሆን ለስላሳ ነገር፤ ሰፍነግ::

**ስፖንጅ ትራስ** ስ ከስፖንጅ የተዘጋጀ ትራስ::

**ስፖንጅ ፍራሽ** ስ ከስፖንጅ የተዘጋጀ ፍራሽ::

**ሶ** የ "ሰ" ፊደል ሳብእ ዘር::

***ሶለሶለ**

**ሶልቧላ** ቅ ጦልጧላ፥ ወዲያ ወዲህ የሚንቀዠቀዥ፥ ዘዋሪ::

**ተንሶለሶለ** ግ ተንጦለጦለ፥ ወዲያ ወዲህ ተንቀዠቀዠ፥ ተንከለከለ::

**አንሶለሶለ** ግ አንጦለጦለ፥ ወዲያ ወዲህ አንቀዠቀዠ፥ አንከለከለ::

**ሶለግ(ሶሉግ)** ስ ከቁግ ከፍ ብሎ የሚገኘውና ቀጠን ያለው የጅራፍ አካል ወይም ክፍል (ሰእሉን ጅራፍ ስር ተመ.)::

**ሶለግ ውሻ** ስ ቀጭንና ሽንጠ ረዥም የሆነ አዳኝ ውሻ::

**ሶላት** "ሰላት" ን ተመ.

**ሶላቶ(ሰላቶ)** ስ ኢጣሊያዊ ወታደር::

**ሶልቧላ** "*ሶለሶለ" ስር ተመ.

**ሶሉግ** "ሶለግ" ን ተመ.

***ሶመሶመ**

**ሶምሶማ** ስ 1. ርትሪታ፤ ከደንገላላ በፊት ያለ

የፈረስ ሩጫ:: 2. ዝግ ያለና ሰውነትን ለማሟሟቅ የሚደረግ ሩጫ::

**አሰመሰመ** ግ አረተረተ፤ ደንገላሳ ለመጋለብ አኮበኮበ::

**ሰማያ** ስ 1. የጦር እጀታ:: 2. (ዘይ.) ቀጥ ብሎ መለል ያለ ቁመና ያለው (ሰው)::

**ሰምሰማ** "*ሰመሰመ" ስር ተመ.

**ሰሞሊና** ስ ለሙቅ፥ ለገንፎ፥ ለዳቦ፥ ... የሚሆን ፉርኖ ዱቄት::

**ሰረን** ቅ ቀይ (በሬ ወይም ላም)::

**ሰሬኔ (ሰረን)** ስ መልኳ ቀይ የሆነ የቆቅ አይነት::

**ሰራ** ስ 1. ግምጃ ወይም ሱቲ:: 2. የጥቁርና የነጭ ጠቃጠቆ ያለበት ከብት::

**ሰራ ወፍ (ሰሪት)** ስ የጥቁርና የነጭ ዝንጉርጉር የሆነች አብረቅራቂ ወፍ::

**ሰርዝ** ስ መልኩ ጥቁር የሆነ ራሰ ትልቅ አሳ::

**ሰስት** ስ 1. በሁለትና በአራት መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ:: በአሃዝ ሲፃፍ ፫÷3 ነው:: ቅ 2. ብዛቱ በሁለት ላይ አንድን የሚጨምር:: *ሰስት ልጆች::*

**ሰስቶ (ሰስቶች)** ስ በሰማይ ላይ መደዳውን በሰልፍ ሆነው የሚታዩ ሰስት ከዋክብት መጠሪያ::

**ሰስትያ** ቅ ከሰስት አንድ እጅ፤ ሲሶ::

**ሰሻሊስት** ቅ በሰሻሊዝም የሚያምንና የሚመራ፤ የሰሻሊዝም ተከታይ::

**ሰሻሊዝም** ስ 1. የማምረቻ መሳሪያዎች በህዝብ ቁጥጥር ስር የሚውሉበት ስርአተ ማህበር፤ ህበረተሰባዊነት:: 2. በካርል ማርክስና በፍሬድሪክ ኤንግልስ የተቀመረ የሳብ አደሩ መደብ ርእዮተ አለም::

**ሰታ** ቅ ለግላጋ፥ ወጣት፥ ጥሩ አቋም ያለው::

***ሰከሰከ**

**ሰክሷካ** ቅ ጦልጧላ፥ ወዲያ ወዲህ የሚል::

**ሱክሱክ አለ** ግ ጡል ጡል አለ::

**አሰከሰከ** ግ ሱክ ሱክ አለ::

**ሰኬት** ስ ለፕላግ ጡቶች መሰኪያ የሚሆኑ ቀዳዳዎች ያሉትና ከኮረንቲ ሽቦዎች ጋር የሚያያዝ የኤሌክትሪክ እቃ::

**ሰክሷካ** "*ሰከሰከ" ስር ተመ.

**ሰፋ** ስ ምቹ መቀመጫና ድጋፍ ያለው ወንበር፤ ፎቴ::

**ሷ** የ "ሰ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር::